አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የየምወድሽ በቀለ ወልደገብርኤል የሕይወት ታሪክና ስራዎቹ

በ

ዙፋን ካሳው

ሰኔ 2016 ዓ.ም.

አዲስአበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የየምወድሽ በቀለ ወልደገብርኤል የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ

በ

ዙፋን ካሳው

አማካሪ

ሙሐመድ አሊ (ዶ/ር)

ሰኔ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የየምወድሽ በቀለ ወልደገብርኤል የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ

በ

ዙፋን ካሳው GSR/9665/14

ሰኔ 2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**የፈተና ቦርድ አባላት**

**የአማካሪ ስም--------------------------------ፊርማ------------------------ቀን--------------**

**የውስጥ ፈታኝ ስም-------------------------ፊርማ----------------------ቀን------------**

**የውጭ ፈታኝ ስም---------------------------ፊርማ------------------------ቀን-------------**

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................................................................................ v

አጠቃሎ ....................................................................................................... vi

ምዕራፍ አንድ ................................................................................................ 1

መግቢያ ........................................................................................................ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ .................................................................................................. 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................................... 1

1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች ................................................................................ 2

1.4. የጥናቱ ዓላማ ............................................................................................... 2

1.5. የጥናቱ ፋይዳ ............................................................................................... 2

1.6. የጥናቱ ዘዴ ................................................................................................. 2

1.7. የመረጃ ምንጮች ............................................................................................ 3

1.7.1. ቃለመጠይቅ (ኢንተርቪው) ................................................................................ 3

1.7.2. ሰነድ ፍተሻ .............................................................................................. 4

1.7.3. ጥልቅ ምንባብ ............................................................................................ 4

1.8. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........................................................................... 4

1.9. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት እና ትንተና ......................................................................... 5

1.10. የጥናቱ ወሰን .............................................................................................. 6

1.11. የጥናቱ አወቃቀር (አደረጃጀት) ........................................................................... 6

ምዕራፍ ሁለት ................................................................................................ 7

ክለሳ ድርሳን ................................................................................................... 7

2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ......................................................................................... 7

2.1.1.የሕይወት ታሪክ ........................................................................7
2.1.2. የሕይወት ታሪክና ሥነፅሑፍ........................................................9
2.1.3. የሕይወት ታሪክ የአጻጻፍ መንገድ..........................................10
2.2. ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት .......................................................................11
2.2.1. ግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ (Biographical Narrative Theory).........11
2.2.2. ሥነማሕበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ (Sociological Theory ) ............12
2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት .............................................................13
2.3.1. የሁለተኛ ድግሪ ጥናቶች ..........................................................14
2.3.2. የመጀመሪያ ድግሪ ጥናት ..........................................................15
ምዕራፍ ሶስት .....................................................................................17
የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክ........................................................17
3.1. ልጅነትና የትምህርት ዘመን ..........................................................17
3.1.1. ልጅነት.....................................................................................17
3.1.2. የትምሕርት ቤት ሕይወት .........................................................18
3.2. የስራ ዓለም ..................................................................................19
3.2.1. ጋዜጠኝነት ...............................................................................19
3.2.2. የማህበራዊ አገልግሎት ስራ (ተጨማሪ ስራዎች).........................29
3.3. የግል አመለካከት እና ሃይማኖት.....................................................33
3.3.1. የግል አመለካከት.......................................................................33
3.3.2. ሃይማኖት..................................................................................36
3.4. ማሕበራዊ ሕይወት.........................................................................36
3.5.ትዳር (ጋብቻ)..................................................................................36
3.6. የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ......................................................................41
3.7. የድርሰት ሕይወት ..........................................................................42

3.7.1. የድርሰት አጀማመር ....................................................................42
3.7.2. የንባብ እና የአጻጻፍ ልማድ ..........................................................48
3.7.3. የድርሰት ስራዎች ብዛት ..............................................................49
3.7.4. የየምወድሽ በቀለ የግጥም መጻሕፍት ..........................................49
3.7.5. የየምወድሽ በቀለ የልቦለድ መጻሕፍት ........................................50
3.7.6. የየምወድሽ በቀለ ኢ. ልቦለድ መጻሕፍት....................................51
3.8. በድርሰት እና በሌሎች ስራዎች የተገኙ ሽልማቶች..........................51
ምዕራፍ አራት .........................................................................................53
የየምወድሽ በቀለ የተመረጡ ድርሰቶች ትንተና............................................53
4.1. የግጥም ስራዎች ...........................................................................53
4.1.1. "አብዮታዊ ግጥሞች" (የግጥም መድብል፣1972)...........................53
4.1.1.1. "ተነሱ ጭቁኖች".......................................................................53
4.1.1.2. "ተነሽ እቴ"...............................................................................55
4.1.1.3. "ሴቶች እንተባበር"....................................................................57
4.1.2. "ዋጊኖስ የግጥም መድብል" ( 2003 ዓ.ም.)..................................59
4.1.2.1. "አይጣል"..................................................................................59
4.1.2.2. "ሴት" ......................................................................................60
4.1.2.3. "ዋጊኖስ"..................................................................................61
4.2. የአጭር ልቦለድ ስራዎች ትንተና.......................................................62
4.2.1. "አናጋው" .....................................................................................63
4.2.2. "ወይ ሀገር" ...................................................................................64
4.2.3. "እንደዚህ ነው?".............................................................................66
4.2.4. "እነግረዋለሁ" ...............................................................................68
4.2.5. "የባከነ ጊዜ" ..................................................................................69

4.2.6. "ሙላቱ"........................................................................71
4.2.7. "ቂጭት" ......................................................................72
4.2.8. "ፈላጊዋ" ....................................................................73
4.3. ረጅም ልቦለድ..................................................................74
ምዕራፍ አምስት........................................................................78
ማጠቃለያ ..............................................................................78
ዋቢ ጽሑፎች............................................................................80
አባሪ ....................................................................................84

# ምስጋና

በመጀመሪያ ጥናቴን ጀምሬ እንድጨርስ ለረዳኝ ሀያሉ ልኡል እግዚአብሄር እና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ምስጋና ይሁን፡፡ ጥናቴን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ድረስ ሳይሰለች ላረመልኝ እና ላስተካከለልኝ አማካሪዬ ሙሐመድ አሊ(ዶ/ር) ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ ትምህርቴን ጀምሬ እስክጨርስ ተስፋ እንዳልቆርጥ ብርታት ለሆኑኝ ውድ ቤተሰቦቸ ለእናቴ የአለምወርቅ አለሙ፣ለእህቴ መአዛ ካሳው፣ለወንድሞቸ ደስታው ካሳው እና ጌታሰው ካሳው ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡እንዲሁም ለጥናቴ ሳትሰለች ሙሉ መረጃ በመስጠት የተባበረችኝ የምወድሽ በቀለን አመሰግናለሁ፡፡ስደክም ብርታት በመሆን ላገዙኝ እና ከጎኔ ለነበሩ ወዳጆቸ በሙሉ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# አጠቃሎ

‹‹የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ›› ጥናት በየምወድሽ በቀለ በስራና የሙያ የሕይወት ታሪክ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ ጥናቱ በዋናነት ከጋዜጠኛነት ሙያ ጋር የተሳሰረችበትን አጋጣሚና የሰራችበትን የህይወት ጉዞ፣ ከድርሰት መጻፍ ጋር የተዋወቀችበትንና ድርሰቶቿ ከጋዜጠንነት ሙያዋ ጋር ያላቸውን ትስስር የሚመረምር ነው፡፡ ለዚህም ሲባል በአንድ በኩል ተጠኚዋን ግለሰብና ቤተሰብ እንዲሁም የቅርብ ጓደኞች ቃለመጠይቅ በማድረግ የህይወት ታሪኳ ክፍል መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የሙያዋንና የድርሰት ስራዎቿን ትስስር ለመመርመርም ከህይወት ታሪኳ ጋር ትስስር ያላቸውን የድርሰት ስራዎች በጥልቅ ምንባብ ተመርጠዋል፡፡የምወድሽ በቀለ ከ1972 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም.ድረስ አስር ረጅም እና አጫጭር ልቦለዶች፣የግጥም መድብሎችና የእውነተኛ ታሪኮች ስብስቦች አሳትማለች፡፡ከሌሎች ደራሲያን መድብሎች ጋር ደግሞ 6 አጫጭር ልቦለዶች ፣ግጥሞችና እውነተኛ ታሪኮች አሏት፡፡በጥናቱ በተመረጡት ልቦለዶች በግል ህይወቷና ከስራ አለም ከነበሯት ገጠመኞቿ ተነስታ በሴቶች ላይ እንደምታተኩር ፤በአፃፃፍ ስልት ደግሞ የወንጀል አፃፃፍን እንድትከተል ተፅእኖ አድርጎባታል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

“የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ” ጥናት በየምወድሽ የድርሰት እና የጋዜጠኝነት ሙያ እንዲሁም በሕይወት ማንነቷ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በጥናቱ የየምወድሽ በቀለ የህይወት ታሪክ ከልጅነት ጀምሮ ጥናቱ እስከተካሄደበት ጊዜ ያላት የግል ሕይወት ቀርቦበታል፡፡የጋዜጠኝነት ፣ የድርሰት እና ተጨማሪ ማህበራዊ አገልግሎቶቿ በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡የምወድሽ በቀለ በግል ከፃፈቻቸው ድርሰቶች በግል ሕይወቷና ከስራ ዓለም ከነበራት ገጠመኞች ጋር የተሳሰሩት “አብዮታዊ ግጥሞች”፣ “ዋጊኖስ የግጥም መድብል”፣“የባከነ ጊዜ አጫጭር ልቦለዶች”፣ “ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች” ረጅም ልቦለድ ድርሰቶቿ ከይዘት አንፃር ተተንትነዋል፡፡

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

“የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ” የሚለው ጥናት በሁለት ማንነቶቿ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡የመጀመሪያው የየምወድሽ ማንነት ጋዜጠኝነቷ ሲሆን የምወድሽ በቀለ የፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና የፕሬስ ሀላፊ በመሆንም ለ 26 ዓመት ሰርታለች። የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር ፕሬዝዳንት በመሆን ያገለገለች ሲሆን በሴቶች መብቶች ላይ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራች ትገኛለች፡፡ደራሲና ጋዜጠኛ የምወድሽ በቀለ በ2007 ዓ.ም ለፐብሊክ ዲፕሎማሲ ተመርጠው ግብፅና ሱዳን ከሄዱ ሴቶች አንዷም ነበረች። ሁለተኛው የየምወድሽ ማንነት ደራሲ መሆንዋ ነው፡፡የምወድሽ ከ 1972 ዓ.ም.እስከ 2014ዓ.ም.ድረስ በልዩ ልዩ የድርሰት ዘውጎች የሚመደቡ መጽሐፎች አሳትማለች፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

1.ልቦለድ፣ ኢ-ልቦለድ፣ ግጥም መጻፍ እና በሁሉም ዘርፎች ደጋግሞ ድርሰቶችን ማድረስ በተለይም በኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን የተለመደ አይደለም፡፡ የምወድሽ በቀለ ይህን ማድረግ ለመቻሏ ያበቃትን ምክንያት ምን እንደሆነ የማወቅ ጉጉት የጥናቱ ቀዳሚ ምክንያት ነው፡፡

2.በልዩልዩ ሙያዊና ማህበራዊ ዘርፎች ተሳትፎዋ ከድርሰቶቿ ጋር አንዳች ግንኙነት ይኖረው ይሆን? የሚለው ጥያቄም ሁለተኛው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 1.3. የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

1. በሕይወት ታሪኳና በድርሰት ስራዋ ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?
2. በተለያዩ የሥነፅሑፍ ዘርፎች ለመጻፍ ያስቻላት ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
3. በድርሰቶቿ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በየምወድሽ በቀለ የህይወት ታሪክና የድርሰት ስራዎች መካከል ያለውን ግንኙነት መፈተሽ ነው፡፡

### የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

1. የየምወድሽ በቀለን የሕይወት ታሪክ ማሳወቅ
2. በተለያዩ የድርሰት የአጻጻፍ አይነቶች ለመጻፍ ያስቻላትን ምክንያት መለየት
3. በድርሰቶቿ እና በግል ህይወቷ መካከል ያለውን ግንኙነት መግለጽ
4. በድርሰቶቿ በተደጋጋሚ የተነሱ ጉዳዮችን መተንተን

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ መጠናቱ በልዩ ልዩ ሙያ የተሰማሩ የተለየ ተሰጥኦ ላላቸው ወገኖች መነቃቃት ይፈጥራል፡፡በሕይወት ታሪክና በድርሰት መካከል ያለ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለሚደረጉ ጥናቶች አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

የየምወድሽ በቀለን የሕይወት ታሪክና ስራዎቿን ለማጥናት የህይወት ታሪክን ከሥነፅሑፋዊ ስራዎች ጋር አዛምዶ ለመተንተን የሚያስችሉ የጥናቱ ዘዴዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡የዚህ ጥናት ዓላማው በየምወድሽ በቀለ እና ስራዎቿ መካከል ያለውን ግንኙነት እና የሕይወት ታሪኳን መመርመር ነው፡፡ የጥናትን አላማ ለማሳካት እና የጥናቱን ግብ ለመምታት የሚፈለገውን መረጃዎች ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን የሚያስችለው ዓይነታዊ (Qualitative ) የጥናት ዘዴ ነው፡፡(ያለው እንዳወቀ ፣2006፣ 410)፡፡ በቃለ

መጠይቅ፣ በጥልቅ ንባብና በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡት መረጃዎች ቁጥራዊ ባለመሆናቸው የጥናት ዘዴው አይነታዊ ሆኗል፡፡

## 1.7. የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት ቀዳማይ ወይም ርቱዕም (Primary) እና ካልአይ ወይም ኢ.ርቱዕም (Secondary) የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህም የመረጃ ምንጮች በቃለመጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻ እና በጥልቅ ንባብ የተገኙ ናቸው፡፡

### 1.7.1. ቃለመጠይቅ (ኢ.ንተርቪ.ው)

ቃለ መጠይቅ ከአንድ ሰው በቀጥታ መረጃ የሚገኝበት ዘዴ ነው፡፡ሆኖም ሁልጊዜ በአንድ ሰው የተሟላ መረጃ ላይገኝ ይችላል፡፡በዚህም ጊዜ ሌሎች ሰዎችን ቃለመጠይቅ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

ፈቃደ አዘዘ ቃለ መጠይቅ ( ኢ.ንተርቪ.ው)ን ሲገልጹ "ስለ አንድ ሰው(a profile ) የምትጽፍ ከሆነ ሊተኮርባቸው ይገባል ያሏቸውን ነጥቦች አስፍረዋል፡፡

1.እርሱን ለማነጋር ፈልገህ ሳታገኘው ቀርተህ ከእርሱ ረዳት ጋር መወያየት ትጀምርና ከዋናው ሰውየ የማታገኘውን ከዚህኛው ታገኝ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከሌሎች ሰዎች የምታገኘውን አታናንቅ፡፡ "እርሱን ብቻ ካላናገርኩ እሞታለሁ!" አትበል፡፡

2.ከተለያዩ ሰዎች የሚገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነታቸውን እያረጋገጡ መጠቀምንም ማሰብ ተገቢ ነው፡፡" ( ፈቃደ አዘዘ ፣1991፣ 96)፡፡

የየምወድሽ በቀለ የህይወት ታሪክና ስራዎቿ ጥናትም ባለታሪኳን በተደጋጋሚ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ግልጽ ያልሆኑ መረጃዎች ሲያጋጥሙ ባለታሪኳን በድጋሚ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃዎቹን ሙሉ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም ስለባለታሪኳ የሚያስፈልጉኝን ተጨማሪ መረጃዎች ከየምወድሽ ጋር ቅርበት ያላቸው የስራ ባልደረቦቿ እና ቤተሰብ ቃለመጠይቅ በማድረግ አግኝቻለሁ፡፡

ከየምወድሽ እና ከደራሲ እንዳለ ጌታ ከበደ (ዶ/ር)፣ ከጋዜጠኛ ተስፋየ ምትኩ፣ ከወይዘሮ መሰረት ነጋ ጋር ስለየምወድሽ በቀለ አስፈላጊ መረጃዎች ለ 6 ወራት በተለያዩ ቀናት በመገናኘት በቃለመጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡

### 1.7.2. ሰነድ ፍተሻ

"ጥናታዊ የመረጃ ምንጮች የሚባሉት በቤተ መፃህፍትና በቤተ መዘክሮች ተሰባስበው የሚገኙት የታተሙና ያልታተሙ መፅሀፎች ፣ ዘገባዎች፣ ጥናቶች፣ መጣጥፎች፣ ሰነዶች፣ ቃለ ጉባኤዎች፣ ደብዳቤዎች፣ ማስታዎሻዎች ወዘተ.ናቸው ፡፡"(አለም እሸቱ ፣1994፣19)፡፡

ይህን ጥናት የተሟላ ለማድረግ የተለያዩ ሰነዶች ላይ ፍተሻ አድርጌአለሁ፡፡ በእርግጥ ስለየምወድሽ የሕይወት ታሪክ እና ስራዎቿ ላይ የተሰሩ እና የተሰነዱ መረጃዎችን በሚገባ ማግኘት ባልችልም በደራሲያን ስራዎች ዙሪያ የተሰሩ መጻህፍት፣ መጽሄቶች፣ እንዲሁም በወመዘክርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተመጽህፍት የሚገኙ ጥናታዊ ጽሁፎች ላይ የሰነድ ፍተሻ አድርጌአለሁ፡፡ በተጨማሪም በግሏ የጻፈቻቸው ደብዳቤዎች፣ ልዩልዩ ሰነዶች፣ፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የሰነድ ፍተሻዎችን በማድረግ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በሰነድ ፍተሻ ያገኘኋቸው መረጃዎች በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከር ረድተውኛል፡፡

### 1.7.3. ጥልቅ ምንባብ

ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃ ከሰበሰብኩባቸው ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ጥልቅ ምንባብ ነው፡፡ ጥናቱን ሙሉ ለማድረግም የምወድሽ በግሏ የጻፈቻቸውን 10 እና ከሌሎች ደራሲያን ጋር በጋራ ያሳተመቻቸው 6 መጻህፍት ላይ ጥልቅ ምንባብ አድርጌአለሁ፡፡

በመጽሀፎቿ ላይ ባደረኩት ተደጋጋሚ እና ጥልቅ ምንባብ በሕይወት ታሪኳና በስራዎቿ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመለየት አስችሎኛል፡፡በተለይም በግል የጻፈቻቸው ድርሰቶቿ መነሻ ገጠመኞች ከግል ሕይወቷ ጋር የተቆራኙ መሆኑን መረጃዎችን እንዳገኝ አግዞኛል፡፡

## 1.8. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱን ለማካሄድ አብዛኛው ወይም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች በቃለመጠይቅ ለመሰብሰብም ባለታሪኳን ጨምሮ ለ አራቱ ዋና መረጃ አቀባዮች በሕይወት ታሪክና ስራዎቿ ዙሪያ የናሙና ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ነው፡፡ በቃለመጠይቁ ወቅት መረጃውን ሙሉ በሙሉ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ መቅረጸ ድምጽ ( Ic Recorder) እንዲሁም ማስታወሻ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 1.9. የመረጃ አሰባሰብ ሂደት እና ትንተና

“በቃለ መጠይቅ አማካኝነት መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ከተሳታፊዎች ጋር ጥሩ መግባባትንና መተማመን መፍጠር ምልልሱ በነጻነትና በጓደኛነት ስሜት እንዲከናወን ከማድረጉም ባሻገር ተፈላጊውን መረጃ በተገቢው መጠን ለማግኘት እንደሚያስችል ይታመናል፡፡”( ፈቃደ አዘዘ ፣ 1991፣96 )፡፡

መረጃዎቹን ከመሰብሰቤ በፊት የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ለማግኘት ከመረጃ አቀባዮቸ ጋር በመገናኘት ስለጥናቱ አላማ በማስተዋወቅ ጀመርኩ፡፡ እንዲሁም የመረጃ አቀባዮች በሚመቻቸው ቀን እና ሰዓት ለመገኘት የሚያስችሉኝን ትውውቆች በማድረግ ወደ ስራ ገባሁ፡፡ ትውውቅ ለማድረግ እና ስለጥናቱ ዓላማ ለማስረዳት 2 ቀናት ወስዶብኛል፡፡ መጋቢት 20 /2015 እና መጋቢት 22 /2015 ከየምወድሽ ጋር በመገናኘት ስለጥናቱ ዓላማ በማስረዳት ነው መረጃ ወደ መሰብሰብ የገባሁት፡፡

የቃለ መጠይቅ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ወራቶችን ፈጅቶብኛል፡፡ መረጃዎቹ ከመጋቢት 20 ቀን 2015 እስከ ነሀሴ 25 ቀን 2015 ዓ.ም. ከመረጃ አቀባዮቸ ጋር በተደጋጋሚ በመገናኘት ተሰብስበዋል፡ ከመረጃ አቀባዮቸ ጋር በተደጋሚ ያደረኩት ቃለ ምልልስ ከተጠናቀቀ በኋላ በመጀመሪያ ቃል በቃል በመስክረብ (Transcribing) (Classifying) የጥናቱ ጥሬ መረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

በመቅረጸ ድምጽ(Ic Recorder) በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ እና ወደ ማስታዎሻ የተገለበጡ ጥሬ መረጃዎች እንደ ይዘታቸው ተከፋፍለዋል፡፡ በየ ይዘታቸው የተከፋፈሉ መረጃዎችም የየምወድሽ በቀለ ውልደትና አስተዳደግ፣ የትምህርት ቤት ሕይወት፣ የስራ አለም፣ የድርሰት ሕይወት፣ የንባብና የመጻፍ ልማድ፣ የግል አመለካከት፣ ሐይማኖት፣ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ እና ማህበራዊ ሕይወት በሚሉ አርእስት ተከፋፍለው ተተንትነዋል፡፡

በቃለ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች በተጨማሪ በጥልቅ ንባብ እና ሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን የድርሰት ስራዎች ትንተና በሚል ርእስ የረጅም ልቦለድ፣አጫጭር ልቦለዶች፣የግጥም ስራዎች ትንተና በሚሉ ንኡስ ርእሶች በየፈርጃቸው በመከፋፈል እና በመተንተን የጥናቱ ማጠቃለያ እና ግኝት ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

## 1.10. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሁለት ጉዳዮች ዙሪያ የተወሰነ ነው፡፡ የመጀመሪያው የየምወድሽ በቀለ የህይወት ታሪክ ከድርሰት ስራዎቿና ከሙያዋ ጋር በተገናኘ የተወሰነ ነው፡፡ሁለተኛው የጥናቱ ወሰን ከድርሰት ስራዎቿ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከ"አብዮታዊ ግጥሞች" መድብል 3 የግጥም ስራዎች፣ ከ"ዋጊኖስ የግጥም መድብል" 3 የግጥም ስራዎች፣ ከ"የባከነ ጊዜ" አጭር ልቦለድ 8 አጫጭር ልቦለዶች እና "ፍቅር የጠማቸው" ረጅም ልቦለድን በመምረጥ በድርሰቶቹ በተነሱ ጉዳዮች (ጭብጦች) ላይ ብቻ ትኩረት ያደርጋል፡፡

ሌሎች የልቦለድ አላባውያን፣ የአጻጻፍ ቴክኒክ፣ የመሳሰሉ የልቦለድ ቅርጾችን ጥናቱ አይመለከትም፡፡ በተጨማሪም ደራሲዋ ከሌሎች ጸሀፍት ጋር በጋራ የሰራቻቸው ስራዎች ውስጥ የተነሱ ዋና ጉዳዮችም በዚህ ጥናት አይዳሰሱም፡፡

## 1.11. የጥናቱ አወቃቀር (አደረጃጀት)

የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክና ስራዎቿ ላይ የተደረገው ጥናት አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ የመጀመሪው ምዕራፍ መግቢያ እና የጥናቱ ማስተዋወቂያ ክፍል ሲሆን የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ ፋይዳ፣ የጥናቱ ዘዴዎች፣የጥናቱ ወሰንና አደረጃጀትን ይዟል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት የተካሄድበት ሲሆን የጽንሰ ሀሳባዊ፣ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራንና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን አካቷል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክ ትንተናን የያዘ ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ አራት ከደራሲዋ የግል ድርሰቶች የጥናቱን ዓላማ መሰረት አድርገው የተመረጡ ድርሰቶች ትንተና ክፍል ሲሆን ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያ እና ግኝት እንዲሁም በጥናቱ መጨረሻ ዋቢ ጽሑፎችና አባሪዎች ቀርበዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

ይህ ምዕራፍ ሶስት ንኡሳን ርዕሶችን ይዟል፡፡ የመጀመሪያው ንዑስ ርእስ የፅንሰ ሀሳብ ቅኝት፣ ሁለተኛው ንድፈ ሀሳብ ቅኝት የተደረገበት ሲሆን ሶስተኛው ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፎች የተቃኘበት ንዑስ ርእስ ነው፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1.የሕይወት ታሪክ

የሕይወት ታሪክ በአንድ ግለሰብ ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን ትረካ ሲሆን ከተራኪው ወይም ከጸሀፊው አንጻር በሁለት ይከፈላል፡፡ የመጀመሪው በባለታሪኩ የሚጻፈው ነው፡፡ይህም ኦቶባዮግራፊ (autobiography) ተብሎ ይጠራል፡፡ሁለተኛው አንጻር ደግሞ የአንድን ግለሰብ የሕይወት ታሪክ በሌላ ወገን የመተረክ ተግባር ሲሆን ይህም የግል የሕይወት ታሪክ (biography) ተብሎ ይጠራል፡፡ (ሳህለስላሴ፣1999፣22-25)፡፡

የሕይወት ታሪክ በራሱ ታሪክ ፈጻሚው ሳይሆን በሌላ ሰው የሚጻፍ መሆኑ ፀሐፊው ታሪኩን የተሟላ ፣ተአማኒና ተነባቢ ለማድረግ ልዩ ልዩ የመረጃ ግብአቶችን ይጠቀማል፡፡

“የህይወት ታሪክ ታሪኩን ከፈፀመው ሰው ውጪ በሆነ ደራሲ የሚጻፍ ተጨባጫዊ (ነባራዊ) ጽሁፍ ሲሆን በህትመት ወይም በፊልም መልክ ተዘጋጅቶ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የነበረበት ዘመን መለያ ከሆኑት ልዩ ልዩ አሻራዎች ጋር እየተዛመዱ ቢብራሩ የሕይወት ታሪኩን ምሉዕ ያደርጉታል ተብሎ ይታመናል፡፡

የሕይወት ታሪክ ሲጻፍ እንደ ፎቶግራፎች ፣ህትመቶች፣ ቃለ-መጠይቆች እና በመሳሰሉት አንደኛና ሁለተኛ መረጃዎች መደገፍ የባለታሪኩን ስብዕና ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ይረዳ ዘንድ ልቦለዳዊ አላባዎችም መጠነኛሚና ይኖራቸዋል፡፡”……(ፋንታሁን፣2003፣208-209)፡፡

የሕይወት ታሪክን ትኩረት በሚመለከት ሰፋ ያለ መረጃም አለ፡፡ በ www.http://keydifferences.com ላይ “difference between biography and autobiography” በሚል ርዕስ የሕይወት ታሪክን ሲገልጽ

> A biography also referred as ‘bio’ is a detailed account of a person’s Life written or produced by another person. It gives an elaborate information regarding the birth place, educational background, work, relationships and demise ofthe person concerned. It presents the subject’s intimate details about life, focusing on the highs and lows and analyzing their whole personality..

የሕይወት ታሪክ በባለታኩ ሳይሆን በሌላ አካል የሚዘጋጅ ሲሆን ስለባለታሪኩ የትውልድቦታ፣ የትምህርት ዳራ፣ ሥራ፣ ማህበራዊ ግንኙነት ወ.ዘ.ተ. የሚቀርብበት ነው፡፡ የሕይወት ታሪክ ስለባለታሪኩ በዝርዝርና በጥልቀት መረጃ የሚቀርብበት ተግባር እንደሆነ ከጥቅሱ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህንኑ ሀሳብ (Liers, Frederick.2005.) እንደሚከተለው ያብራሩታል፡፡

> Authors of biological narratives typically choose people or characters that have personal significance to them.The point or direction of the narrative outlines the personal impact the subject has in the author’s life. In a biographical narrative, the author highlights certain details to develop an in-depth impression of the person. Sensory details replace direct explanations. The author creates an emotional impact with the narrative using specific and highly descriptive words and phrases.

የሕይወት ታሪክ የባለታሪኩን የግል ሥነሕይወታዊ መረጃዎችን እና አካላዊ መገለጫዎችን እንዲሁም የድርጊት ዝርዝሮችን ሁሉ የምናሳይበት ወይም የምናቀርብበት ነው፡፡የሕይወት ታሪክ ጸሀፊውም በሚጠቅሙ እና በባለታሪኩ ወሳኝ እና ጠቃሚ የሕይወት መስመሮች ላይ ትኩረት በማድረግ በጥልቀት የሚቀርብበት እንደሆነ ከላይ የቀረበው ሀሳብ ያስረዳል፡፡ የሕይወት ታሪክ ትረካ ገላጭ የሆኑ ቃላትና ሀረጋትን በመጠቀምም በሚቀርበው የሕይወት

ታሪክ ላይ ስሜታዊ ተፅእኖ መፍጠር የሚቻልበትም ነው፡፡ የሕይወት ታሪክ አዘገጃጀት እንደ አዘጋጁ አላማ ሰፊና ውስን ሊሆን እንደሚችልም ይገለጻል፡፡

> The true story of someone's life or it may tell about an important part of aperson's life. An account of a person's entire life is almost always told in chronological order (in the time order events occurred).It contains variety of important information about the person's life. It often how the person feels and thinks about things.(Robin Fleming.2009,102).

በጥቅሱ እንደተገለጸው የሕይወት ታሪክ የባለታሪኩ ሙሉ የሕይወት ታሪኩ ወይም ከሕይወት ታሪኩ የተወሰነውና ለትረካው ተፈላጊ የሆነው ክፍል ሊሆን ይችላል፡፡ የሕይወት ታሪክ አጻጻፍም የድርጊቶች ተከታታይነትን በጠበቀ መልኩ የሚቀርብም ነው፡፡ "የሕይወት ታሪክ ዝግጅት እጅግ አድካሚ ነው፡፡ አድካሚ የሚሆነውም ግለሰቡን የሚመለከቱ መረጃዎችን ከተለያየ አቅጣጫ ማሰባሰብ ስለሚጠይቅ ነው፡፡"( አለም እሸቱ፣ 1997፣86-87፣ ፈቃደ አዘዘ ፣1999)፡፡

## 2.1.2. የሕይወት ታሪክና ሥነፅሑፍ

ሥነፅሑፍ ወጥ የሆነ ብያኔ ባይሰጠውም የሰው ልጅ ሀሳቡን በተለያየ መንገድ የሚገልጽበት ዘዴ መሆኑ ሁሉንም ብያኔዎች የሚያስማማ እንደሆነ ዘሪሁን አስፋው በሥነፅሁፍ መሰረታዊያን መፅሀፋቸው ላይ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ሥነፅሑፍ ከተለያዩ መስኮች ጋርም ቁርኝቱ የጠበቀ ነው፡፡

"የህይወት ታሪኮች ፣የህወት ታሪኮች፣የግል ማስታዎሻዎች፣ የጉዞ ትውስቶች፣ ወጎችና የፍልስፍና ስራዎች ከሥነፅሑፍ ይቆጠሩ እንደነበር እንገነዘባለን ይላሉ፡፡ እነዚህ ሥነፅሑፍ ለመባል የበቁት ባማረ ቋንቋ በተባ የሀሳብ አገላለጽ ተቀነባብረው በመጻፋቸው ነው ፡፡" (ዘሪሁን አስፋው ፣1992፣2)፡፡

በተለይም የደራሲ የሕይወት ታሪክ ሲሆን ከሥነፅሑፍ ጋር የበለጠ የተቆራኘ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ደራሲ ለድርሰቱ መነሻ የሚያደርገው በራሱ ወይም በዙሪያው ከሚገኙ፣ ከገጠሙት የሕይወት መልኮች መነሻነት በመሆኑ ነው፡፡

ደራሲ ገጠመኙን እና በሕይወቱ የተረዳውን ሁሉ ወደ ድርሰት ይቀይረዋል ወይም ይጽፈዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከሀገራችን ደራሲዎች ጀምሮ እስከ ውጭ ሀገር ከያኒያን ድረስ የሚጽፏቸው የድርሰት ስራዎች በራሳቸው ሕይወት ገጠመኞች ወይም ከሚኖሩበት አካባቢ ነባራዊ ሁኔታዎች እና ገጠመኞች መነሻነት የተቀዱ እንደሚኖሩባቸው ይታመናል፡፡

ለምሳሌ የስብሀት ገብረእግዚአብሄር "ሌቱም አይነጋልኝ" እና "ትኩሳት" እንደወረደ የተጻፉ እና የደራሲውን ትክክለኛ ገጠመኞች የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ደራሲውም ሁለቱን ድርሰቶች እንደወረደ የተጻፉ መሆናቸውን በመጻህፍቱ ላይ አስፍረዋል፡፡ እንዲሁም ደራሲ ዘነበ ወላ የጻፈው "ማስታወሻ" ስለ ስብሐት ገብረእግዚአብሄር ትክክለኛ ሕይወት የሚያሳይ ነው፡፡

በደራሲ ዘነበ ወላ ማስታወሻ (የስብሐት የሕይወት ታሪክ) ከመጽሀፉ ክፍል አንድ ቀድሞ የተጻፈው የባለታሪኩ የስብሐት ገብረእግዚአብሄር የእጅ ጽሁፍ ይህንኑ ያስረዳል፡፡(ዘነበወላ፣ማስታወሻ፣2009)፡፡ እንደወረደ የተጻፉት እነዚህ ስራዎች የደራሲዎቹ ገጠመኞች ለድርሰቶቻቸው መነሻ ለመሆናቸው ማሳያ ናቸው፡፡

### 2.1.3. የሕይወት ታሪክ የአጻጻፍ መንገድ

የህይወት ታሪክ ጥናት የራሱ ሞዴሎች አሉት፡፡ ከእነዚህ ሞዴሎች መካከል ፈቃደ አዘዘ ለፒ.ኤች.ዲ ተማሪዎች ያዘጋጁትን ቴምፕሌት በሞዴልነት ተወስዷል፡፡ የፈቃደ አዘዘ ቴምፕሌት ለቃለመጠይቅ መነሻ የሆኑ 12 ማጠንጠኛ ርእሶች ሲኖሩት በስሩ 30 የሚሆኑ ንኡሳን ርእሶችን ያካተተ ነው፡፡

የባለታሪኩ የትውልድ ሐረግ፣ የቤተሰብ ፣ የባህላዊ ስነምግባር፣ የአካባቢ (environment) የህይወት ታሪክ ፣ የግል የኢኮኖሚ የሕይወት ታሪክ፣ የፍቅር፣ ከአስተዳደርና ከፍትሕ ጋር የተያያዘ የሕይወት ታሪክ፣ የማንነት(identity)፣ ከሀገር ጉዳይ ጋር የተያያዘ፣ ከስርአተ ጾታ ጋር የተያያዘ ፣ ከልጆች አስተዳደግና አያያዝ ጋር የተያያዘ እና የሙያ የሕይወት ታሪክ የሚሉት 12ቱ ማጠንጠኛ ርእሶች ናቸው፡፡( ፈቃደ አዘዘ ፣1999፣72-75)፡፡

የሕይወት ታሪኩ በሙሉ ተቀድቶ ከተደራጀ በኋላ በመረጃ አቀባዩ ላይ ተመስርቶ ፎክለረኛው /የሕይወት ታሪክ ተመራማሪው በሚያዘጋጀው ጽሁፍ ውስጥ ስርአት ባለው መልክ በየቦታው የተሰራጨትን መረጃዎች በተፈለገው መልክ ማደራጀት ያሻል፡፡እነዚህን ክፍፍሎች የምንፈጥርና የምንቀርጸው ስለሕይወት የምናስበውን እና የምንመረምረውን መልክ ለመስጠት በምናደርገው ጥረት ነው፡፡ ቅደም ተከተል ሳይዝ የቀረበውን አንዳንዴም የተዝረከረከውን ሰብስቦና አደራጅቶ መልክ በማስያዝ ሃሳቦችን ፣ድርጊቶችን ወዘተ. ቁልጭ አድርጎ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡ ( ፈቃደ አዘዘ፣1999፣70-72) ፡፡

የምወድሽን የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ መረጃዎችን በአግባቡ እና በቀላሉ ለመሰብሰብና ታሪኩን በቅደም ተከተል ለመጻፍ ቴምፕሌቱ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል፡፡

## 2.2. ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት

የየምወድሽ በቀለን የሕይወት ታሪክና ስራዎቿን ለማጥናት የህይወት ታሪክን ከሥነፅሑፋዊ ስራዎች ጋር አዛምዶ ለመተንተን የሚያስችሉ ሁለት የሥነፅሑፍ ንድፈ ሀሳቦች ተመርጠዋል፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ንድፈ ሀሳባቦች ቅኝት እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1. ግለ ተረክ ንድፈ ሀሳብ (Biographical Narrative Theory)

እያንዳንዱ የሰው ልጅ የራሱ የሆነ ታሪክ አለው፡፡ ስለሌሎች ማለትም በቅርብ ከሚያውቃቸው የቅርብ ቤተሰቦቹ ጀምሮ ስለተለያዩ የሩቅ ሰዎችም የሚያውቀው ታሪክ ይኖረዋል፡፡ ሐረገወይን ሽዋረጋ በ2004 ዓ.ም "በባሕርዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የህይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ" በሚል ርእስ ባደረገችው ጥናት ስለ ግለተረክ ንድፈ ሀሳብ እንዲህ ስትል ጽፋለች፡፡

"የሰው ልጆች በአለም ውስጥ ሲኖሩ ያካበቱት ልምድ እና በኑሮአቸው ወቅት ከሌሎች ሰዎች ጋር የነበራቸው ተራክቦ አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ ወይም ትርጉም ያለው ሆኖ ያገኙታል፡፡ ስለዚህ ይህን የህይወት ልምድ (ተሞክሮ) ለሌሎች ሰዎች ይተርኩታል፡፡ የግል የሕይወት ታሪክና ተሞክሮን ለሌሎች ሰዎች ለመተረክ ባዮግራፊ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ነው ትላለች፡፡"

ከዚሁ ጋር አያይዛ Labov እና Waletzkyን በመጥቀስ ተረክ አንዱ የህይወት ልምድን የመግለጫ ዘዴ ነው" በማለት ገልጻለች፡፡ ተረክ ማለት እውነታን ወይም ልቦለዳዊ ሁነትን መንገር ማለት ነው፡፡ ወይም እንደገና የተራኪውን ትረካ መዘርዘር መተረክ ማለት ነው፡፡ ተረክ አጫጭር ሁነቶችን፣ ረጅም ታሪኮችን፣ የህይወት ታሪኮችን፣ የግል ማስታወሻዎችን ወዘተ. የሚያካትት ሲሆን ነገሮችን አዛምዶ የማጥናት ባህሪ ያለው ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡(ሐረገወይን ሸዋረጋ፣2004፣16 )፡፡

## 2.2.2. ሥነማሕበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ (Sociological Theory )

ሥነማሕበረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ( Sociological Theory) በግለሰብ እና ማሕበራዊ እውነታ መካከል ያለውን ግንኙነት ለመፈተሽ የሚያስችል ስነዘዴ ነው፡፡ "ጥልቅና ዋነኛ ተብለው ከሚጠቀሱት 10 የስነጽሁፍ  የጥናት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ስነ ማህረሰባዊ ንድፈ ሐሳብ (Sociological Approach) ነው፡፡" (X.J.Kennedy,2005.)፡፡ሥነማህበረሰባዊ ንድፈ ሀሳብ ሥነፅሑፋዊ ስራዎችን ከማህበረሰቡ እና ከደራሲው ህይወት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማሳየትም ያስችላል፡፡

"ይህ ንድፈ ሐሳብ የከያኒውንና የማህበረሰቡን ግንኙነት በመቃኘት ከያኒው የሚኖርበትን ማህበረሰባዊ መገለጫዎች በመመርመር ከሥነፅሑፍ ጋር ያላቸውን ቁርኝትና ውክልና የሚፈትሽም ነው፡፡ እንዲሁም የማህበረሰቡ መገለጫ የሆነውን ሥነፅሑፍ ከተጻፈበት ፖለቲካዊ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ አውድ አንጻር የሚቃኝ የጥናት ዘዴ ነው፡፡"(X.J Kennedy,2005.)፡፡ በሌላ በኩል ሥነማሕበረሰባዊ ንድፈ ሀሳብን ማሕበራዊ ሂስ በሚል የሚያብራሩት ዘሪሁን አስፋውም ተከታዩን ሀሳብ አስፍረዋል፡፡

> ሥነማሕበረሰባዊ ሂስ በኪነጥበብ እና ማህበረሰብ መካከል ያለው ግንኙነት ለማሳየት ለመመርመር የሚያስችል ነው፡፡ ደራሲው ከማህበረሰቡ የተገኘና ማህበረሰቡ የቀረጸው እናም የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጽታዎች በስራው ውስጥ የሚያንጸባርቅ መሆኑን ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ ደራሲው የማበረሰቡ አባል በመሆኑ በኖረበት ዘመን የታዩት የተለያዩ ማሕበረሰባዊ ክንዋኔዎችና እንቅስቃሴዎች ይነኩታል፡፡ የተከሰቱ መጥፎም ሆኑ ጥሩ ነገሮች በሆነው መንገድ ይመለከቱታል፡፡ በሥነፅሁፋዊ ስራውም ላይ ተጽእኖአቸው መታየቱ አይቀርም፡፡ ከዘመኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች ውጭ ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ በማህበረሰቡ

ውስጥ የሚደረጉ የእውቀት፣ የቴክኖሎጅና የኪነጥበብ እንቅስቃሴዎች ይመለከቱታል፡፡ በአጠቃላይ ደራሲው ያለበት ማሕበረሰብ እና ዘመን ታሪክ አሻራውን በስራው ላይ ማሳየቱ አይቀርም፡፡ (ዘሪሁን አስፋው፣1992፣ 365)፡፡

ከጥቅሶቹ እንደምንረዳው በደራሲና በሕይወት ታሪክ መካከል ያለን ቁርኝት እንዲሁም ደራሲው ደራሲ ለመሆን መነሻ የሆኑትን ማሕበረሰባዊ ገጠመኞች ለማጥናት ሥነማሕበረሰባዊ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም ለጥናቴ ተስማሚ የሚሆነውና ማህበረሰባዊ ጉዳዮችን ለማሳየት የሚያመቸውን ሥነማሕበረሰባዊ የጥናት ዘዴ (Sociological Approach) ተጠቅሜአለሁ፡፡

ከላይ የቀረቡት ብያኔዎች እንደሚያስረዱት ባዮግራፊ (Biographical Narrative Theory) እና ሥነማሕበረሰባዊ (Sociolojical Approach) ንድፈ ሀሳቦች የግል የሕይወት ታሪክን ለመተንተን እና ለማብራራት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም የሕይወት ታሪክን ከሥነፅሑፍ ስራዎች ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ለመመርመርም ያስችላሉ፡፡ እኔም የየምወድሽ በቀለን የሕይወት ታሪክና ስራዎቿን ለመተንተን እና ለማብራራት እንዲሁም በግል ህይወቷ እና ስራዎቿ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ሁለቱን ንድፈ ሀሳቦች መርጫለሁ፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ይህ ክፍል በሕይወት ታሪክ ላይ ከዚህ በፊት የተጠኑ ጥናቶች የሚዳሰሱበት ነው፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ ክፍል፣ በአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍ እና ፎክሎር፣ በውጭ ቋንቋና ሥነፅሑፍ ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ፣ ለሁለተኛ ድግሪ እና ሶስተኛ ድግሪ (ዲሰርቴሽን) ማሟያነት የተጠኑ ጥናቶች አንብቤአለሁ፡፡ በሶስቱ የትምህርት ክፍሎች ከ 1970ዎቹ ጀምሮ እስከ 2010 ዓ.ም. ድረስ በሕይወት ታሪክ ላይ የተሰሩ አርባ የጥናት ወረቀቶች አግኝቻለሁ፡፡

የእኔ ጥናት በደራሲ ጎራ የሚካተት በመሆኑ ንባብ ካደረኩባቸው ጥናቶች በደራሲያን የሕይወት ታሪክና ስራዎች ላይ ያተኮሩ 3 ጥናቶች ተመርጠዋል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት በሕይወት ታሪክ ላይ

የተደረጉ 2 ጥናቶች ፤በዚሁ ትምሕርት ክፍል ለመጀመሪያ ድግሪ ማሚያነት የተሰራ 1 ጥናት ቀጥሎ ቅኝት የተደረገባቸው ናቸው፡፡

### 2.3.1. የሁለተኛ ድግሪ ጥናቶች

ኤልሳቤጥ መኩሪያ 2009 ኢ.ም. “የደራሲ ይልማ ሃብተየስ እጅጌ የሕይወት ታሪክ” በሚል ርእስ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያነት ያቀረበችው ጥናት ነው፡፡ ኤልሳቤጥ የደራሲው የሕይወት ታሪክን በስፋት በመዳሰስ አቅርባለች፡፡ ደራሲው የግል የሕይወት ጉዞውን በስፋት ባቀረበችበት ጥናት የሰራቸው የሥነፅሑፍ ስራዎችን በቁጥር ጠቅሳለች፡፡

የኤልሳቤጥ ጥናት አላማ ደራሲ ይልማ በወንጀል ክትትል ጽሁፍ ጸሀፊ በመሆኑ እና በአብዛኛው በዚህ ዘመን የማይታወቅ በመሆኑ የሕይወት ታሪኩን መሰነድ የሚል ነው፡፡
ኤልሳቤጥ የደራሲውን የሕይወት ታሪክ ብቻ ነው ያጠናችው፤ ስራዎቹን በቁጥር ከመጥቀስ ውጭ በድርሰቶቹ የተነሱ ዋና ጉዳዮችን አልዳሰሰችም፡፡ አጥኝዋ ጥናቱን ስታካሂድ የጥናቱ ባለታሪክ መረጃዎቹን ሰብስባ ሳትጨርስ ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው የምትፈልገውን መረጃ ለማግኘት ተቸግራ እንደነበርም ገልጻለች፡፡

የደራሲውን መልከ ብዙ ችሎታዎች እና በደራሲነት በተለይም ደግሞ በወንጀል ታሪኮች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ልቦለዶችን ለመጻፍ መነሻ የሆኑ ምክንያቶችን ፈትሻለች፡፡ ደራሲው በትምሕርት ቤት ሕይወቱ ከጓደኞቹ ጋር ይጻጻፍ የነበረው ደብዳቤ የፅሁፍ ክህሎቱን እንዳዳበረለት ገልጻለች፡፡ደራሲው ድርሰቶች እና የድርሰት ገጠመኞቹ ወይም ልቦለድ ለመጻፍ መነሻ የሆኑት ሀሳቦች ይሰራው ከነበረው ስራ ጋር የማገይናኝ መሆኑን ማረጋገጥም ችላለች፡፡

ደራሲ ይልማ ሀብተየስ የላቭራቶሪ ቴክኒሺያን መሆኑ ልቦለድ ከመጻፍ እንዳላስተጓጎለው በጥናቷ አሳይታለች፡፡ የኤልሳቤጥ ጥናት ከእኔ ጥናት ይለያል፡፡ የመጀመሪያው ተጠኚው ግለሰቦች የተለያዩ መሆናቸው ነው፡፡ ሁለተኛው መለያ የኤልሳቤጥ ጥናት በባለታሪኩ (በይልማ ሃብተየስ) ላይ የተወሰነ ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ በተጠኝዋ (ከየምወድሽ) የሕይወት ታሪክ በተጨማሪ የድርሰት ስራዎቿን በመጨመሩ ነው፡፡

ማሚ ግርማ በ 2007 ዓ.ም. "የአርቲስት ጌታቸው ደባልቄ የሕይወት ግለታሪክና ኪናዊ ስራዎቻቸው" በሚል ርእስ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያነት ጥናት አቅርባለች፡፡ ማሚ ግርማ በአርቲስት ጌታቸው ደባልቄ የሕይወት ታሪክ ላይ ያቀረበችው ጥናት በስድስት ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡

አጥኝዋ የአርቲስት ጌታቸው ደባልቄን የሕይወት ታሪክ በዘመን ከፋፍላም አቅርባለች፡፡ ከውልደት እስከ ትዳር፣ ከተማሪነት እስከ ሙያ ቅጥርነት ያሉትን የሕይወቱን ታሪኮች በመከፋፈል ቃኝታለች፡፡ በተጨማሪም የአርቲስት ጌታቸው ደባልቄ በዘመነ ቀዳማዊ ሀይለስላሴ፣ በደርግ እና በዘመነ ኢህአዴግ የሕይወት መልካቸው ምን እንደነበር በጥናቷ ቃኝታለች፡፡

የማሚ ግርማ ጥናት የባለታሪኩን የሕይወት ታሪክ ከራሱ ከባለታሪኩ እና ባለታሪኩን ከሚያውቁት ሰዎች መረጃዎችን በመሰብሰብ የተነተነ እና መጨረሻም ማጠቃለያ እና ይሁንታ ላይ የደረሰ መሆኑ የጥናቱን ዋና አላማ ያሳካ ነው፡፡ የማሚ ጥናት በሕይወት ታሪክ ላይ የተደረገ መሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁንና የእኔ ጥናት ተጠኝዋን ከድርሰት ስራዎቿ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና በድርሰቶቹ የተነሱ ጉልህ ጉዳዮችን የሚመለከት በመሆኑ ደግሞ ይለያል፡፡

## 2.3.2. የመጀመሪያ ድግሪ ጥናት

አንዱአለም ሽመልስ በ 1998 ዓ.ም. ለአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከየምወድሽ በቀለ ስራዎች ውስጥ "የቋንቋ አጠቃቀም እና የአተራረክ ቴክኒክ "በእብዱ በለጠች ኖቬላ"ልቦለድ በሚል ርእስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሚያነት (ዲ.ማ.ጽ.) ጥናት አቅርቧል፡፡ የአንዱአለም ሽመልስ ጥናት በ"እብዱ በለጠች (ኖቬላ)" የቋንቋ አጠቃቀም እና የአተራረክ ቴክኒክን መመርመር ዋና አላማ ያደረገ ነው፡፡

ጥናቱ በመረጃ ትንተና ክፍሉም የአተራረክ ቴክኒክ የሚባሉት ምልሰት፣ ገለፃ፣ ንግር እና ምልሰት በስፋት የተዳሰሰበት ነው፡፡ እንዲሁም በዚሁ ክፍል የቋንቋ አጠቃቀም ከቃላት ምርጫ እና ከዘይቤ አጠቃቀም አንጻር የተቃኘበት ነው፡፡

የአንዱአለም ጥናት በየምወድሽ በቀለ ልቦለድ በአንዱ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ይሁንና የአንዱአለም ጥናት  በየምወድሽ በቀለ "እብዱ በለጠች ኖቬላ" ልቦለድ የቋንቋ አጠቃቀምና የአተራረክ ቴክኒክ የተወሰነ በመሆኑ ከእኔ በሕይወት ታሪኳና የድርሰቶቿ ይዘት ላይ ካተኮረው ከዚሕ ጥናት ይለያል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## የየምወድሽ በቀለ የሕይወት ታሪክ

በዚህ ምእራፍ የየምወድሽ በቀለ ውልደትና አስተዳደግ፣ የትምህርት ቤት ሕይወት፣ የስራ አለም፣ የድርሰት ሕይወት፣ የንባብና የመጻፍ ልማድ፣ የግል አመለካከት፣ ሐይማኖት፣ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ እና ማህበራዊ ሕይወት ቀርበውበታል፡፡

### 3.1. ልጅነትና የትምህርት ዘመን

#### 3.1.1. ልጅነት

በተለያዩ የሕይወት አጋጣሚዎች ከሰሜን ሸዋ ይፋት ወደ አዲስ የመጡት ባሻ በቀለ ወልደገብርኤል ከወይዘሮ ወርቅነሽ ወልደማርያም ጋር ትዳር መስርተው መኖር የጀመሩት ጎላ ሚካኤል እና ተክለሀይማት በሚባሉት ሁለት ደብሮች መካከል በሚገኘው ተክለሀይማኖት መንደር ውስጥ ነበር፡፡

የምወድሽ በቀለ በወቅቱ የፖሊስ ሰራዊት አባል ከነበሩት ባሻ በቀለ ወልደገብርኤል እና በጠጅ ንግድ ላይ ከተሰማሩት ወይዘሮ ወርቅነሽ ወልደማርያም በ 1952 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወለደች፡፡

> አንድ ልጅ ነኝ እኔ ለቤተሰቦቸ ወንድም እህት የለኝም በጣም ሞልቃቃ ከሚባሉት ወገን ሆኘ ነው ያደኩት እጅግ በጣም ደግ ደግ የደጎች ደግ የነበረች እናት ነበረችኝ በስስት ነው ያደኩት፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ሚያዚያ2፣ቃ.መ.)፡፡

እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስም በ 1959 ዓ.ም. በ 7 አመቷ በተወለደችበት አካባቢ ጎላ ሚካኤል ውስጥ የኔታ ቁሩ በሚባሉ የቤተክህነት አባት አመት ለማይሞላ ጊዜ ፊደል ቆጥራለች፡፡ ልጅነቷን እንደ እድሜ እኩዮቿ እየተጫወተች ብታድግም በቤት ውስጥ ግን ብቸኛ ልጅ በመሆኗ ከእናት እና አባቷ ጋር ብቻ ነው ያደገችው፡፡

### 3.1.2. የትምሕርት ቤት ሕይወት

የምወድሽ ለወራቶች ፊደል ከቆጠረች በኋላ ዘጠኝ አመት ሲሞላት ቀጥታ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት ገባች፡፡ በወቅቱ የቅድመ መደበኛ (ኬጅ) ትምህርት ቤት ባለመኖሩ የግል ትምህርት ቤት በሆነው የአፍሪካ አንድነት ትምህርት ቤት የአንደኛ ክፍል ትምሕርቷን ጀመረች፡፡በዚሁ ትምህርት ቤትም እስከ ስድስተኛ ክፍል ከ1961 እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ተምራለች፡፡

የምወድሽ በወቅቱ በነበረው የትምህርት ካሪኩለም (ስርአት) ይሰጥ የነበረውን የስድስተኛ ክፍል ሚኒስትሪ ካለፈች በኋላ ከ1967 እስከ 1968 ዓ.ም. ሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍልን ወሰን ሰገድ ትምሕርት ቤት ተምራለች፡፡ ከዘጠነኛ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ልኡል መኮንን በአሁኑ አዲስ ከተማ ትምሕርት ቤት ከ1969 እስከ 1972 ዓ.ም. ድረስ ተምራለች፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን እንዳጠናቀቀች ቀጣይ የህይወት መስመርን መሰረት እንድትይዝ ያደረጋት የትምህርት ጅማሮ ገጠማት፡፡ የምወድሽ ከ 12ኛ ክፍል በኋላ ነጻ የትምህርት እድል አገኘች፡፡ በ 1972 ዓ.ም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የታተመው “አብዮታዊ ግጥሞች” የተሰኘው የግጥም መጽሀፏ የትምህርት እድሏ መነሻ ሆነ፡፡ መጽሀፏን ለመሸጥ ወደ ፌደራል ፖሊስ የሄደችው የምወድሽ በዛው መስሪያቤት የጋዜጠኝነት የስራ ልምምድ እንድታደርግ መንገድ ከፈተላት ፡፡

የስራ ልምምድ እያረገች ባለችበት ተቋም የትምህርት እድል አገኘች፡፡ በፌደራል ፖሊስ ልምምድ ለሚያደርጉ የማስታወቂያ ሚኒስቴር በሰጠው የትምህርት እድል የምወድሽ የጋዜጠኝነት ትምህርትን በነጻ ለመከታተል ተመርጣ “ዋርነር ላበር” በተሰኘ የጀርመን ኢንስቲትዩት የጋዜጠኝነት ስልጠና ለ 6 ወር ወስዳለች፡፡ ከጀርመን በመጡ ባለሙያዎች ለ6 ወር የወሰደችው ስልጠናም ወደምትመኘው ሙያ እንድትቀላቀል መንገድ የከፈተላ መሆኑንም ትናገራለች፡፡

> የአስራ ሁለተኛ ክፍል ውጤት ተያይዞ ስልጠና ገባሁ እሚገርም ነገር ነው ያው የፍላጎቴን መንገድ የገባሁበት ማለት ነው እዛ ስድስት ወር በደንብ መደበኛ ስልጠና ሰለጠንኩ ከሁሉም ክልል የተውጣጡ ወደ ስልሳ የሚሆኑ ጋዜጠኞች በሬዲዮ በፕሬስ ሰለጠንን በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረ፡፡ ከእውቅና አንጋፋ ጋዜጠኞች

ክፍሌ ሙላት፣ማርታ ኩምሳ ፣ብዙ ወንድማገኝ ከነሱ ጋር ነው የተማርኩት፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ሚያዚያ2፣ቃ.መ.)፡፡

ከ 1973 ዓ.ም. ጀምሮ የ ስድስት ወር የጋዜጠኝነት ስልጠና ከወሰደች በኋላ በወቅቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጊቢ ይገኙ በነበሩት ልኡል በእደ ማርያም ትምህርት ቤት እና አሚሪካን ሚሽን ትምሕርት ቤቶች ለ 2 ዓመት በጋዜጠኝነት ዲፕሎማ ተምራለች፡፡ የጋዜጠኝነት ስራን በስድስት ወር ስልጠና ቀጥሎም በዲፕሎማ ባገኘችው ትምህርት የጀመረችው የምወድሽ በ1980 ዓ.ም."በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ" በተልእኮ በርቀት ተምራ በ"ፐብሊክ ሪሌሽን ኤንድ ኮሚኒኬሽን" የመጀመሪያ ድግሪዋን አግኝታለች፡፡

በተጨማሪም የስነጽሁፍ ትምህርቷን በኔዘርላንድ ኤምባሲ ባገኘችው እድል በአዲስ አበባ "በሮያል ኮሌጅ" ከ 25 ሴት ደራሲያን ጋር ለ አስር ወራት ተምራለች፡፡ "አሁንም ትምህርት መማሬን አላቆምም" የምትለው የምወድሽ በቀለ በ"ሊደርሽፕ እና ፕሮጀክት ማኔጅመንት" ሁለተኛ ድግሪዋን በ2015 ዓ.ም. አግኝታለች፡፡

## 3.2. የስራ ዓለም

### 3.2.1. ጋዜጠኝነት

የምወድሽ ለ ስድስት ወር የጋዜጠኝነት ትምህርት ስልጠና ከወሰደች በኋላ በ 1974 ዓ.ም መጨረሻ በፖሊስ ሚዲያ "ፖሊስና ርምጃው" ጋዜጣ ስራ ጀመረች፡፡ በሁለት ሳምንት 126 ሺ ኮፒ ድረስ በሚሸጠው ፖሊስና ርምጃው ጋዜጣም በጀማሪ ሪፖርተርነት በ 230 ብር ደመወዝ ተቀጠረች፡፡



በ1975 ዓ.ም.በፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ የምወድሽ ከስራ ባልደረቦቿ ጋር በስራ ላይ፡፡

የጋዜጠኝነት ሙያ ፍላጎቱ ያደረባት አባቷ የፖሊስና ርምጃው ጋዜጣን በየ አስራ አምስት ቀኑ እያመጡ እንድታነብ ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ትናራለች፡፡ እያነበበች ባደገችው ጋዜጣ ብሆን ብላ የምትመኘውን የጋዜጠኝነት ስራ ጀመረች፡፡ ወደ ስራ አለም ከመግባቷ በፊት በጋዜጣው ይወጡ የነበሩ የወንጀል ታሪኮችን እንደምታነብ ታስታውሳለች፡፡

> አባቴ የሚያመጣልኝን የፖሊስ ጋዜጣ አነባለሁ የተፈጸሙ አስቂኝ እና አሳዛኝ ወንጀሎች በጋዜጣው ይወጡ ነበር ለምሳሌ “መልኩን ጠልቶ እራሱን ገደለ”፣“የሽሮ ሌባው ታሰረ” የሚሉ ርዕሱ እራሱ ያስቀኛል ……….በዛው ልክ በጣም አሳዛኝ ወንጀሎችም በጋዜጣው ይወጡ ነበረ አሁንም በፖሊስ ላይብራሪ ውስጥ አሉ፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ሚያዚያ 9፣ቃ.መ.)፡፡

በ"ፖሊስና ርምጃው"ጋዜጣ በጀማሪ ሪፖርተርነት ከ1974 ዓ.ም እስከ 1979 ዓ.ም. ሰርታለች፡፡በአዘጋጅነት ከ1980 ዓ.ም.እስከ 1985ዓ.ም. እንዲሁም ከ1986 እስከ 1992 ዓ.ም. ድረስ በዋና አዘጋጅነት አገልግላለች፡፡የምወድሽ በቀለ ከ1993 ዓ.ም. እስከ 2001 ዓ.ም ድረስ ደግሞ የጋዜጣው የፕሬስ ሀላፊ ሆና በመስራት በተቋሙ ለ 26 አመታት አገልግላለች፡፡

> ጥሩ ጊዜ ስለነበረ በዚያች በአጭር ኮርስ ዜና መስራት እየለመድኩ መጣሁ ማለት ነው ፖሊስ እና እርምጃው ጋዜጣ ውስጥ 26 አመት ነው የሰራሁት ከጀማሪ ሪፖርተርነት የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ሆኛለሁ ከዛን በሏላ የፕሬስ ሀላፊ ሆኛለሁ፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ሚያዚያ 9፣ ቃ.መ.)፡፡

በዚሁ ጋዜጣ 26 አመታትን ያገለገለችው የምወድሽ ሲቪል መርማሪ ጋዜጠኛ በመሆን የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መነሻ በማድረግ የምርመራ ዘገባዎችን ሰርታለች፡፡ የፖሊስ ስልጠናን ባትወስድም የፖሊስ ስራ የሚጠይቀውን ህግና ስርአትን ጠንቅቃ እንደምታውቅ ትናራለች፡፡ የተፈጸሙ አሰቃቂ ወንጀሎችን፣ ጨለማ ተገን በማድረግ የሚፈጸሙ የአስገድዶ መድፈርና የነፍስ ማጥፋት ወንጀሎችን ከመነሻቸው በማነፍነፍ ድርጊቱ በተፈጸመበት ቦታም በመገኘት በወንጀሎቹ ላይ ምርመራ በማድረግ የሚያስከትሉትን ኢኮኖሚዊ፣ ማህበራዊ፣ ሰብአዊ፣ስነልቦናዊ ጉዳቶችን በማሳየት ሰርታለች፡፡

የጋዜጣው አምድ አዘጋጅ በነበረችበት ጊዜም በ 15 ቀን ውስጥ 3 አምድ ታዘጋጅ ነበር፡፡"የጋራ ችግሮች እንዴት ይቃለላሉ" አምድ ፣"ምን አስተዋሉ" አምድ ላይ ደግሞ "ህግ አስከባሪዎች ህግ ጥሰው ይሆን"? በሚል ርእስ ፖሊሶችን የሚገመግም የምርመራ ዘገባ ሰርታለች፡፡በዚህ አምድ በጣም ብዙ ጊዜ የተገመገምችበት እና የፖሊሶችን ችግር ነቀሶ የማውጣት ስራ  የሰራችበት እንደነበር ታስታውሳለች፡፡

የምወድሽ በፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ስትሰራ በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦባት እንደነበር ትናገራለች፡፡ በተለይም "ሕግ አስከባሪዎች ህግ ጥሰው ይሆን"? በሚለው አምድ በምትሰራው የምርመራ ዘገባ "የሰሩት ወንጀል ከሚያሳስባቸው" ከፖሊስ አባላት እና ከተለያዩ አካላት የቀረበባትን ትችት እና ገጠመኝ እንዲህ ስትል ትገልጻለች፡፡

> የወንጀል ዜናዎችን ስንሰራ ወንጀለኛውን ፖሊስ ወንጀለኛ ብሎ ደብድቦ ገርፎ ወንጀለኛ ነኝ ብሎ ስላመነ ሳይሆን ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ምን ይላል?

ወንጀሉን እንዴት ፈጸመው? ምን አነሳሳው? እሱስ ፈጽሞታል ወይ? የሚለውን ነገር አጣርተን ውሳኔ እስከሚሰጠው ድረስ ጠብቀን የምንሰራበት ሁኔታ ነው ያለው ግን በዛ ውስጥ ደግሞ እንግዲህ አንዳንድ ጊዜ የተጣመመ ፖለቲካ ደግሞ ፖለቲካ ብሎ ይከሰሻል እና ተከሰሽ አውቃለሁኝ ግን መጨረሻ ላይ ያው በማስጠንቀቂያ ነው የታለፍነው፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ሚያዚያ 21፣ቃ.መ.)

በተጨማሪም ምርጥ የፖሊሶች የምርመራ ስራዎች እንዲሁም የውጭ ሀገር የወንጀል የምርመራ ዘገባዎች ተተርጉመው የሚቀርቡበት አምድ አዘጋጅ ነበረች፡፡በፖሊስ ሬዲዮ "ጠንቀቅ" እና "እይታ" የተሰኙ ፕሮግራሞችም አዘጋጅታ ታቀርብ ነበር፡፡ በተለይም "ጠንቀቅ" በሚለው ፕሮግራሚ ላይ በሳምንቱ የተፈጸሙ የዝርፊ ወንጀሎችን በማሰባሰብ ህብረተሰቡ እንዲጠነቀቅ ግንዛቤ ትሰጥበት ነበር፡፡

በምርመራ ዘገባ ስራዋ ብዙ የህይወት ውጣውረዶችን አሳልፌአለሁ ትላለች፡፡ የምወድሽ የወንጀል የምርመራ ዜናን ስትሰራ ከገጠሟትን ፈታኝ ጊዜያት የማትረሳውን እንዲህ ትገልጻለች፡፡

አንድ ከገጠር ወደ አዲስ አበባ የመጣ ልጅ አንዲትን ልጅ ይገድላል ከዛ እኔ እልሽ ልጠይቅ እሂዳለሁኝ ለምን ገደልካት ስለው እንተኛ አልኳት ከዛ ተኛን ከዛን በኋላ ቢራ ገዝቶ መጥቶ ድጋሚ ነይ እንተኛ ስላት እምቢ አለችኝ ከዛ ሽንኩርት በምትከትፍበት ቢላዋ ወጋኋት ሲል ሂድ አፈር አባክ ብላ አስር ጊዜ መተኛት አለባት አልኩት ውስጤ ተናዶ አንዳንዴ ስምታዊ ትሆኚ እና ከጆርናሊዝም ኢቲክስ ውጭ ትሆኛለሽ እና እንዲህ ስለው እንግዲህ ኤግዚቢት ተብሎ የያዘው ቢላውን ብድግ አድርጎ እኔን ሊወጋ ሲል መርማሪው አስር አለቃ ምትኩ ይባላሉ እጁን ቀብ አድርገው ነው ያዳኑኝ፡፡(የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ሚያዚያ 21፣ቃ.መ.)፡፡

በፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ በርካታ የወንጀል ታሪኮችን ዜናዎችን እና እውነተኛ ታሪኮችን እንዲሁም የፍቅር ታሪኮችን የሰራችው የምወድሽ ከጋዜጣው ትልቅ እውቀት አግኝቻለሁ ወንጀል በጣም አስከፊ መሆኑም ተረድቻለሁ ብላኛለች፡፡ የተፈጸሙ ወንጀሎች ምን ይመስላሉ? ለምንስ ይፈጸማሉ? ሰው ወንጀለኛ የሚሆነው ፈልጎ ነው ሳይፈልግ? የሚለውን ነገር በሙሉ በጋዜጣው ከሰራሁት የወንጀል ምርመራ ዘገባ ብዙ ትምህርት አግኝቻበታለሁ ትላለች፡፡

# ፖሊስና ርምጃው

ጥቅምት ፳፫ ፲፱፻፺፫ ተመሰረተ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
የኘሬስ ዝግጅት ኃላፊና ዋና አዘጋጅ
የምወድሽ በቀለ
የፖሊስ ህትመት
ፋክስ FAX 51 12 13
Email : fpl& telecom. net.et
ስልክ ቁጥር 52 13 55
ፖ. ሣ. ቁ 40046
የባንክ ሂሣብ ቁጥር 0171818145200 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ


## ዐብይ ርዕስ

# ለስኬታማ ተግባር በጋራ መነሳት

አዲሱን የአስራ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ዓመተ ምህረትን በብሩህ ህሊና ተቀብለን የዕንቁጣጣሽንና የመስቀል በዓልን እንደየዓዳችን በመልካም ምኞትና በደስታ አክብረናል።

ትናንት አልፎ ሄዷል። ለዘንድሮው አቅደን የተነሳነውን ለመተግበር ፈረሱም ሜዳውም ፊታችን ላይ ነው ያለው። ዛሬን በሥራ አሳልፈን ውጤታማ መሆን የኛ ፈንታ ነው።

ሕይወታችንን ለመቀየር ምን ያስፈልገናል? በአመቱ ውስጥ ምን መከወን ይኖርብናል? ወዴት እንጓዝ? ምን እንፍጠር? እና ሌሎችንም መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ መዘጋጀት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል።

ከራስ ፍላጎት ባሻገር ደግሞ ሀገራዊ ግዴታዎችም እንዳሉ ይታወቃል። ሀገራችን ካለችበት የድህነት አረንቋ ለማውጣት ዜጎቿ የነፍስ ወከፍ ኃላፊነት አለብን። ዳር ድንበሯ የታፈረና

## ምን አስተዋሉ?

# ሕግ አስከባሪዎች ሕጉን በአግባቡ ይተረጉማሉ?

...ግሥ ተከታታዮች የ... ቅቶችን ... ቆዎችና ...ሮቶች በጉዳዩ ባለቤት ...ሰ ሁሜዎች ዘንድ እን ...ይታያል? ሕግ አስከ ...ሁጉን በአግባቡ ይተ ...ሉ? የሚለውን ጥያ... ይዘን ወደአዲስ ...ተማ ፖሊስ ነው...

...ማስተዳድሩ ፖሊስ



...ነር ጀማል ...ስ እንዲሰጡ ... በመጀመ...

የተከበሰ ሁሉ አይተበርም። ጥፋተኞችን በዝምድና የመ... መልከትና የመርዳት ሁኔታ ስ? አለናችው።

በርግጥ አሉ ህላፊው «አንዳንድ የፖሊስ አባላት በወገናዊነት ከሥነምግባር ጋር የተያያዙ ችግሮች ይታይባቸዋል። እነዚህ ደግሞ በአገልግሎት ላይ ችግር ይፈከትላሉ። ይህ ዓይነቱ ነገር ግን በሁሉም ፖሊስ ሊያስወቅስ አይገባም። ይልቅ በፖሊሱ ላይ ያለ የሙያ ብቃት ማነስ፣ የሰው ሀይል ችግሮች አሉ። ይህ ደግሞ በየጊዜው ለአቤቱታ የሚመጡትን ግለሰቦች የጉዳያቸውን ሁኔታ በአግባቡ ተቀብሎ የማስተናገድ፣ የማስረዳት፣ የብቃት አለመኖርና የአቅም ችግር ቅሬታን ሊፈጥር ችሏል። ከዚህ ውጪ ግን በግል ስሜት ከሥራ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ ፖሊስ ህዝቡን ይበድላል ማለት አይቻልም። እነዚህ ተግባሮች ይፈፀማሉ የሚል ግለሰብ ከሰራዊት...

ኢ.ሰና ርምጃው

የጋራ ችግሮች



እንዴት ይቃለላ

አዘጋጅ የምወደሽ በቀለ

# መካከለኛው ምሥራቅ ድርሶ መል ወደ ሞት የሚወስዱ ደላሎችስ?

የውሻ ሬሳ እንኳን ባለቤት አለው። እህቴ የእናቴ ልጅ በምን ሁኔታ
ም። ከሀገር ያወጣቻት ደላላ መጀመሪያ ከፎቅ ተወርውራ ሞተች፣ ከ8 ወር
ግሞ በመኪና አደጋ ሕይወቷ አለፈ ሬሣሽን ካገኘሽ ምን ትፈልጊያለሽ ?
ቷ ከሰል ተሞልቶልሻል እያለችኝ ውስጥ አንጀቴ አረረ ተብሰለሰልኩ» እነኚህን
ወደቢሮአችን ከመጡ አንዲት የአዲስ አበባ ነዋሪ ነው። ዝርዝሩን ጽሁፉን
ችሁ።

ተከታታይ የሆኑት
ንጉሴ የተባሉ ፀሐፊ
ል ፖሊስ ትራንስፖ
ድርጅት አስተያየ
ልከውልናል። እን
ል ደብደቢያቸው በ
ጣት ሴቶች 12ኛ
ጠናቀቁ በኋ ላ ወ
ጠናቀ ቃ ቸው በፊ
ውጭ መጓዝን የች
መፍቻ ቁልፍ አ
ል በተለይም ወደ
ምሥራቅ ሀገ
ደርጉት ጉዞ እን
ይሆንላቸውም። በ
ናቸውን በቢታችን
እንዲሸማቀቅና
ካሚ በሆነ ሥራ

ና እገዛ ማድረግ ያስፈልጋ
ል። አለበለዚያ በየጊዜው
የሚሰማው ህገወጥ አካሄድ
ያሰቡትንና መሆን የሚፈል
ጉትን ሳይሆኑ በተቋኒው
«ከድጡ ወደ ማጡ» እን
ዲሉ ያሳሰቡት አቅጣጫ እያ
ጋጠማቸው ነውና ወጣት ሴ
ቶችም ሆኑ ሌላው የኅብረ
ተሰብ አካል በብርቱ ያስብ
በት እላለሁ»ብለዋል።

ቢሮአችን መጥተው የ
ህግ ያለህ ያሉት በመግቢያ
ው ላይ ሀሳባቸውን ያነበባ



ታ በሌሎችም እየደረ
ሬም ደላላዋ ከዚህ
ያልታቀበች በመሆኗ
ታ ወጣቶችም ወደ
ሀገር እየሄዱ ስለሆነ
ሥት ትኩረት ቢያደ
ብዬ ወደ እናንተ



የወንጀል ታሪኮች ለስነጽሁፋዊ ስራዎቿ መነሻ ታሪኮችን ያገኘችባው እንደሆኑም ታነሳለች፡፡ ከጻፈቻቸው ልቦለዶች "ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች" ረጅም ልቦለድ በሰራቻቻቸው የወንጀል ታሪኮች የተገኙ ታሪኮች መነሻነት የተደረሰ እንደሆነ ተረድቻለሁ፡፡ ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች ሙሉ ታሪኩ በወንጀል ታሪክ ላይ ያተኮረ ሲሆን በብዛት በሴቶች ላይ የተፈጸመ ወንጀልን የሚያሳይ እና ሴቶች ወንጀል ፈጻሚ የሆኑባቸው ታሪኮችንም የያዘ ነው፡፡ ነገር ግን በድርሰቱ ሴቶች በደል የሚደርስባቸው ሆነው ተስለዋል፡፡

ደራሲዋ ለ26 አመታት "የፖሊስ እና እርምጃው ጋዜጣ አዘጋጅ እና በወንጀል ነክ ታሪኮች ስትሰራ በተለይም "ህጉ ምን ይላል" የሚል አምድ አዘጋጅ በነበረችበት ወቅት ከሰራቻቸው የምርመራ ዘገባዎች እውነተኛ የወንጀል ታሪኮች ለልቦለዱ መነሻ ገጠመኞች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

የምወድሽም የልቦለድ ስራዎቿ መነሻን ስትገልጽ፦ "ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች በማየው በስራየ ባየኋቸው ጉዳዮች ላይ የነበሩ ነገሮችን፣ ወንጀሎችን፣ ነው ያሳየሁበት፡፡ የማውቃቸው የኖርኩባቸው እውነቶች ስለሆኑ በቀጣይም የኖሩኩባቸው ታሪኮችን በልቦለድም ይሁን በኢ.ልቦለድ ማምጣት እችል ይሆናል እንደሱ አስባለሁ"፡፡(የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ሚያዚያ 21፣ቃ.መ.)፡፡

በፖሊስ እና ርምጃው ጋዜጣ ስትሰራ ትጉህ እና መቅረትን የማትወድ እንደነበረች ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ ይናገራል፡፡ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ በፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ስራ ከመጀመሩ በፊት ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ( ከ1990 ዓ.ም ) በፊት ስለ ድርሰት ታሪክ ሲማሩ በ 1982 ዓ.ም. የታተመው የየምወድሽ መጽሀፍ "የባከነ ጊዜ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ"ን ለትምህርት ማጣቀሻነት ይማሩበት እንደነበር ያስታውሳል፡፡

ለ19ኛው ክፍለ ዘመን ማጠቃሻነት ይሄው የየምወድሽ በቀለ መጽሀፍ ይቀርብ እንደነበር ይናገራል፡፡ ትምህርት እንደጨረሰ በፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ በሪፖርተርነት ሲቀጠር ከሷ ጋር የመስራት እድልን አገኘ፡፡ የምወድሽ ጡረታ እስክትወጣ ድረስም (ከ1991 እስከ 2001 ዓ.ም) አብሯት ሰርቷል፡፡ ለስራ ያላትን አቋም ሲገልጽ፦

> ስራ ላይ ያላት አቋም የእውነት ለመናገር በጣም ጠንካራ ነች ጠንካራ ቃላት ያጥረኛል ፡፡ ምክንያቱም እኔንም እለካዋለሁ፤ የማይደክማት ሰው ነች፤ ልጆች ታሳድጋለች፤ ቤተሰብ ትመራለች ፤እዚህ ደግሞ ፖሊስ እና እርምጃው አንጋፋ ጋዜጣ

ነው ፤እነ ማሞ ውድነህ የሰሩበት ነው ያንን ነው የተሸከመችው፤ ጋዜጣው ተወዳጅ ተፈላ እንዲሆን ተነባቢ እንዲሆን ተደራሽም እንዲሆን በጣም ጥረት ታደርግ ነበር፡፡(ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣ 2015፣ ግንቦት 21፣ቃ.መ.)፡፡

ከፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ በተጨማሪም በብሌን ቁጥር 3 መጽሄት በ1999 ዓ.ም "አርትኦት ምንድን ነው አርታኢስ ማነው"? በሚል ርእስ አርቲክል በመጻፍ አስነብባለች፡፡ በጋዜጠኝነት ተቀጥራ ለ 26 አመት ከሰራችበት ፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ በጡረታ ከወጣች በኋላም ሙያውን ቀጥላበታለች፡፡

"የምወድሽ ገጾች" በሚል የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅታ ታቀርባለች፡፡ በየሳምንቱ እሁድ ረፋድ ላይ በአሀዱ ሬዲዮ በቀጥታ በሚተላለፈው ፕሮግራሟ ሴቶችን የተመለከቱ ሀሳቦች ይነሱበታል፡፡ ፕሮግራሙ ከተጀመረ ሰባተኛ አመቱን ይዟል፡፡ የምወድሽ "የምወዳቸው ገጾች ሴቶች ናቸው" ትላለች፡፡ በፕሮግራሙ የኢትዮጵያውያን ሴቶች ታሪክ ይነገርበታል ሴቶች ስለፖለቲካዊ ፣ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ያላቸውን መረዳት ያቀርቡበታል፡፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ሙያዊ ትንተና በማቅረብ የጋዜጠኝነት ስራዋን በሬዲዮ ፕሮግራም በግሏ በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡



በአሀዱ ራዲዮ የምወድሽ ገጾች ስቱዲዮ ቀጥታ ውይይት ላይ፡፡

በጋዜጠኝነት እና በድርሰት ስራዋ በቤተሰቧ ላይ የደረሰ ጥሩም ይሁን መጥፎ ነገር አለ ወይ ብየ ወይዘሮ መሰረት ነጋን ጠየቋት፡፡ ወይዘሮ መሰረት ነጋ የምወድሽ የአክስት ልጅ ናት፡፡ግን ቅርበታቸው እንደ እናት እና ልጅ እንደሆነ ትናራለች፡፡ “በየምወድሽ ሙያ የደረሰብን ክስም ሆነ መጥፎ ነገር የለም እንደውም በሷ ሙያ ኩራት ነው የሚሰማን እንኮራባታለን” ትላለች፡፡ (ወ/ሮ መሰረት ነጋ ፣2015፣ግንቦት 19፣ቃ.መ.)፡፡

ባለቤቷ ግን ከጋዜጠኝነቱ ስራዋ ይልቅ ለስነጽሁፍ ስራዋ ድጋፍ ያደርግላት እንደነበር ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ይናገራል፡፡“ባለቤቷ ነጋዴ ነበር፡፡ የጋዜጠኛነት ስራዋን ብዙም አይደግፍም፡፡ምናልባት በምትሰራቸው የምርመራ ስራዎች ክስ ገጥሟት ያውቅ ነበር፤ጉዳትም ሊደርስባት ነበር፤በእነዚህ ክፉ ገጠመኞች መነሻ ይመስለኛል ጋዜጠኝነቱን የማይደግፈው፡፡ በስነጽሁፍ ስራዋ ግን ደስተኛ ነበር፡፡ ብዙ ድርሰቶቿን የሚያሳትመው እሱ ነው፡፡”(ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣2015፣ግንቦት 21፣ቃ.መ.)፡፡

### 3.2.2. የማህበራዊ አገልግሎት ስራ (ተጨማሪ ስራዎች)

የምወድሽ በግሏ ከምትሰራው የጋዜጠኝነት ስራ በተጨማሪ ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ትሰራለች፡፡ በጋዜጠኝነቱ ስራም ከሴቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የምታስቀድመው የምወድሽ በ 2007 ዓ.ም."Women Can Do It" (ሴቶች ይችላሉ) የተሰኘ የበጎ አድራጎት ሀገር በቀል ድርጅት በመክፈት እና በመምራት በሴቶች ዙሪያ እየሰራች ትገኛለች፡፡

ለዚህ ድርጅት መመስረት መነሻው ጡረታ ከመውጣቷ በፊት እንደነበር ነግራኛለች፡፡ ፖሊስ ውስጥ እየሰራ በነበረችበት ወደ ኖርዌይ ለስልጠና የሄደችበት አጋጣሚ የሴቶች ይችላሉ በጎ አድራጎት ድርጅትን እንድትከፍት መነሻ ሆናት፡፡ በኖርዌይ "ውመን ካን ዱ ኢት" የሚለውን ሀሳብ እንደ አንድ መሳሪያ አድርገው ነው የሚጠቀሙበት ትላለች፡፡ "የትኛዋም ሴት ችሎታ አላት" የምትለው የምወድሽ ይሄን ሀሳብ ወደ ኢትዮጵያም ለማምጣት መነሻዋ እንደሆነም ትናራለች፡፡

ድርጅቱ ከተመሰረተ ዘጠነኛ አመቱን ይዟል፡፡ በድርጅቱ ሴቶች መቻላቸውን የሚያሳዩ ስራዎች እየሰራች ነው፡፡በተጨማሪም ሴቶችም ወንዶችም ስለጾታ ጥቃት ጎጅነት እንዲያውቁ በአዲስ አበባ ትምሕርት ቤቶች ላይ በድርጅቱ አማካኝነት ትሰራለች፡፡ በአቻ ግፊት ትምሕርታቸው ላይ እንዳይዘናጉ ለማገዝም ለተማሪዎች ስልጠናዎች ትሰጣለች፡፡

"ሴቶች ይችላሉ" (Women Can Do It) በሚለው ድርጅት ውስጥ "ተማሪ ነኝ ጾታዊ ጥቃትን እቃወማለሁ" በሚል ሀሳብም ተማሪዎች የሚሳተፉበት ክበብም መስርታለች፡፡ የምወድሽ በዚህ ስራ ተማሪዎች ዋና አላማቸው መማርና መማር ብቻ መሆኑን እንዲያውቁ ግንዛቤ የምፈጥርበት ነው ትላለች፡፡ በልጃገረዶች ክበባት ደግሞ የስነጽሁፍ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች ችሎታውን የሚያሳዩበት መድረክም አላት፡፡ "ጣዝሙት" በሚል ርእስ ስኬታማ የሆኑ ሴቶች እውቅና እንዲያገኙ እና ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ የምታርግበት አመታዊ መድረክም ታዘጋጃለች፡፡



በ2013 ዓ.ም. ለስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ሴት ተፎካካሪዎችን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡

የመገናኛ ብዙሀንን በሴቶች መብት እና በጾታ ጥቃት ዙሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው እያደረገች ነው፡፡"የሴቶች መብት እንዲከበር እፈልጋለሁ ጾታዊ ጥቃቶች እንዲቆሙ እታገላለሁ" የምትለው የምወድሽ ከዚሁ ጋር የተያያዙ በሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ለመቅረብ ያለቁ ስራዎች አሉኝ ብላለች፡፡

> ሴቶች ላይ የተነሱ ጉዳዮችን እና አዘጋገብን በተመለከተ 52 ሳምንት በሬዲዮ 52 ሳምንት ደግሞ  በቴሌቪዥን ለመስራት ተፈራርሜአለሁ ፡፡ እሱን አሁን ልጀምር ነው፡፡ ሌሎችም ከዚህ ከሚዲያ አድቮኬሲ ጋር የሚገናኙ ስራዎችን በጣም አጥብቄ ለመስራት እና ውጤት ለማስመዝገብ እፈልጋለሁኝ፡፡ ሴቶች ለምን ወደ ውሳኔ ሰጭነት መድረኩ አልመጣንም? ለምን መሪዎች አልሆንም? ለምን ሁሌ ተጠቂዎች እንሆናለን? የሚሉትን ነገሮች ይዘን ሴቶች ልጆችን ወጣቶችን በተለይ የማነሳሳት ስራ ለመስራት እንግዲህ መንገድ ጀምሬአለሁ ይሄ ደግሞ ይሳካል ብየ አስባለሁ፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ሚያዚያ 22፣ ቃ.መ.)፡፡

የምወድሽ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ብዙ ተሳትፎ አላት፡፡ የኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴ ግድብ የመሰረት ድንጋይ ከተቀመጠበት 2004 ዓ.ም. ጀምሮ የህዳሴ ብሄራዊ ምክርቤት አባል ሆና እያገለገለች ትገኛለች፡፡ በ 2010 ዓ.ም. ደራሲያን እና ታዋቂ ግለሰቦች ካካተተው

ቡድን ጋር ቡድን ወደ ግብጽ በመሄድም የአባይን እውነታ ለግብጹ ፕሬዝዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲ ቤተመንግስት በመግባት አባይ መነሻው ኢትዮጵያ መሆኑን አስረድቻለሁ ትላለች፡፡

> አባይ መነሻው የኛ ነው 80 በመቶ የአባይ ዉሀ መነሻው ኢትዮጵያ ነው ይሄንን እውነታ እና ለአባይ ተፋሰስ ሀገራት እየሰጠን መሆኑን አልሲሲ ቤተመንግስት ሁሉ ገብተን ለአልሲሲ አስረድተናል እና ተሟግተናል ለሀገሬ በፊትም አሁንም እውነታን ይዤ የመሟገት ከፍተኛ ፍላጎት ነው ያለኝ፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ ሚያዚያ 22፣ቃ.መ.)፡፡

የምወድሽ ለሀገሯ ትልቅ ፍቅር አላት በወሬዋ መሀል ኢትዮጵያ ልዩ ሀገር ናት ትላለች፡፡ "የሀገራችን ባህልንም ሆነ ሁሉንም ነገር ከሌሎች ሀገራት ጋር ሳወዳድረው እኛ ትልቆች ነን ግን ትልቅነታችንን አላወጣነውም አልተጠቀምንበትም የሚል እምነት አለኝ" በማለት ትገልጻለች፡፡ ከአሜሪካ እስከ አውሮፓ እንዲሁም ብዙ የአፍሪካ ሀገራትንም የማየት እድል ያገኘችው የምወድሽ ከሁሉም ሀገራት ኢትዮጵያ ልዩ ነች በማለት ለሀገሯ ያላትን ፍቅር ትገልጻለች፡፡

ለሰው ብቻ ሳይሆን ለሀገሯ ትልቅ ፍቅር ያላት ሀገር ወዳድ መሆኗን ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየም ነግሮኛል፡፡ "በጣም ሀገሯን ትወዳለች በእውነት በጣም በጣም ስለሀገሯ ትጨነቃለች እንደጋዜጠኛ እና እንደ ሀላፊ ደግሞ ሀገሩን እንደሷ የሚወድ ሲገኝ ደስ ይላል"፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣ 2015፣ ግንቦት 21፣ቃ.መ.)፡፡ ሀገሯን መውደዷን ከምትሰራቸው ማህበራዊ ጉዳዮች እና ኢትዮጵያ ውስጥ ኑሮዋን ማድረጓን ማሳያ ነው ይላል፡፡

የኢትዮጵያ ሴት ደራሲያን ማህበር ከመሰረቱት ሴት ደራሲያን አንዷ የሆነችው የምወድሽ በቀለ የማህበሩ ፕሬዝዳንት በመሆንም አገልግላለች፡፡ የኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን አባል፣የኢትዮጵያ ሴት መገናኛ ብዙሀን ማህበር አባል፣የገቢዎች ሚኒስቴር አምባሳደር፣የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት የቦርድ ሰብሳቢ በመሆንም ሰርታለች፡፡አሁንም የየማህበራቱ አባል በመሆን እየሰራችም ትገኛለች፡፡ከሴቶች ይችላሉ ድርጅት ጎን ለጎን የጎዳና ሴት ተዳዳሪዎች ማህበር የቦርድ አባል በመሆን እየሰራች ትገኛለች፡፡



በ1996 ዓ.ም. በሴት ደራሲያን ክበብ ንግግር ስታደርግ፡፡

## 3.3. የግል አመለካከት እና ሃይማኖት

ማንኛውም የሰው ልጅ የራሱ የሆነ የሕይወት መንገድ እና አመለካከት አለው፡፡በራሱ እንዲሆን የሚመኘው እንዲሆን የሚፈለገው ህልሞች እና ውጥኖችም ይኖሩታል፡፡የምወድሽ በቀለም የራሷ የሆና እና መሆን አለበት የምትለው የግል እምነት አላት፡፡የራሷ የሆነ ጠንካራ ሐይማትም አላት፡፡

### 3.3.1. የግል አመለካከት

የምወድሽ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል አይደለሁም ትላለች፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ሰው ከፖለቲካ ውጭ መሆን አይችልም የሚል የግል አመለካከት እንዳላት ትናራለች፡፡የምወድሽ ስለ ሕይወት ያላት አመለካከትም እውነታን ይዞ ለሌሎች ደራሽ በመሆን ሕይወትን በደስታ ማሳለፍ ነው ትላለች፡፡ "ሕይወትን ካመረርሻት ትመራለች" የሕይወት አክባጁም አቅላዩም ራሱ ባለቤቱ ነው የሚል የግል አመለካከት አላት፡፡

> ህይወት መራርም ጣፋጭም ነው ግን አቅላዩም አክባጁም ባለቤቱ ነው ብየ አምናለሁኝ ፡፡ እና እኔ ባለኝ ነገር እደሰታለሁ፡፡ ፈጣሪየን ስለሚሰጠኝ ቀን ስለ አንዲቷ ሰከንድ በጣም አድርጌ አመሰግነዋለሁ፡፡ ለዚህ ያልታደሉትን ሁልጊዜ አስባለሁኝ፡፡ እኔ አይን አለኝ ፣እጅ አለኝ፣ እግር አለኝ፣ እናገራለሁ፣ አስባለሁ፣ እሰራለሁ ስለዚህ ሁሌም አመስጋኝ ነኝ፡፡(የምወድሽ በቀለ፣2015፣ሚያዚያ 21፣ቃ.መ.)፡፡

የትኛውም ሰው ሕይወትን ቀለል አድርጎ ማየት የሚችል እና ለሚገጥመው ችግር የመፍትሔ ሰው መሆን እንዳለበትም ታምናለች፡፡ የምወድሽ ከማንበብ እና መጻፍ ውጭ በየትኛውም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የማትሳተፍ እንደሆነች የነገረኝ ጓደኛዋ እና የስራ ባልደረባዋ ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ ነው፡፡

> በነገራችን ላይ ፖለቲካም አትወድም፡፡ ትኩረቷ ሰው ላይ ነው እንጅ ፖለቲካ ላይ ብትጠጋ የትናየት ትደርስ ነበር ፡፡መናገር ትችላለች ማሳመን ትችላለች ግን እንደዛ አይነት ሰው አይደለችም፡፡ ከፖለቲካ የራቀች ሰው ናት የወደቀ ሰውን ማንሳት ላይ ነው የምታተኩረው፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣2015፣ግንቦት 21፣ ቃ.መ.)፡፡

የምታያቸውን ማህበራዊ ጉደለቶች በድርሰቷ እንደምትገልጽም የሚያስታወሰውን "ድንቄም አዲስ አበባ" የሚል የግጥም ስራ በማንሳት ይናገራል፡፡ለጻፈችው ግጥም መነሻ የሆኑትን ገጠመኞችም እንዲህ ያስታውሳል፡-

> ያየችውን ችግር በደንብ አድርጋ ችግሩን በሚያሳይ መልኩ ትጽፋለች፡፡ አንድ የማረሳት ግጥም አለች አዲስ አበባ መድረክ ላይም አቅርባዋለች፡፡ "ድንቄም አዲስ አበባ" የምትል ያኔ 1997 አካባቢ ነው እና መብራት በጣም ይጠፋ ነበር እና ድንቄም አዲስ አበባ በጣም ነው የሚገርመው በቃ እንደስሟ አልሆነችም ለማለት ድንቄም.....ድንቄም ብላ አቅርባለች፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣2015፣ ግንቦት 21፣ቃ.መ.)፡፡



በ1997 ዓ.ም.በአዲስ አበባ ስታዲየም ግጥም ስታቀርብ፡፡

የምወድሽ ውሸት አለመውደድ አንዱ የሕይወት መርኋ እንደሆነ ትናገራለች፡፡ቀጠሮ አክባሪም ናት ማንኛውም ሰው ሲቀጥራት ቀድማ ትገኛለች ይኋታል፡፡ ቀጠሮ አክባሪ መሆኗን እኔም ለቃለመጠይቅ በነበረን ቀጠሮ አረጋግጫለሁ፡፡የምወድሽ ሰው ስትወድም ስትጠላም በምክንያት መሆኑን ጓደኛዋና የስራ ባልደረባዋ ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ሲገልጽ፡-

> በተለይ ሌባ አትወድም ብዙ ጊዜ ባለመታመናቸው የሚሳቀቁ ልጆች ነበሩ፡፡ እዛ ላይ አትደራደርም ካስተካካለ ካሻሻለ ይቅርታ ከጠየቀ ግን ችግር የለባትም፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣ 2015፣ ግንቦት 21፣ቃ.መ.)፡፡

### 3.3.2. ሃይማኖት

የየምወድሽ አባት ባሻ በቀለ ወልደገብርኤል እና እናቷ ወይዘሮ ወርቅነሽ ወልደማሪያም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ነበሩ፡፡እናት እና አባቷ ይከተሉት የነበረውን እምነት የሚያከብሩ ነበሩ ትላለች፡፡

"የቤተክርስቲያን ትምህርት ባይኖራቸውም እንኳን ምንም ቅልቅል የሌለባቸው ከልባቸው የሚያምኑ ገብርኤልን፣ ሚካኤልን የሚደግሱ ነበሩ፡፡"(የምወድሽ በቀለ፣2015፣ ሚያዚያ 2፣ ቃ.መ.)፡፡ ስትል በእምነታቸው ብርቱ እንደነበሩ ትገልጻለች፡፡የምወድሽም እንደ እናት እና አባቷ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ነኝ ብላለች፡፡

## 3.4. ማሕበራዊ ሕይወት

የምወድሽ ማህበራዊ ግንኙነቷ እና ሕይወቷ ሰፊ ነው፡፡ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከስራ ባልደረባ፣ ከጎረቤት ሁሉ በየትኛውም ማህበራዊ ሕይወት ትሳተፋለች፡፡ ሰው ሲታመም ትጠይቃለች፣ በሀዘንም በደስታም አብራ ታሳልፋለች፡፡ ከሰዎች ጋር ያላት የመግባባት እና ማህበራዊ ትስስሯ ሰፊ እንደሆነ ይነገርላታል፡፡

## 3.5.ትዳር (ጋብቻ)

የምወድሽ ከባለቤቷ ጋር የተገናኘነው በስራ አጋጣሚ ነው ትላለች፡፡ ባለቤቷ አቶ ረጋሳ ገበየሁ በንግድ የሚተዳደሩም ነበሩ፡፡

በንግድ ስራ ከተሰማሩት ባለቤቷ አቶ ረጋሳ ገበየሁ ጋር ከአብዮታዊ ግጥሞች ድርሰቷ በኃላ በ 1982 ዓ.ም.ለታተመው የባከነ ጊዜ አጫጭር ልቦለድ ድርሰት ለማሳተም የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ አሳትሞላታል፡፡በዚህ የጀመረው የየምወድሽ እና የአቶ ረጋሳ ትውውቅ ወደ ትዳር አምርቶ 4 ልጆችን እንዲያፈሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

ባለቤቷ አሁን በሕይወት ባይኖሩም ጥሩ የትዳር አመታት እንዳሳለፉ ትናገራለች፡፡ የምወድሽ የ3 ሴቶች እና የ1 ወንድ ልጆች እናት ናት፡፡4 የልጅ ልጆች አያትም ሆናለች፡፡የአክስቷ ልጅ ወይዘሮ መሰረትም ለልጆቿ ጥሩ እናት መሆኗን ትናራለች፡፡

> ልጆቿ አሁን ከእሷ ጋር አይኖሩም ውጭ ነው ያሉት እና ልጆቿ በጣም ጎበዞች ናቸው፡፡ አንዷ ዶክተር ናት፣ አንዷ ኢንጅነር ናት፣ አንዷ አካውንቲንግ ናት እና ጥሩ ጥሩ ልጆች አሷት አብቅታለች፡፡ ለልጆቿ ጥሩ እናት ናት በጣም ከሌላው ቤተሰብ ጋርም በጣም ጥሩ ቅርበት ነው ያላት፡፡ (ወ/ሮ መሰረት ነጋ፣ 2015፣ ግንቦት 19.ቃ.መ.)፡፡

ከቤተሰቡ እንደ አንቺ ጋዜጠኛ ወይም ደራሲ የሆነ ሰው አለወይ? ብየ የምወድሽን ስጠይቃት ማንንም የኔን ሙያ የተከተለ የለም ብላኛለች፡፡ የየምወድሽን ሙያ ከቤተሰቡ የተከተለ ሰው ባይኖርም መጻሐፍትን እንዲያቡ ግፊት ታደርግባቸው እንደነበር የአክስቷ ልጅ መሰረት ትናራለች፡፡ "ማንበብ ትልቅ ደረጃ ያደርሳል" ትለናች፡፡ የምወድሽ መጽሀፎቿ እንደታተሙ ቅድሚያ ለእያንዳንዱ ቤተሰቦቿ ፊርማ ትሰጠናለች፡፡ እንደ እሷ ደራሲ የሆነ ቤተሰብ ባይኖርም ጥሩ አንባቢ እንድሆን አድርጋናለች" ፡፡(ወ/ሮ መሰረት ነጋ፣ 2015፣ ግንቦት 19፣ቃ.መ.)፡፡

የምወድሽ ከዘመድ አዝማድ ጋር ጥሩ ቅርበት እንዳላት እና በገንዘብም በሀሳብም እንደምትረዳ ከወይዘሮ መሰረት ጋር ባረጉት ቃለመጠይቅ ተረድቻለሁ፡፡ወይዘሮ መሰረት አሁን የግል ስራ ላይ ብትሰማራም ከየምወድሽ ጋር እንደ ልጅ አብራ መኖሯን ትናገራለች፡፡ ለቤተሰቡ የምታደርገውን ድጋፍም ወይዘሮ መሰረት እንዲህ ስትል ትገልጻለች፦

ድጋፍ ታደርግልኛለች የሆነ ነገር ሲጎልብኝ በገንዘብም ትረዳኛለች እንድማርም ትገፋፋኛለች፡፡ መጽሀፎቿ ገና ሳይመረቁ ለቤተሰብ ነው መጀመሪያ የምትሰጠው፡፡ ከቤተሰብ ጋር ያላት ቅርበት በጣም የጠበቀ ነው፡፡ (ወ/ሮ መሰረት ነጋ፣2015፣ግንቦት 19፣ቃ.መ.)፡፡

ወይዘሮ መሰረትን ለምወድሽ በስራዋ የምታደርጉላት እገዛ አለወይ ብየ ጠይቂያትም ነበር ቤተሰቡ ሁሉ ይተጋገዛል ያለችኝ ወ/ሮ መሰረት መጽሀፍ ስትጽፍ በኮምፒዩተር ጽሁፍ እንደምታግዛት ትናገራለች፡፡

አወ በጽሁፍ ደረጃ የተወሰነ ጽሁፎችን አግዛታለሁ፡፡ ማለትም የኮምፒዩተር ጽሁፍ አግዛታለሁ፡፡ ለምሳሌ ሁለት መጽሀፍ አግዠታለሁ፡፡ "ያልፈራ ፍሬን" እና "ናዋዡ ምሁርን፡፡"(ወ/ሮ መሰረት ነጋ፣2015፣ግንቦት 19፣ ቃ.መ.)፡፡

የምወድሽ በስራ ቦታዋ እና በሌሎች ማህበራ ጉዳዮችም ቀድማ ደራሽ ናት፡፡ ሰው ሲቸገር አትወድም ከችግሩ የሚወጣበትን መንገድ መፈለግ ይቀናታል፡፡ ከቻለች ብቻዋን ካልሆነ ሰዎችን በማስተባበር ለተቸገሩ ቀድሞ መድረስ ያደስታታል፡፡ይህንንም ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ እንዲህ ሲል ይገልጻል፦

ለሰው ችግር ቀድሞ ደራሽ ናት ሰው ሲታመም የመጠየቅ ጊዜ ብዙ ሰዎች ስራ አለን አይመቸንም ሊሉ ይችላሉ የምወድሽ ግን በፍጹም አልችልም አትልም፡፡ በእኔ ሕይወት ትልቅ ቦታ አላት አንድ አጋጣሚ ልንገርሽ በአጋጣሚ ከባለቤቴ ጋር አብረን በነበርንበት ጊዜ አንግባባም ነበር እና የመጀመሪያ ልጄ ሲወለድ እንዴት አድርጌ መጠቅለል እንዳለብኝ እንዴት ማቀፍ እንዳለብኝ ያስተማረችኝ የምወድሽ ናት፡፡ እንዲህ አድርገህ ጠቅልለው እንዲህ አድርገው እቀፈው ባለችኝ መሰረት አደርግ ነበር....... በዛ መልኩ ልጄን በጣም ስትሮንግ ሆኘ ነው ያሳደኩት፡፡ ባለቤቴ ለስራዋ ነበር ቅድሚያ የምትሰጠው ጥላ ነው የምትሄደው እኔ ደግሞ ልጄን ጥየ መሄድ ይከብደኛል ፡፡በዚህ ጊዜ የምወድሽ ስነግራት ከፈቃድ ውጭ ትጨምርልኛለች ልጄን እጠብቃለሁ ፤ሂጀ እየተንከባከብኩ አሳድጌአለሁ እና በጣም መልካም ሰው ናት፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣2015፣ ግንቦት 21፣ቃ.መ.)፡፡

የጎዳና ተዳዳሪዎችን ማገዝ ገና ተቀጣሪ ሁና እየሰራች እያለችም ምኞቷ እንደነበር ይነገርላታል፡፡ ቢቻል ከጎዳና ህይወት እንዲወጡ ካልሆነም ደግሞ መመገብ እና መታጠብ እንዲችሉ ጥረት ታደርግ እንደነበርም ጋዜጠኛ ተስፋየ ይናራል፡፡

> መሳለሚያ ወረድ ብሎ ትልቅ ጊቢ ቤት ነበራቸው አንድ ቀን አሳየችኝ ይህን ጊቢ አምስት ስድስት ሻወር አሰርቸ በነጻ እዚህ ጎዳና ተዳዳሪዎች እንዲታጠቡ ማድረግ እፈልጋለሁ አለችኝ፡፡ በጣም ነው የገረመኝ ይሄ ከ 20 አመት በፊት ነው ምን አይነት ሂውማኒቲ ነው፡፡ እሱን ማሳካት ችላለች፣ በውመን ካን ዱ ኢት የጎዳና ተዳዳሪዎችን ጨምሮ ሴቶች ላይ የምትሰራው ስራ ቀድሞ የነበረ ፍላጎቷ ነው፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣2015፣ ግንቦት 21፣ ቃ.መ.)፡፡



በአዲስ አበባ በ 1995 ዓ.ም. የጎዳና ልጆችን ቃለመጠይቅ ስታደርግ፡፡

ለሌሎች ቀድሞ መድረስ የዘወትር ተግባርና ልምዷ መሆኑን ደራሲ እንዳለጌታ እንዲህ ሲል ይገልጸል፡፡ "የምደውሽ ለወደደችው ሟች ናት፡፡ በችግር ጊዜ ፈጥና መድረስ ትችላለች፡፡ በዙሪያዋ ባሉ ሰዎች ስኬት የሚሰማት ደስታ ከፍ ያለ ነው፡፡ ማስተባበር ይሆንላታል"፡፡ (እንዳለጌታ ከበደ (ዶ/ር)፣2015፣ቃ.መ.)፡፡ ከሰዎች ጋር ያላት ቅርበት ሰፊ መሆኑን እና አሁንም ሰዎችን ለማገዝ የምታደርገው ጥረት ቀድሞ የነበረ ልምዷ መሆኑን ተረድቻሁ፡፡ በግሏ ለመሰረተችው "ሴቶች ይችላሉ" ሀገር በቀል በጎ አድራሆት ድርጅት መነሻዋ ከቀድሞ የመጣው ሰውን የማገዝ እና የመርዳት ፍላጎት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡



በ 1995 ዓ.ም. አዲስ አበባ የጎዳና ልጆችን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡

## 3.6. የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ

የምወድሽ አብዛኛውን ጊዜዋን በስራ፣ በማንበብ እና በመጻፍ ብታሳልፍም በትርፍ ጊዜዋ ፊልም ማየት እና መዝናናት እንደምትወድ ትናገራለች፡፡ ሙዚቃ፣ዳንስ እና ፊልም ከልጅነቴ ጀምሮ ነው የምወደው ትላለች፡፡ ትርፍ ጊዜ ሲኖራት በምን እንደምታሳልፍ ስትገልጽ ፦

> ለምሳሌ ወጣ ብለን ስብሰባ በምናደርግበት ጊዜ ከከተማ ወጣ ስትይ የአየር ለውጥ አለ ከሀገር ወጣ ስትይ የአየር ለውጥ አለ ወደ ልጆቹ ጋር ስሄድ ያንያን ጊዜ ትርፍ ጊዜ ይኖረኛል፡፡ሙዚቃ ደግሞ እወዳለሁ በነገርሽ ላይ ሌሊትም ቢሆን ሙዚቃ አዳምጣለሁ በቃ ደስ ይለኛል ድሮድሮ ፊልም ያየሁትን ፊልም በቃ እያንዳንዱን በቃሌ ጭምር ነበር የማጠናው አሁን እንደሱ አይደለሁም ግን ፊልም ማየት እወዳለሁኝ ሙዚቃ በጣም እወዳለሁ ማንበብ እወዳለሁ አልፎ አልፎ ደግሞ ዳንስ የሚጋብዘኝም ካለ .....ዳንስ እወዳለሁ ደስ ይለኛል ዘና ብሎ መኖር ደስስስ ይለኛል፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ ግንቦት 15፣ ቃ.መ.)፡፡

የምታያቸው ፊልሞች እና የምታዳምጣቸው ዘፈኖች የፍቅር ይዘት ያላቸው እንደሆኑ የምትናገረው የምወድሽ ይህም በምትጽፋቸው ድርሰቶች ይዘት ውስጥ በጎ ተጽእኖ እንዳደረገላት ትናራለች፡፡ የምወድሽ የመዝናናት እድል ስታገኝ የተገኘችበት ቦታን አድማቂ ናት፡፡ በተከፈተው ሙዚቃ ሁሉ ትደንሳለች ሰውን ማዝናናት ትወዳለች፡፡ ለማዘንም ለመደሰትም ቅርብ እና ሰው ሲያዝን አብራ የምታዝን የሚደሰት ሰው ስታገኝም አብራ የምትደሰት ናት ይሏታል፡፡

> ጌቱጌዘር እናዘጋጃለን እሷ ነች የምታስተባብረው አንድ ቁጥር ዳንሰኛ እሷ ነች በድምጿም ትዘፍናለች በቃ ለዛም ነው ጤነኛ ሆና እንደዚህ እድሜዋ የረዘመው ሁሌም የሚቆዝም፣ ነገር የሚበላ ሰው በሽተኛ ነው የሚሆነው እሷ ከራሷም አልፋ ከሰው ጋርም ነው የምትግባባው ፡፡ በጣም ነጻ ናት ጀኔራሎች ባሉበት እንደንሳለን እንደዛ ነው ባህሪያዋ እኛም እንደዛ ሆነናል፡፡ (ጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋየ ምትኩ፣ 2015፣ ግንቦት 21፣ ቃ.መ.)፡፡

# 3.7. የድርሰት ሕይወት

## 3.7.1. የድርሰት አጀማመር

የምወድሽ ገና በልጅነቷ አባቷ በሚገዙላት መጽሀፍት እንዲሁም ጋዜጣ ነው ከስነጽሁፋዊ ስራዎች ጋር የተገናኘችው እና ማንበብ የጀመረችው፡፡ አባቷ ባሻ በቀለ ወልደገብርኤል “በሳምንት አንድ መጽሀፍ አንብበሽ ከጨረስሽ ሽልማት ይሰጥሻል” እያሉ የማንበብ ፍላጎት እንዲኖራት አደረጉ፡፡

የያኔዋ ታዳጊ ልጅም አንድም የአባቷን ትእዛዝ ለመፈጸም ሁለትም በአባቷ የተገባላትን የሽልማት ቃል ለማግኘት በሳምንት አንድ መጽሀፍ አንብባ መጨረስን ተያያዘችው፡፡ በሳምንት ከአንድ ወደ ሁለት መጽሀፍ ከዛም የአባትን ትእዛዝ ሳይጠብቁ በሳምንቱ ከአንድ መጽሀፍ ተጨማሪ መጽሀፍ እንዲገዛላት ወደ መጠየቅ ተሸጋገረች፡፡

አባት ባሻ በቀለም በየሳምንቱ የሚወጡ አዳዲስ የልቦለድ መጽሀፍትን መግዛት እና ለልጃቸው መስጠትን ተያያዙት፡፡ የምወድሽ ለድርሰት ዝንባሌዋ እንዲዳብር ያደረጋትን መነሻ ስጠይቃት አባቴ ነው ብላኛለች፡፡ አባቷ ይገዙላት የነበሩትን መጽሀፍትም ታስታውሳለች፡፡

> በልጅነቴ ነው ማንበብ የጀመርኩት፡፡አባቴ ቅዳሜ ቅዳሜ ሁለት መጽሀፍ ሶስት መጽሀፍ ይገዛልኛል፡፡የመጻህፍቶቹ ዋጋ ደግሞ በጣም እርካሽ ናቸው፡፡በተከታታይ የሚወጡ “አንድ ልጅ ወድጄ”፣ “አንዲት ወጣት ወድጄ”፣ “የፍቅር ረመጥ” የሚባሉ መጽሀፍት ያኔ ይወጡ ነበረ ትንንሽ ማለት ነው ከዛ እነሱን መጽሀፍት ያመጣልኛል አነባለሁ፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ሚያዚያ 22፣ ቃ.መ.)፡፡

በዚህ የዳበረው የስነጽሁፍ ጅማሮ በትምህርት ቤት ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የሚሰማትን ያየችውን ሁሉ በግጥም እንድትገልጽ አስቻላት፡፡ በትምህርት ቤት የተለያዩ ግጥሞችን በመጻፍ የስነጽሁፍ ችሎታዋን ማሳደግን ተያያዘችው፡፡

> ግጥም አገጣጠሜ ደግሞ በሰው ስም ነው፡፡ አሁን ያንቺ ስም ዙፋን ከሆነ በዙፋን አንድ፣ በቁመትሽ፣ በአይንሽ፣ በሁኔታሽ ምናምን እንደዛ ነበር የምገጥመው፡፡ ትምህርት ቤት ውስጥ በጣም ሳቂታ በጣም ቀልደኛ ዝም ብሎ በድፍረት የሚናገር

አይነት ልጅ ነበርኩኝ እና ልጆቹን በግጥም ስድብ ሁሉ በቃ አጭር ከሆኑ በተለይ እኔ የረዘምኩ ስለሆነ አጭር እንደመሳቂያ ነበር ያኔ እኔ ባለኝ ግንዛቤ እሱ ሁሉ ግጥም ይጻፍበት ነበር፡፡(የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ ሚያዚያ 22፣ ቃ.መ.)፡፡

በሚወጡ የሥነፅሑፍ ውድድሮች ትምህርት ቤት ወክላ የምትሳተፈው የምወድሽ የመጻፍ ህልሟን የሚያሳካ እድል ገጠማት፡፡ በ 1972 ዓ.ም የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ በነበረችበት የባህል ሚኒስቴር ባወጣው የግጥም ውድድር የጻፈቻቸውን ግጥሞች በማቅረብ አሸናፊ ሆነች፡፡ ግጥሞቹ ተሰባስበው "አብዮታዊ ግጥሞች" የሚል ርእስ ተሰጥቷቸው የመጀመሪያዋ የግጥም መድብል ታተመላት፡፡ የሴቶች ጉዳይ ከልጅነቷ ጀምሮ ልቧን እምደሚነካት የጻፈቻቸውን ግጥሞች ታስታውሳለች፡፡

ያኔ ስለሴተኛ አዳሪነት ጽፌአለሁኝ ምክንያቱም በአካባቢያችን እናቴ የምታከራየው ቤቶች ውስጥም ሴተኛ አዳሪ ስለነበሩ፡፡ሴተኛ አዳሪ በመሆናቸው ትምሕርት አይማሩም፣ሌቱን ሙሉ የት እንደሚያድሩ አላውቅም ወደ ቤት የሚመጡት እኛ ከእንቅልፍ ስንነሳ ሲነጋ ነው፣ሴተኛ አዳሪ መሆናቸው ልቤን ስለሚነካው ስለነሱ ጽፌአለሁ ሴት እንደምትችል ገና በልጅነቴ ነው የጻፍኩት፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ ሚያዚያ 22፣ ቃ.መ.)፡፡

በ 1972 ዓ.ም. በታተመው አብዮታዊ ግጥሞች ውስጥ "ተነሽ እቴ" ግጥም ከላይ የተነሳውን ሀሳብ የሚደግፍ እና የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ በግጥሞቿ ስንኞች ሴቶች በተለይም በስራ ማጣት ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሚመጡ ሴቶች ለሴተኛ አዳሪነት እየተጋላጡ መሆኑን አንስታበታለች፡፡

ተነሽ እቴ

የቡና ቤቲቱ

ተሰናጅ ለዘመቻ

ይቅር ሽኩቻው፡፡

መጠሪያሽ ከሚሆን ሴተኛ አዳሪ

ተነሽ እቴ ለሥራ ተጣጣሪ

ሂጅና ገጠር ስሪ፡፡ (አብዮታዊ ግጥሞች፣13-14፣1972)

የግጥሙ ስንኞች እንደሚያስረዱት ሴቶች በወቅቱ ለችግር እንደተጋለጡ ነው፡፡ ለዚህ ሀሳብ መነሻ በልጅነቷ በቅርበት ከምታውቃቸው ሴተኛ አዳሪ የቤት ተከራዮቻቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በልጅነቷ የተለያዩ ልቦለዶችን በማንበብ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪ እያለች በ 9 አመቷ ግጥም በመጻፍ የጀመረው የስነጽሁፍ ሕይወት ከ 1972 ዓ.ም ጀምሮ ይህ ጥናት እስከተደረገበት 2016 ዓ.ም. ድረስ በግል እንዲሁም ከሌሎች ደራሲያን ጋር በመሆን 16 ድርሰቶችን ለአንባቢ እንድታደርስ አስችሏታል፡፡

የምወድሽ ድርሰቶቿ ከሕይወት ታሪኳ እና ትክክለኛ ገጠመኞቿ የተቀዱ ለመሆናቸው ሌላም ማሳያ አለ፡፡ በሴት ላይ በማተኮር የምወድሽ በቀለ ከሌሎች ደራሲያት ጋር በ 1995 ዓ.ም. ከታተመው "ዕጣ" አጫጭር ልቦለድ ታሪኮች ውስጥ "የቁራ ጩኸት" በሚል አርእስት ባቀረበችው አጭር ልቦለድ ታሪክ ጉዳዩ ከግል ሕይወቷ ጋር የሚገናኝ ነገር ያለው ይመስላል፡፡ በአንዲት በልጅነቷ በለጋ እድሜዋ በተደፈረች ሴት ላይ የሚያተኩረው አጭር ልቦለድ ልጅቷ በመደፈሯ የደረሰባትን አካላዊ ስነልቦና እና ሞራላዊ ጉዳት የሚያሳይ ታሪክን የያዘ ነው፡፡

ገና በ 16 አመቷ በጓደኛዋ ወንድም የተደፈረችው ቤቲ የደረሰባትን አካላዊ ህመምና ስቃይ ስነልቦናዊ ቀውስ እንዲሁም የፍትህ መዛባትን አሳይታበታለች፡፡ በአስገድዶ መደፈር የሚደርስን ጉዳት ከማሳየት በተጨማሪ ታሪኩ የፍትሕ ጥያቄንም የሚያሳይ ነው፡፡ በ 16 አመቷ አስገድዶ የደፈራት ወንጀለኛ በ 8 አመት እስራት ብቻ እንዲቀጣ መደረጉን በማሳየት የፍትሕ አሰጣጥ ጉድለትን በታሪኩ ትሞግታለች፡፡


"የዚያን ቀን ውሳኔውን ስሰማ ራሴን ወቀስኩት፡፡ ልጄን ገና በ 16 አመቷ ለአካለ መጠን ሳትደርስ በእህቱ መኝታ ክፍል አስገድዶ ደፍሯት፣ለማይሽር የህሊና ቁስል ዳርጓት ህግ ይቀጣልኛል ብዬ ከሁለተ ዓመት በላይ ተንከራትቼ፣ስምንት ዓመት መወሰኑ አቃጠለኝ፡፡ ምነው አጸፋውን አናቱን ብዬ በተከሰስኩና እኔ ላይ እስራት በተፈረደብኝ አሰኘኝ፡፡

ፉከራ ብቻ!ቃላት ብቻ!እኛ ሴቶች የሚደርስብን ጥቃት ወንዶቹ አይሰማቸው ይሆን?ወይንስ ያኔ ገና ከ 40 ዓመት በፊት "ወንዶች ለሴቶች በሚያዝኑበት ወቅት" የወጣው ህግ ያለመለወጡ ይሆን ዳኞችንም እንዳይጫኑ የሚያደርጋቸው?አልገባኝም"፡፡(ዕጣ፣1995፣70-71)፡፡

በደረሰባት አስገድዶ መደፈር የኤችአይቪ(ኤድስ) በሽተኛ እንድትሆን ምክንያት የሆነው ደፋሪው ባለታሪክ በፍርድቤት የተወሰነበት ቅጣትን ተመጣጣኝ እንዳልሆነ አሳይታበታለች፡፡ የቁራ ጩኸት በማለትም ሰሚ ማጣትን በማጉላት ለመሰል አጸያፊ ድርጊቶች እና ወንጀሎች ትኩረትን እንደሚፈልግ መልእክት አስተላልፋበታለች፡፡

ነገር ግን ታሪኩ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ እና የየምወድሽ ታሪክ ይመስላል፡፡ በታሪኩ ላይ የተገለጹት መቼቶች ከየምወድሽ የሕይወት ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡በሴቶች ላይ በምትሰራቸው የበጎ አድራት ስራዎች መሰል ጥቃቶች በሴቶች ላይ እንዳይፈጠሩ አጥብቃ ለመስራቷ ከግል ሕይወቷ ጋር የተገናኘ መነሻ ታሪክ ያለው ነው፡፡

በምትጽፋቸው ድርሰቶችም እውቅ ሐያሲያን ሙያዊ አስተያየት ይሰጧት ነበር፡፡ የምወድሽ በምጽፋቸው ድርሰቶች ይሰጡኝ የነበሩ ሙያዊ አስተያየቶች ለስራዎቸ መሻሻል አግዘውኛል ትላለች፡፡ አሁን በሕይወት የሌሉት ደራሲና ሐያሲ መስፍን ሀብተማርያም እና ደራሲና ሐያሲ ዘሪሁን አስፋው ስራዋን በማረም ሙያዊ እገዛ ያደርጉላት እንደነበር ትናገራች፡፡



የምወድሽ በቀለ ከደራሲ ስብሀት ገብረእግዚአብሄር ጋር፡፡

“ጋዜጠኝነትና ድርሰትን እስከምሞት ድረስ አልተወውም” የምትለው የምወድሽ አሁንም ሕትመት እየጠበቁ የሚገኙ ያለቁ የድርሰት ስራዎች አሉኝ ብላለች፡፡

የምወድሽ በትወና በመድረክ ቲያትር የመሳተፍ እድል እንደነበራት ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ነግሮኛል፡፡ ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ የምወድሽን በስራዎቿ ከ 1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ያውቃታል፡፡ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ከየምወድሽ ጋር በአካል የተዋወቀው እንዳለጌታ ከበደ በኢትዮጵያን ደራሲያን ማህበር በሚታተመው ብሌን ቁጥር 3 መጽሔት በአዘጋጅነት አብረው እንደሰሩ ይናገራል፡፡ የምወድሽ የድርሰት ስራዎችን ከማበርከት በተጨማሪ ለሌሎችም የኪነጥበብ ባለሙያዎች  በር የከፈተች ናት ይላል፡፡

> በኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አማካኝነት ሕያው የጥበብ ጉዞ ወደ ፍቅር እስከመቃብር ሀገር በሚል ርእስ ጉዞ ሲዘጋጅ አብረን ነበርን፡፡ከመጽሀፉ የተቀነጨበ ድራማዊ ምንባብ ሲሰራም ጋሽ አስፋው ዳምጤ ፊታውራሪ መሸሻን ወክለው ሲጫወቱ እሷ ወይዘሮ ጥሩ አይነትን ወክላ ተውናለች፡፡ በተለያዩ መድረኮች አብረን ስራዎቻችን አቅርበናል፡፡አዳዲስ ሴት ደራሲያን ለማብቃት በምታደርገው ውለታም እኔም መሰሎቼም የክብር ወንበር የምንለቅላት ነበረች፡፡ (እንዳለጌታ ከበደ (ዶ/ር)፣ 2015፣ ሰኔ 20፣ቃ.መ.)

ደራሲ እንዳለጌታ ከበደም የየምወድሽን ድርሰቶች ፣የምታነሳቸውን ማህበራዊ ጉዳዮች እወዳቸዋለሁ ይላል፡፡ ከድርሰቶቿ ውስጥ አብልጦ የሚወዳቸውን ስራዎችም እንዲህ ይገልጻል፡፡

> ከየምወድሽ ስራዎች የተለየ ግምት የምሰጣቸው ሁለት ናቸው፡፡ የባከነ ጊዜን እና ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች፡፡የባከነ ጊዜ እንደተማርኩት በደራስያት የታተመ የመጀመሪያው የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ ነው፡፡ ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች ከስራዎቿ በተለየ ሁኔታ አከብረዋለሁ፡፡ ምነው ቢባል ልቦለዱ ወንጀል ነክ ነው፡፡ (እንዳለጌታ ከበደ (ዶ/ር) ፣ 2015፣ ሰኔ 20፣ ቃ.መ.)፡፡

### 3.7.2. የንባብ እና የአጻጻፍ ልማድ

የምወድሽ በቀለ መጻፍ እና ማንበብ በሕይወት እስካለች የማትተወው ከምንም በላይ የምታስቀድመው እንደሆነ ትናገራለች፡፡ ለማንበብ ቦታ የማትመርጥ ቢሆንም ከምታነበው ደግሞ በተለይም የድርሰት ስራዎች የአሽናፊነት ጭብጥ ያላቸው ቢሆኑ ደስ ይለኛል ትላለች፡፡

> ማንበብ የምወደው ሁል ጊዜ ስለ እውነት ከሆነ የተጻፈው ነገር የእውነትን ጥቅም እና አሸናፊነት የሚያሳይ ሲሆን ደስ ይለኛል ስለ ፍቅር ከሆነ የፍቅር አሸናፊነት የሚያተኩር የአንድነትን የህብረትን ብቻ የጋራ ነገሮችን የሚያጎላ ፣ ወደፊት የሚያሻግር ድርሰት ሲሆን እወዳለሁኝ ትላለች፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ ሚያዚያ 28፣ ቃ.መ.)

ከስነጽሁፍ ስራዎች ውጭ ለትምህርት እና ለሌሎች ተጨማሪ ስራዎች አነባለሁ ትላለች፡፡ ድርሰት ስትጽፊ የምትመርጭው ቦታና ጊዜ አለ ወይ? ብየ ስጠይቃት ሌሊት እና ብቻዋን ስትሆን መጻፍን እንደምትመርጥ ትናገራለች፡፡

> ብዙ ጊዜ አልተኛም ብዙ ማለት ረጅም እንቅልፋም አይደለሁም፡፡ እና እነሳ እና ሀሳብ ከመጣልኝ ሌሊት ላይ እጽፋለሁ፡፡ ለመጻፍ የምመርጠው ሁኔታ ሌሊት እና ብቻየን ስሆን ነው ቦታ አልመርጥም ቤቴም ሆነ ሌላ ቦታ ጊዜው ሌሊት ከሆነ እና ብቻየን ከሆንኩ ማለቴ ነው፡፡ (የምወድሽ በቀለ፣2015፣ ሚያዚያ 28፣ ቃ.መ.)፡፡

የምወድሽ ሲከፋትም ትጽፋለች ከሰዎች ስሜት ተነስታም ትጽፋለች ትገጥማለች ይኋታል፡፡የአክስቷ ልጅ መሰረት ነጋ ለመጻፍ የምትመርጠውን ቦታና ሁኔታ ስትገልጽ፡-

> የምወድሽ ጸጥ ያለ ቦታ ትፈልጋለች ብዙ ጊዜ ሌሊት ነው የምትጽፈው ብዙውን ጊዜ ሳያት ሌሊት ነው የምትወደው ጸጥ ሲል ነው በቃ ሰው ሲተኛ እሷ ትጽፋለች ሌሊትን ነው የምትመርጠው፡፡ (ወ/ሮ መሰረት ነጋ፣ 2015፣ ግንቦት 19፣ ቃ.መ.)፡፡

የምወድሽ ገና በልጅነቷ ስታነባቸው የነበሩ "የፍቅር ረመጥ" ፣ "የእንቁላል ሌባው በእስራት ተቀጣ" የሚሉ መሰል የፍቅር እና የወንጀል ጭብጥ ያላቸው መጻህፍት እንዲሁም ጋዜጦች

አሁን በምትጽፋው መጽሀፎች ጭብጥ ላይም ይታያሉ፡፡እሷ ግን ለድርሰቶቸ መነሻየ ከማህበረሰቡ የማያቸው ማህበራዊ ጉዳዮች ናቸው ትላለች፡፡

### 3.7.3. የድርሰት ስራዎች ብዛት

የምወድሽ በቀለ ከ 1972 ዓ.ም ጀምሮ በግሏ 10 ከሌሎች ደራሲያን ጋር በጋራ 6 በአጠቃላይ 16 መጽሀፍትን ይህ ጥናት እስከተደረገበት ጊዜ ( እስከ 2016 ዓ.ም.) ለህትመት አብቅታለች፡፡ በግሏ ከጻፈቻው መጽሀፍት ውስጥ በጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ እውነተኛ ታሪኮች ስብስብ የሆነው ከባድ ቁስል በነጻ ለአንባቢ የተሰራጨ ነው፡፡ የእውነተኛ ታሪኮች ስብስብ የሆነው "ከባድ ቁስል" በሶስት ቋንቋ በአማርኛ፣ ኦሮሚኛ እና እንግሊዘኛ ተተርጉሞ 6000 ኮፒ በነጻ ተሰራጭቷል፡፡

### 3.7.4. የየምወድሽ በቀለ የግጥም መጻሕፍት

| የድርሰቱ ርእስ | የህትመት አመተ ምህረት |
|---|---|
| አብዮታዊ ግጥሞች | 1972 ዓ.ም. |
| ያልፈራ ፍሬ እና ሌሎች የግጥም ስብስብ | 1992 ዓ.ም. |
| ዋጊኖስ የግጥም መድብል | 2003 ዓ.ም. |

### 3.7.5. የየምወድሽ በቀለ የልቦለድ መጻሕፍት

| የድርሰቱ ርእስ | የህትመት አመተ ምህረት |
|---|---|
| የባከነ ጊዜ አጫጭር ልቦለዶች ስብስብ | 1982 ዓ.ም. |
| እብዱ በለጠች ኖቤላ ረጅም ልቦለድ | 1996 ዓ.ም. |
| ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች ረጅም ልቦለድ | 2002 ዓ.ም. |

### 3.7.6. የየምወድሽ በቀለ ኢ. ልቦለድ መጻሕፍት

| የድርሰቱ ርእስ | የህትመት አመተ ምህረት |
|---|---|
| ናዋገፉ ምሁር | 2004 ዓ.ም. |
| የጀርባ ሐቆች | 2010 ዓ.ም. |
| ነገን በተስፋ አያለሁ | 2013 ዓ.ም. |
| ከባድ ቁስል | 2014 ዓ.ም. |

## 3.8. በድርሰት እና በሌሎች ስራዎች የተገኙ ሽልማቶች

የምወድሽ በቀለ በድርሰት ስራ በ 1972 ዓ.ም የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የግጥም ውድድር በአብዮታዊ ግጥሞች ስራዋ አሸናፊ በመሆን የመጀመሪያ የ 3 ሺ. ብር የገንዘብ ሽልማት አግኝታለች፡፡

በድርሰት ስራዋ ከበድ ያለ ሽልማት ባታገኝም የተለያዩ የእውቅና ሰርትፊኬት ከተለያዩ ተቋማት ተበርክቶላታል፡፡ ከኢትዮጵያ ታላቁ የህዳሴ ግድብ ምክርቤት ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሀይለማርያም ደሳለኝ የሰርትፊኬት እና ዋንጫ ሽልማት ተበርክቶላታል፡፡ ከአሁኑ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ የገቢዎች ሚኒስቴር አምባሳደር ሆና በሰራችው ስራ የሰርቲፊኬት ሽልማት እና እውቅና አግኝታለች፡፡

ከኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት ስንዱ አዋርድ ዋንጫ እና ሰርቲፊኬት ተሸልማለች፡፡ሌሎች በርካታ የእውቅናና ሰርቲፊኬትም ከተለያዩ ተቋማት ተበርክቶላታል፡፡

የምወድሽን በስራሽ ያገኘሻቸው ሹመቶች አሉ ወይ? ብየ ስጠይቃት "ሹመት አልፈልግም" ትላለች፡፡ "እኔ በግሌ ሹመት ማለት እስር ማለት ነው፡፡ ለአንድ ለዛ ለሾመሽ አካል የምትገዥበት ስለሚመስለኝ ለሹመት ፍላጎትም የለኝ ሊሾመኝም የፈለገም ሰው የለም፡፡ እኔም ሹመት የምትለውን ነገር በጣም ነው የምሸሻት"፡፡(የምወድሽ በቀለ፣ 2015፣ ቃ.መ.)፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የየምወድሽ በቀለ የተመረጡ ድርሰቶች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ የየምወድሽ በቀለ የድርሰት ስራዎች ውስጥ የጥናቱ አላማን መሰረት በማድረግ የተመረጡ ስራዎች ትንተና የቀረበበት ነው፡፡ የምወድሽ በቀለ ከ1970ዎቹ ጀምሮ ይህ ጥናት እስከተደረገበት 2016 ዓ.ም.ድረስ 16 መጻህፍትን በግሏ እና ከሌሎች ደራሲያን ጋር በጋራ ለንባብ አብቅታለች፡፡ይህ ጥናት በግሏ ከሰራቻቸው 10 መጻህፍት ውስጥ 15 ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

ለትንተና የተመረጡት ስራዎች በሴቶች እና ወንጀል ነክ ጉዳዮችን ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ "አብዮታዊ ግጥሞች"፣ "ዋጊኖስ የግጥም መድብል"፣"የባከነ ጊዜ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች" እና "ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች" ረጅም ልቦለድ እንደሚከተለው ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

### 4.1. የግጥም ስራዎች

#### 4.1.1. "አብዮታዊ ግጥሞች" (የግጥም መድብል፣1972)

አብዮታዊ ግጥሞች "ተነሱጭቁኖች"፣ "አብዮት መስክሪ"፣ "ተነሽ እቱ"፣ "እሰይ የምስራች"፣ "እናሸንፋለን"፣ "የአድዋ ድል ተደገመ"፣ "ሴቶች እንተባበር" የሚል አርእስት ያላቸው ግጥሞችን ይዟል፡፡ አብዮታዊ ግጥሞች የ 7 ግጥሞች መድብል ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሦስቱ ተጠንተዋል፡፡

##### 4.1.1.1. "ተነሱ ጭቁኖች"

በግጥሞቹ ስንኞቹ የተወከሉት ወዛደሮች (የጉልበት ሰራተኞች)፣ ሴቶች፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ስርአቱ ጭቆና አደረሰባቸው ብላ ከገለጸቻቸው ውስጥ ሴቷ ላይ ይደርስ የነበረው ጭቆና ደግሞ የባሰ መሆኑን አንስታለች፡፡ በስንኞቿ ሴቶች የነበረውን ስርአት ለማስወገድ መነሳት እና ለመብታቸው መታገል

እንደሚገባቸው አስፍራለች፡፡ መዋረድ፣መገረፍ፣መድከም፣ለሴተኛ አዳሪነት መጋለጥ በግጥሙ ውስጥ በሴቶች ላይ ይደርሱ የነበሩ ጭቆናዎች ማሳያ ተደርገዋል፡፡

ተነሽ ጭቁኗ ሴት

ታገይ ለእኩልነት፡፡(አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣6)፡፡

በማለት ሴቶች እኩልነታቸው እንደተነፈጋቸው ትገልጻለች፡፡ ሴቷ በወቅቱ ይደርስባት የነበረውን ጭቆና ለመገላገል ብሎም የተነፈጋትን እኩልነት ለማስከበር ለአብዮቱ መታገል እንዳለባት በስንኞቿ ሀሳቧን አስፍራለች፡፡ ከስንኞቹ እንደምንረዳውም በወቅቱ የነበረው ስርአት የሴቶችን እኩልነት የማይቀበል ወይም በሌላ አገላለጽ "ሴት ወደ ቤት ወንድ ወደ ችሎት" የሚለውን አባባል የሚደግፍ እንደነበር ነው፡፡ የምወድሽ በዚሁ ግጥም ላይ ስለ እኩልነት ብቻ አንስታ አልጨረሰችም፡፡ በሴቶች ላይ ይደርሱ የነበሩ አካላዊ ጉዳቶችንም ታስረዳለች፡፡

ያኔ እህት ወዝአደሯ

ተገፎ ክብሯ

ተዋርዳ ተገርፋ

ስትደክም ስትለፋ

ነበር ጓዲት፡፡(አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣6)

ሴት ከቤት ወጥታ መስራት የማትችልበት ወቅት እንደነበር ከስንኞቹ ሀሳብ እንረዳለን፡፡ ከቤት ወጥታ መስራትን ለምትሞክር በጉልበቷ እሰራለሁ የምትል ሴት ደግሞ ይደርስባት የነበረውን አካላዊ ጥቃት በስንኖቿ እንዲህ ስትል አስፍራለች፡፡

ተነሽ ወዝአደሪት፣

ታገይ ንቂ ተማሪ፣

መብትሽን እንድትአስከብሪ፣

ከወንድምሽ ጋር ተባበሪ፣

ጭቁንነትሽን አብስሪ፣

የልፋት ዋጋሽን እንድትአገኚ፣

በርቺ እስከመጨረሻ አትቦዝኚ፡፡ ( አብዮታዊ ግጥሞች፣ 1972፣5-6)

የግጥሞቹ ስንኞች እንደሚያስረዱት ሴቷ ለመብቷ መከበር፣ ለእኩልነቷ፣ ከማጀት ወጥታ መስራት እንድትችል፣ መማር እንድትችል የነበረውን ስርአት እንዲወድቅ መታገል እንዳለባት ነው፡፡

## 4.1.1.2. "ተነሽ እቴ"

የምወድሽ በ"አብዮታዊ ግጥሞች" የግጥም መድብል በነበረው ስርአት የተጨቆነው ወዝአደሩ ፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ ፣ከተማሪ እስከ ሰራተኛ ወንዱም ሴቱም ነው ትላለች፡፡ ወደ ትግል የሚገባ ታጋይ ሁሉ ወደ ኋላ ማለት እንደሌለበትም የሚያነሳሱ ሀሳቦችን አስተላልፋለች፡፡ በነበረው ስርአት ሴቶች በይበልጥ ለችግር እየተጋለጡ እንደሆነ ደጋግማ አንስታለች፡፡ በተለይም የገጠር ሴቶች ተወልደው ባደጉበት ቀየ ስራ እንዳያገኙ እየተደረጉ በመሆኑ ወደ ከተማ እየመጡ ለሴተኛ አዳሪነት እየተጋለጡ እንደነበር የግጥሞቹ ስንኞች ያስረዳሉ፡፡

ተነሽ እቴ፣

የቡና ቤቲቱ፡፡

ተሰናጅ ለዘመቻው፣

ይቅር ሽኩቻው፡፡

የአድኃሪያንን ወሬ አትስሚ፣

ቁረጭ አታቅማሚ፡፡

የአረንጓዴውን ዘመቻ ጥሪ፣

ተቀብለሽ ለጓደኞችሽም አብስሪ፡፡(አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣13)፡፡

በግጥሞቿ ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ "በአዳሀሪያን" እየተጨቆነ ነው ብትልም የሴቶች ግን ከሁሉም የከፋ እንደሆነ ደጋግማ ጽፋለች፡፡ መውደቅ እንዳለበት ይፈለግ የነበረው የወቅቱ ስርአት አድሀሪያን ወይም አስመሳይ የሚል ስያሜም በግጥሙ ተሰጥቶታል፡፡

አብዮቱ "የአረንጓዴ ዘመቻ" ተብሎ የተጠቀሰው አብዮት እንዲመጣ ለዘመቻ መውጣት እንጅ ወደ ኋላ ማለት እንደማያስፈልግ ከግጥሙ ስንኞች መረዳት ይቻላል፡፡ ሴቶች ስራ አጥ እንዲሆኑ ስለተደረገ ለቡና ቤት ስራ ተጋልጠዋል፤ የነበረውን ስርአት ለመጣል አብዮቱን መደገፍ እና እኩል መሆናቸውን ማሳወቅ አለባቸው ትላለች፡፡

በየከተማው ከመንከራተቱ፣

ይሻላል ሰርቶ መብላቱ፣

በይ ተነሽ እቱ፡፡

መጠሪያሽ ከሚሆን ሴተኛ አዳሪ፣

ተነሽ እቱ ለስራ ተጣጣሪ፣

ሂጂና ገጠር ስሪ፡፡ (አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣14)፡፡

ከግጥሞቹ ስንኞች እንደምንረዳው ሴቶች እኩልነት ስለተነፈጋቸው ሰርተው መለወጥ አልቻሉም፤በገጠር የሚኖሩ ሴቶች ለድህነት እየተዳረጉ መሆኑን ተከትሎ ወደ ከተማ በመፍለስ ለሴተኛ አዳሪነት እየተጋለጡ መሆኑን ነው፡፡ በከተማ፣ በሴተኛ አዳሪነት ፣በድህነት ከመማቀቅ ለመቅጣት ሴቷ ለመብቷ መቆም እንዳለባት ትናገራለች፡፡ ከዚህ ጭቆና ለመውጣት ወደ ገጠር በመመለስ በስራ መሰማራት ፣እኩልነትን ማረጋገጥ እና እራስን መቻል እንደሚገባት ስንኞቿ ያስረዳሉ፡፡

ተነሽ እቱ እኩልነትሽ ይታወቅ፣

ይቅር ከተማ በድህነት መማቀቅ

ላይ ላዩን ተደሳች መሳይ ውስጥ ውስጡን ከመጨነቅ፣

ቤዳንስ ቤቱ ከመሞላቀቅ፡፡

በየመንገዱ ዳር ከምትቸገሪ፣

ራስሽን ለመርዳት ጣሪ፣

ተነሽ እቴ አትግደርደሪ፡፡(አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣14)፡፡

የነበረው ስርአት ጨቋኝ ህዝቡ ደግሞ ተጨቋኝ መሆኑን በስፋት በገለጻችበት በአብዮታዊ የግጥም መድብል የጾታ እኩልነት እንዳልነበረ፣ ሴቶች ዝቅ ተደርገው የሚታዩበት የስርአቱ ከፍተኛ ጭቆና በሴቶች ላይ የበረታ መሆኑን ገልጻለች፡፡ የጭቆናው መገለጫ ደግሞ የከተማ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት ሆኖ በስንኞቹ ተገልጿል፡፡

ሥጋሽን (ክቡር ገላሽን) ሳትወጅ ቸርችረሽ፣

የሥቃይ ኑሮ  እየኖርሽ፣

እስከመቼ ትዘልቂዋለሽ?፣

ወደሽ አይደለም እቴ፣

ጥሎብሽ ነው ስርአቱ፡፡

ይሰማሽ የበታችነቱ፣

ተነሽ ለእኩልነት፣

ለመጠቀም በአገኘሽው መብት፡፡(አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣14፣)

ከስርአቱ ጭቆና ነጻ ለመውጣት በወቅቱ የነበረውን ትግል መቀላቀል ለወንዱ ብቻ ሳይሆን ለሴቷም አስፈላጊ መሆኑን በግጥም ስንኞቿ አቅርባለች፡፡

### 4.1.1.3. “ሴቶች እንተባበር”

“አብዮታዊ ግጥሞች” የግጥም መድብል ስርአቱ ለማስወገድ ሁሉም ተሳታፊ መሆን እንደሚገባው ስርአቱን በማፍረስ “የወዛደሩን ፓርቲ” መገንባት እንደሚገባ የተሻለው እሱ እንደሆነ “ሴቶች እንተባበር” በማለት 73 ስንኞችን በያዘው ግጥሟ ገልጻለች፡፡ የነበረው

ስርአት ወድቆ የወዛደሩን ፓርቲ ለመመስረት ደግሞ ሴቶች የእኩልነት ዘመቻ ሊያቀነቅኑ ይገባልም እንደሚገባ እና መተባር እንዳለባቸው በስንኞቿ አስፍራለች፡፡

ሴቶች እህቶቸ ተነሱ እንተባበር፣

ከተማ ያለነው እንዲሁ ገጠር፡፡

እኩልነታችን ይታወቅ ሁነን ባንድነት፣

እንታገል ለመብታችን ለነጻነት፡፡ (አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣25)፡፡

ከስንኞቹ መረዳት እንደሚቻለው ስርአቱን ለማስወገድ ከከተማ እስከ ገጠር ያሉት ሴቶች መተባበርን፣ አንድ መሆንን፣ ስለ እኩልነት ማቀንቀንን፣ ለነጻነት መታገልን ይጠይቃል፡፡ለሁሉም ሴቶች እኩል መብት፣ እኩል ነጻነት እንደሚያስፈልግ የምወድሽ የነበረውን ከፋፋይ ስርአት እንዲህ ስትል ትገልጻለች፡፡

እማማ ተነሽ ውጪ ከማድቤት፣

ዓይንሽ አይቃጠል በፊውዳሎች ቤት፡፡

እመቤቷም በቃሽ ማዘዙ ይቅር፣

መታጀብ አበቃ በገረድ ባሽከር፡፡ (አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣25)፡፡

ስትል ለሴቶች የሚሰጠው መብት እና ክብር የሀብት ደረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን ትተቻለች፣ ትነቅፋለች፡፡ ለሁሉም ሴቶች እኩል መብት እና ነጻነት ያስፈልጋል የምትለው የምወድሽ ይህን እኩልነት ለማምጣት መተባበር እንደሚያስፈልግ በግጥም ስንኞቿ ደጋግማ አንስታለች፡፡

ቡና ቤት እህቴም ኑሮ የመረረሽ፣

በሰካራም ጥፊ የበለዘው ፊትሽ፣

ነይ ተባበሪ ታገይ ለመብትሽ

ለፍተሽ እደሪ በጉልበትሽ፡፡(አብዮታዊ ግጥሞች፣1972፣25-26)፡፡

በአብዮታዊ ግጥሞች የቀረቡት ዋና ሀሳቦች የነበረውን ስርአት ጨቋኝነት የሚተቹ ቢሆኑም በስርአቱ ከሁሉም በላይ እየተበደሉ ያሉት ሴቶች መሆናቸውን የጻፈችበት ነው፡፡ የሴቶች እኩልነት ይከበር፣ሴቶች ጾታን መሰረት ያደረገ ተጽእኖ ሊደርስባቸው አይገባም፣ እኩል የስራ እድል ሊፈጠርላቸው ይገባል የሚሉ አንኳር ጉዳዮችን ደጋግማ በግጥሞቿ አንስታለች፡፡

## 4.1.2. "ዋጊኖስ የግጥም መድብል" ( 2003 ዓ.ም.)

ዋጊኖስ የግጥም መድብል በ 2003 ዓ.ም.የታተመ 104 ግጥሞችን የያዘ ነው፡፡ ግጥሞቹ የተለያየ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ የተወሰኑትን በማሳየት የምወድሽ በግጥሞቿ ልታስተላልፍ የፈለገችውን ማጠንጠኛ ሀሳብ ተለይተዋል፡፡ ዋጊኖስ ከስያሜው ስንነሳ "ዋጊኖስ" በሰሜን ሸዋ ይፋት ውስጥ የሚበቅል ለመድሀኒትነት በተለይም ለቁስል የሚያገለግል እጽዋት ነው"፡፡ (ዋጊኖስ፣2003፣57)፡፡

በዚህ የግጥም መድብል በርካታ ማህበራዊ ጉዳዮች እና ህጸጾች የተነሱ ሲሆን ስለ ሀገር እና ሴት፣ ሰላምና ፍቅር፣አንድነት የግጥሞቹ ማጠንጠኛ ሀሳቦች ሆነዋል፡፡ ከ 104 ግጥሞች ውስጥ ሦስቱ ግጥሞች እንደሚከተለው ተጠንተዋል፡፡

### 4.1.2.1. "አይጣል"

የምወድሽ በ"ዋጊኖስ" የግጥም መድብል "አይጣል" የሚል ርእስን የያዘው ግጥም 9 ስንኞች ይዟል፡፡ የሴቶችን ልፋት እና ጥረትን የሚያሳይ ሀሳቦችን ገልጻበታለች፡፡ ስንኞቹ እንደሚያስረዱት ብዙ ውጣውረድን ያሳለፈች ሴት መጨረሻዋ ስኬት እንደሚሆን ነው፡፡መውደቅ መነሳት፣መውጣት መውረድ በሕይወት የሚያልፉ መሰናክሎች እነዚህን ማለፍ ደግሞ በኢኮኖሚ ማደግ ፣በትምህርትም የሚፈልጉበት ደረጃ መድረስ ፣ራስን መቻል የስኬቶቹ ማሳያዎችም ተደርገው ቀርበዋል፡፡

ልክ እንደዝንጀሮ ቧጥጬ ቧጥጬ ፣

ለማደግ ታግየ ራሴን ለውጬ፣

ወጥቸ ወርጀ ጥሬ ግሬ፣

ሌት ተቀን ቧችሬ ቧችሬ፣

ሰው ሆንኩ ተውተርትሬ፣

ቆምኩኝ በሁለት እግሬ፡፡(ዋጊኖስ፣2003፣50)፡፡

የግጥሞቹ ስንኞች እንደሚያስረዱት የምወድሽ የራሷን ሕይወት የገለጸችበት ይመስላል፡፡ምክንያቱም ከየምወድሽ የህይወት ታሪክ እንደምንረዳው የምትፈልገውን የጋዜጠኝነት እና የድርሰት ሙያ ለማግኘት ፈታኝ ነገሮችን አልፋለች፡፡ የእሷ ሕይወት ደግሞ የብዙ ሴቶችን ሕይወት የሚያንጸባቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ብዙ ውጣውረዶችን ማሳለፏን እና መጨረሻዋ ስኬት መሆኑን ባነሳችበት በዚህ ግጥም የብዙ ሴቶች ጥረት ለስኬት የሚያበቃ እንደሚሆንም የሚያስረዳ ነው፡፡ ሰው የማንንም ድጋፍ ሳይፈልግ ለመቆም ሁለት እግር እንደሚያስፈልገው ሁሉ ራስን የሚፈልጉበት ደረጃ ማድረስም ከዚሁ ጋር የሚወዳደር እንደሆነ በስንኞቹ አስረድታለች፡፡

### 4.1.2.2. "ሴት"

"ሴት" 13 ስንኞችን የያዘ ግጥም ነው፡፡ በዚህ ግጥም ሴት የብዙ ነገር መሰረት መሆኗን በስንኞቹ ተገልጸዋል፡፡ ሴት ለመኖር ፣ዘር ለማስቀጠል፣የዘላለም የሕይወት ቅኔ፣የሰውን ልጅ ያሕል ፍጡር በማህጸን የምታበቅልና ደምና ስጋዋን ቆርሳ የምትሰጥ መሆኗን በግጥሞቿ አስፍራለች፡፡ በግጥሙ ስንኞች መኖር ትርጉም የሚኖረው ሴት ስትኖር መሆኑን ገጣሚዋ እንዲህ ትላለች፡፡

ፍሬ ትርጉም ያለው - የመኖር ብያኔ፣

የዝንተ ዓለም ሚስጥር-ህይወታዊ ቅኔ፡፡

ግሩም ትርኢቱ- የተፈጥሮ ጉዞ፣

ባንቺው ተጸንሶ- ባንቺ ሆድ ተረግዞ፡፡

በማህጸንሽ በቅሎ-ማህጸንሽን ፈልቅቆ፣

ከውስጠኛው ደምሽ-ሥጋሽን ቦጭቆ፡፡

ታሪካዊ ሂደት- ተፈጥሮ ስሪቱ፣

ባንቺ ነው ድምቀቱ- ልደቱ ውበቱ፡፡(ዋጊኖስ፣2003፣61)፡፡

ከግጥሙ ስንኞች እንደምንረዳው ከጽንሰት እስከ ውልደት ሴት የምታሳልፋቸው ተፈጥሮአዊ ጉዞዎች ተአምራዊ መሆናቸውን የዝንተአለም ሚስጢር መሆናቸውን ነው፡፡ ሕይታዊ ቅኔ የተባለችው ሴት ሰው ለተባለውን ፍጡር ተፈጥሮአዊ ስሪቱን የምትከውን መሰረት መሆኗን የምወድሽ በስንኞቿ ገልጻለች፡፡ ከዚህ ተፈትሮአዊ ሂደት በተጨማሪ ገመናን ደባቂ ነሽ ስትልም ሴትን እንዲህ ትገልጻታለች፡፡

ገመናን ደባቂ- አድርገሽ በጉያ፣

ትልቋ ዋርካ- እናት መጠለያ፡፡

የሀገር መመሰያ- የሁሉም ገበያ፣

የፍቅር ተምሳሌት- ትውልድ መቀጠያ፣

ቁንሮ ነሽ ስቲቷ- የለሽም መተኪያ፡፡(ዋጊኖስ፣2003፣61)፡፡

የምወድሽ በእነዚህ ስንኞች ሴት ብዙ ነገር ናት ትላለች፡፡ ሴት እናት፣መጠለያ ዋርካ፣ትውልድ መቀጠያ፣የሀገር መመሰያ ናት ብላለች፡፡ ሴት እንደ ሀገር መተኪያ የሌላት መሆኗን ከላይ የቀረቡት ስንኞች ያስረዳሉ፡፡

### 4.1.2.3. “ዋጊኖስ”

የግጥም መድብሉ መጠሪያ ሆኖ የቀረበው “ዋጊኖስ” 22 ስንኞችን የያዘ ሲሆን ዋጊኖስ በሰሜን ሸዋ ዞን ይፋት ውስጥ የሚበቅል ለመድሀኒትነት በተለይም ለቁስል የሚያገለግል እጽዋት መሆኑን የምወድሽ በግጥሙ መጨረሻ ላይ ሰፍሯል፡፡

“ዋጊኖስ” ሰላናምና ፍቅርን እጦት የሚናውዙ የታመሙ እናት የተወከሉበት ስንኞችን የያዘ ግጥም ነው፡፡ የግጥሙ ስንኞች ከህመማቸው መፈወስ የሚፈልጉ ሴት አዛውንትን ወይም በእድሜአቸው የገፉ እናትን ሀሳብ የሚንጸባርቅ ነው፡፡ የምወድሽ “በዋጊኖስ” ግጥም ስንኞች የሚፈውሳቸው የሚያክማቸው መድሀኒት ባለማግኘታቸው ወደ ሞት የተቃረቡ እናትን ሀሳብ እንዲህ ገልጸበታለች፡፡

ሰላና ፍቅሬን የሚመኝ አጥብቆ፣

በጥብጦ የሚያጠጣኝ ቀጥቅጦ እንቆቆ፡፡

እንድገላገልም ከአጓጉል ወጌሻ፣

ሊሆነኝ የሚችል ፍቱን መታሻ፣

ዋጊኖስ ነውና ለኔ መፈወሻ፣

ይህን የሚያደርግ ብፈልግም ብሻ፡፡

ሁሉን ተቋቁሞ ችሎ 'ሚከላ፣

አላገኘሁም የሚያመጣ መላ፣

አለችኝ እማማ በደከመ ነፍሷ፣

በሰለለ ድምጿ፣

በጣም ቀስ ቀስ ቀስ ብላ፡፡(ዋጊኖስ፣ 2003፣57)፡፡

በነዚህ የግጥም ስንኞች ጸሀፊዋ ኢትዮጵያ በእማማ ወይም በሴት በመወከል አቅርባለች፡፡ ሴት የሀገር መወከያ መሆኗንም በስንኞቹ መረዳት ይቻላል፡፡ ቀደም ብሎ "ሴት" በሚለው ግጥም ከቀረቡት ስንኞች ጋር ተቀራራቢነት ይዘት ያለው ይህ ግጥም እና ስትቸገር ልጆቿን እንደምትጠራው ሁሉ ኢትጵያም መፈወሻ መድሀኒት ፍለጋን ልጆቿን ትጣራለች የሚል መልእክትም የያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ በ"ዋጊኖስ የግጥም መድብል" ሴት በብዙ መልኩ ተገልጻለች፡፡

## 4.2. የአጭር ልቦለድ ስራዎች ትንተና

### "የባከነ ጊዜ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች" (1982 ዓ.ም.)

የምወድሽ አብዮታዊ ግጥሞችን ባሳተመች አስረኛ አመት ላይ በ 1982 ዓ.ም. "የባከነ ጊዜ እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች" አሳትማለች፡፡ ለህትመት ከበቁት የግል ድርሰቶቿም ሁለተኛ ድርሰቷ ነው፡፡ የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም 8 አጫጭር ልቦለዶችን ይዟል፡፡ በዚህ

አጭር ልቦለድ የቀረቡ ታሪኮች ሁሉም በሴት እና ወንጀል ነክ ጉዳዮች ያተኮሩ መሆናቸውን ተከትሎ ሁሉም ትንታኔ ተደርጎባቸዋል፡፡

### 4.2.1. "አናጋው"

የምወድሽ በባከነ ጊዜና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች በእያንዳንዳቸው ታሪኮች ውስጥ የተሳሉ ዋና እና ረዳት ገጸባህሪያት በውስን መቼት በአንድ ነጠላ ታሪክ አጣፍጣ አቅርባለች፡፡ እያንዳንዳው ያጠነጠኑበትን ዋና ጉዳይ ለመረዳት እና ለማብራራት ያመቹ ዘንድ ከታሪኩ የሰፈሩ ሀሳቦችን በማጣቀስ እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

"አናጋው" አጭር ልቦለድ በሙስና ዙሪያ የሚያጠነጥን ታሪክ ነው፡፡ አናጋው ታሪኩን እስከመጨረሻው ይዞ የሚዘልቅ ዋና ገጸባህሪ ሲሆን በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት የስራ ሀላፊ ነው፡፡ በስራ ሀላፊነቱ ድሀውን ህዝብ ከማገልገል ይልቅ ሀብታሙን ብቻ ማልገልን የሚወድ "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚል መርህን የሚከተል ነው፡፡

አናጋው በስሩ ያሉ ሰራተኞች በወቅቱ ክበብ ተብሎ በሚጠራ የሰራተኛ ማህበር እንዲደራጁ አይፈቅድም፡፡እንዲማሩም አይፈልግም ምክንያቱም ከተማሩ እና ከተደራጁ ስልጣኔን ይወስዱብኛል የሚል የግል አመለካከት አለው፡፡ በገንዘባቸው ለሚሄዱ(ጉቦ ለሚሰጡ) ግን በወቅቱ የነበረውን የትኛውን ህግ በመጣስ ጉዳያቸውን ይፈጽምላቸዋል፡፡

> አናጋው የለመደውን ጉራ ጀመረ፡፡ብዙ ጊዜ ስራ እንደሚበዛበት በዚህ አብዮት ውስጥ ስላደረገው አስተዋጽኦ ሌላም ሌላም ጨማምሮ ማውራት ይወዳል፡፡ምላሱም ንቃተ ህሊናቸው ባልዳበረ ግለሰቦች አካባቢ ያስሞግሰዋል፡፡ አስቴርንም በወሬው ስቧታል፡፡በተለይም ጉዳይዋን ወዲያ ወዲህ ብሎ እንደሚፈጽምላት ሲነግራት የጠየቃትን ለመፈጸም አልተግደረደረችም፡፡ የወይዘሮ ትንቢለል የውስኪ ግብዣ ለአናጋው ድንፋታ እገዛ አድርጎለታል፡፡ በዚህም በዚያ ሰብኮ አስቴርን ስላሳመናት ሰሞኑን ተገናኝተው ለመዝናናት ቀጠሮ ተለዋወጡ፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች፣1982፣14)፡፡

ታሪኩ እንደሚያስረዳው አናጋው የተሰጠውን የሕዝብን ሀላፊነት በአግባቡ ከመወጣት ይልቅ በጉቦ እና እጅ መንሻ ማገልገል የሚቀናው ነው፡፡ በዚህ አጭር ታሪክ አንድን ስራ ለማናከወን ጉቦ በመቀበል እና የሴቶችን ገላ መደራደሪያ በማድረግ የሚጠቀሙ ብዙ

መሆናቸውን በአናጋው ገልጻለች፡፡በመጨረሻ ግን ማንም ሰው ከህግ በታች እንደሆነም በታሪኩ መጨረሻ ላይ ለማሳየት ሞክራለች፡፡አናጋው እና መሰሎቹ ወደ እስር ሲወረወሩ አሳይታለች፡፡

> አናጋው ቀደም ብሎ ሄዶ ከነወ/ሮ ትንቢለል ጋር ሲጫወት ተስፋየ መጣ፡፡ ከአስቴር እና ወ/ሮ ትንቢለል ጋር አስተዋወቀው፡፡ጉዳያቸውን የሚፈጽምላቸው እሱ መሆኑን እና የቀበሌ ዋና ጸሀፊ መሆኑን ጭምር ገለጸላቸው፡፡ቀደም ሲል ያዘጋጀውን ጽሁፍ ለአናጋው አስረከበው አናጋው አንገቱ ላይ ተጠምጥሞ ደስታውን ገለጠለትና ሺ ብሩን ጠቅለል አድርጎ ተስፋየ ኪስ ከተተው፡፡ሁለት ሰዎች ከተቀመጡበት ተነስተው እጅ ወደላይ አሏቸው፡፡ተስፋየ እጆቹን አነሳ አናጋውም እንደዚሁ፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች፣1982፣18-19)፡፡

### 4.2.2. “ወይ ሀገር”

“ወይ ሀገር” አጭር ልቦለድ በስደት ህይወት ዙሪያ ያጠነጠነ ታሪክ ነው፡፡ የታሪኩ ዋና ገጸባህሪ “አየለች” “ቤንዚን እንደ ውሀ ወደ ሚፈልቅበት” ሳውድ አረቢያ የሄደችው ገና በ 18 አመቷ ነው፡፡ በሰው ሀገር በቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ በምታገኘው ገንዘብ ቤተሰቦቿን ትረዳለች፡፡ ከ 6 አመት የአረብ ቆይታ በኃላ ወደ ኢትዮጵያ ትመለሳለች፡፡

አየለች ስትመለስ የቆዳዋ ቀለም በመዋቢያ ተቀይሯል ፡፡እሷን ያዩ የቀየው ሰዎችም እና የጓደኞቿ ምኞትም ከመማር ይልቅ እንደሷ መሆን አረብ ሀገር መሄድ ሆነ፡፡በልቦለዱ ስሟ ያልተገለጸው የአየለች ጓደኛም ስደትን ከጥሩ እድል ጋር በማገናኘት እንዲህ ትናገራለች፡፡

> ጓደኛየ ዓረብ ሀገር ሄዳ እንዲህ መምነሽነሿ እኔን መንፈሳዊ ቅናት አሳደረብኝ አንድ ቀን እኔም ጥሩ እድል እንደሚገጥመኝ አስብ ጀመረ፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች፣1982፣23)፡፡

አየለች ወደ ሀገሯ ስትመለስ ትዳር ይዛለች ለመባል ከአንድ አረብ ጋር ነው የመጣችው፡፡ በዚህም ቤተሰቦቿም ተደስተዋል የአካባቢው ሰውም ልጅ እንደ እሷ ነው ማለቱን ተያይዞታል፡፡አየለች ግን እንደ ባል ያስተዋወቀችው ሰው ህጋዊ ባል አልነበረም ይህንም ለጓደኛዋ እንዲህ ስትል ትነግራታለች፡፡

ይኸውልሽ ይሄ በቀደም ያየሽው ሰባተኛ ባሌ ነው ፡፡ገና ከዚህ እንደሄድኩ የተቀጠርኩት አንድ ቴምር ነጋዴ ቤት ነበር፡፡እጅግ ይንከባከበኝ ነበር ለካ አረቡ ወዶኝ ኖሮ ባለቤቱን እየተደበቀ እዚያው ቤት ውስጥ ጉድ ጉድ ማለት ጀመርን፡፡ ገንዘብም አንበሸበሸኝ እኔም ሀገሬን ትቸ ገንዘብ ለማግኘት ደሀ ቤተሰቦቸን የመርዳት ሀላፊነት ለመወጣት የተሰደድኩ በመሆኔ ለጊዜው ተደስትኩ፡፡ በዚህ መልኩ ሰባት ሰዎች አግብቻለሁ፡፡ምክንያቱም ይሄን ካላደረኩ ቤተሰቦቸን መርዳት ስለማልችል፡፡ ሌሎች ከዚህ በላይ ያገቡም አይጠፉም፡፡ የተቀጠርኩባቸው ቤቶች ባለቤቶች በድብቅ ስለማስተናግዳቸው እንጂ ሕጋዊ ባል አላገባሁም አለችኝ፡፡ (የባከነ ጊዜ እና ሌሎች ፣1982፣24-25)፡፡

ታሪኩ እንደሚያስረዳው ሴቶች ገና ያለ እድሜያቸው ትምህርታውን ትተው ወደ ውጭ ሀገር እንደሚሰደዱ ነው፡፡ቤተሰብም ስለልጆቻቸው ከሀገር መውጣት እና ብር ማግኘት እንጅ ብሩን በምን መንገድ እንደሚያመጡት ጉዳታቸው አይገባቸውም፡፡ወደ አረብ ሀገር የሚሰደዱ ሴቶች ከላይ ደስተኛ የሚመስሉ ግን ደግሞ ውስጣቸው የተጎዳ እና ጾታዊ ጥቃት የሚደርስባቸው ፣መከራና ስቃይ የሚፈራረቅባቸው መሆኑን ደራሲዋ በአየለች ታሪክ አስረድታለች፡፡

ያለትዳር መኖር እና መወስለት ያለውን ስነልቦናዊ ጫናም ከጥቅሱ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ መልኩ ለገንዘብ ሲባል የስብእና መርከስን ያሳያል፡፡ በተደጋጋሚ ማግባት እና ባለትዳር የሆኑ ወንዶች ቅምጥ በመሆን ከባህል ያፈነገጠ ስራ የሚሰራበት የስደት ኑሮን አሳይታበታለች፡፡ ለገንዘብ ሲባል ማድረግ የማይገባን እስከማድረግ የሚደረስበትን ስደት ሕይወት በአየለች ሕይወት የምወድሽ አሳይታለች፡፡

በታሪኩ ዋና ገጸባህሪዋ አየለች በአረብ ሀገር ያሳለፈችውን እንግልት ቀስ በቀስ ለጓደኛዋ ትነግራታለች፡፡እውነታው ከላይ እንደሚታየው እንደሚነገረው እንዳልሆነ የስደትን አስከፊነትም ሁሉ ዘርዝራ ትናራለች፡፡ገንዘብ ለማግኘት ከተለያዩ ወንዶች ጋር ያደረገችው ጾታዊ ግንኙነት ለህመም እንደዳረጋትም ጭምር የስደት ኑሮ አስከፊነትን ታጫውታታለች፡፡ ውጫዊ ሰውነቷ ጤነኛ ቢመስልም ውስጧ ግን በብዙ መልኩ ታሟል እና ሌሎች እህቶቿ የስደት አስከፊነትን እንዲረዱትም ትመክራለች፡፡

ያላየ በወሬ ብዙ ይመኛል በብልጭልጭ ተራ ነገር ይደለላል በውጭ ሀገር ኑሮው ርካሽ ሰው አዋቂ ልዩ ነገር ይመስለዋል ግን አይደለም፡፡ከሀገር ርቀው ሲሄዱ ታዛዥነት እንጅ አዛዥነት አይገኝም፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች ፣1982፣28-29)፡፡ስትል አየለች ለጓደኛዋ ትነግራታለች ፡፡

የምወድሽ በዚህ አጭር ልቦለድ ላይም የስደት አስከፊነትን አሳይታለች ለስደት እየተጋለጡ ያሉት ደግሞ ሴቶች መሆናቸውን ትኩረት እንደሚሻ በታሪኩ ተናግራለች፡፡ ሴቶች በሀገራቸው መማር፣በሀገራቸው ትዳር መመስረት፣በሀገራቸው ስራ መስራት እንጅ ለግዞት መዳረግ እንደሌለባቸው በታሪኩ አስረድታለች፡፡

### 4.2.3. “እንደዚህ ነው?”

“እንደዚህ ነው ?” አጭር ልቦለድ ታሪኩ በፍቅር መከዳት ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡ በ“ገነት” እና “ጣሰው” ፍቅር ላይ የሚያተኩረው አጭር ልቦለዱ በመጨረሻም “ጣሰው” በፍቅረኛው “ገነት” ላይ በቃሉ አለመገኘትን በማሳየት የሚቋጭ ነው፡፡በዚህ አጭር ልቦለድ ገነት የአስር አመት የፍቅር ታሪኳን የምትነግርበት ሲሆን ባሳለፈችው የፍቅር ታሪክ የገጠሟት ወንዶች ሁሉ “አስመሳዮች”፣ “የማይታመኑ” እንደነበሩ ለጓደኛዋ ተዋበች ትናገራለች፡፡

ገነት ከብዙ ወንዶች ጋር ካሳለፈችው ያልተሳካ የፍቅር ግንኙነት በኋላ ነው ከጣሰው ጋር የተገናኘት፡፡ጣሰው ከምታውቃቸው ወንዶች ሁሉ የተለየ ነበር፡፡በጣም ተቀራርበዋል ጣሰው ለገንዘቡ የማሳይሳሳ እንደፈለገች የሚያዝናናት ደግ በመሆኑ ፍቅራቸው እንዲዘልቅ ጾምና ጸሎቱን ይዛለች፡፡

ከጣሰው ጋር እንደሚጋቡ እና የቤተሰቡን መቸ ነው የምታገቢው ጥያቄ የምትመልስበት ወንድ እንደሆነ እርግጠኛ እየሆነች ነው፡፡

> ፍቅራቸው ዕለት በዕለት እየዳበረ በመሄዱ ተዋበች ደግና ኃብታም ፍቅረኛ ማግኘቷን ለቤተሰቦቿ ነግራ ውስጥ ውስጡን የጋብቻ መሰናዶዋን ጀምራለች፡፡እናትየዋም “ልጅዎን ይስጡኝ” ተብለው የሚጠየቁበትን ዕለት በናፍቆት ይጠባበቃሉ፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች ፣1982፣ 33)፡፡

ተዋበች ደስተኛ የሆችበት የፍቅር ጉዞዋ ደግና ሀብታሙ ፍቅረኛዋ ጣሰው ግን ከቀን ወደ ቀን በማታውቀው ምክንያት ከሷ እየራቀ መጣ፡፡ስልክ አይደውልም እንደለመደችው በየቀኑ

ልታገኘውአልቻለችም፡፡ የጣሰው መጥፋትን ተከትሎ የመንግስት ድርጅት የሂሳብ አጣሪ ወይም ኦዲተር ሆኖ ከሚሰራ “አባተ” ከሚባል ሰው ጋር በተዋወቀች እለት ተዋበች ስለ ጣሰው ልትቀበለው የሚከብድን እውነታ አወቀች፡፡

በዚህ ታሪክ ላይ ጸሀፊዋ የምወድሽ በፍቅርም ሴቶች ተጎጅ መሆናቸውን አሳይታለች፡፡ ህብረተሰቡም ትዳር መያዝን ለሴት ልጅ ግዴታ አድርጎ እንደሚመለከት እና በዚህም ሴቶች ከማይወዱት ፣በውል ማንነቱን ከማያውቁት ሰው ጋር በሚጀምሩት ግንኙነት የሰመረ ሕይወት እንደማይገጥማቸው የምወድሽ በታሪኩ ለማሳየት ሞክራለች፡፡ ተዋበች ልታገባው የተመኘችውን ጣሰውን ምን እንደሚሰራ ባለማወቋ ፣ፍላጎቷ የቤተሰቦቿን “አግቢ” የሚል ተደጋጋሚ ጥያቄን ለመመለስ ብቻ መሆኑ መጨረሻው እንዳይሰምር እንዳደረገው ታሪኩ ያስረዳል፡፡

ለተዋበች ደግና ሀብታም ሆኖ የቀረባት “ጣሰው” በአንድ የመንግስት ድርጅት ሂሳብ ሰራተኛ እንደነበር እና የኦዲት ጉድለት እንደተገኘበት አዲስ ከተዋወቀችው “አባተ” ሰማች፡፡የጣሰው በድንገት መጥፋትም ከሰራው ወንጀል ጋር ተያይዞ መሆኑን ተከታዩ የታሪኩ ክፍል ያስረዳል፡፡

> አባተ ለልጁ ሳንቲም ሰጠ እና ፖሊስ ጋዜጣን ገዛ፡፡በጋዜጣው ሶስተኛ ገጽ ላይ የሰፈረውን የወንጀል ዜና ሲቃኝ እሱ ይሰራበት ከነበረው መስሪያ ቤት ገንዘብ አጉድሎ ሂሳቡን መርምሮ ጉድለቱን ያረጋገጠበት ሰው ፎቶግራፍ አየ፡፡በ 10 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰኑን የሚገልጽ ዜናና ጉርድ ፎቶ፡፡ ተዋበችም ጋዜጣውን አየችው እምነት አጉዳዩ ጣሰው ነው፡፡ ተዋበችም ለካ እንደዚህ ነው ብላ ከተቀመጠችበት ወንበር ተንሸራታ ወለሉላይ በጀርባዋ ተንጋላ ቀረች”፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች ፣1982፣ 41-42)፡፡

“እንደዚህ ነው?” አጭር ልቦለድ ታሪክ እንደሚያስረዳው ሴቶች ላይ የሚደርሱ ልማዳዊ ጫናዎች ለምሳሌ ሴት ልጅ ቶሎ ትዳር መያዝ አለባት የሚል እና መሰል ቤተሰባዊ ጫናዎች ሴትን ልጅ ወዳልተፈለገ መስመር ሊስያገቡ እንደሚችሉ ነው፡፡ይህም ሴቶች ዘላቂ ወዳልሆነ የፍቅር ግንኙነት እንዲገቡ፣በፍቅር ተጎጅ እንዲሆኑ፣ ለማህበራዊና ስነልቦናዊ ጫና እንዲጋለጡ ያደርጋዋቸል የሚል ጭብጥን ይዟል፡፡እንዲሁም ሙስናና ወንጀል በዚህ አጭር ልቦለድ “እምነት አጉዳዩ ጣሰው” ተብሎ ቀርቧል፡፡

### 4.2.4. “እነግረዋለሁ”

“እነግረዋለሁ” አጭር ልቦለድ በባህላዊ ተጽእኖ ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ የፍቅር ጥያቄ ለማቅረብ የማህበረሰቡ ወግና ልማዱ ተብትቦ የያዛት ዋና ገጸባህሪ የሚሰማትን ስሜት ለወደደችው ወንድ ለመናገር የምታሳልፈውን ስቃይ የሚያሳይ ታሪክ ነው፡፡የሴትነት ወጉን ትታ ለወደደችው የስራ ባደረባዋ ፍቅሬን ብነግረው የምፈልገውን ምላሽ ባይሰጠኝስ ብላ ፍቅር ፈሪ ያደረጋት ገጸ ባህሪ፡፡

ዋና ገጸባህሪዋ “ሰናይት” በፍቅር ያበደችለት እንቅልፍ የነሳት ስራ እንዳትሰራ ያደረጋት ለስራ ባልደረባዋ ግርማን የሚሰማን እንኳን አውጥታ ለመናር ድፍረት አላገኘችም፡፡ ሰናይት ለግርማ የሚሰማትን ፍቅር ለመናገር ከዛሬ ነገ ሁሌም “እነግረዋለሁ” እያለች ቀጠሮ ብትይዝም አልተሳካላትም፡፡ ለመናገር ባሰበችበት ቀን ሁሉ የሴትነት ባህሪዋ ድፍረት አሳጣት፡፡ከዚህ ሁሉ በኋላ አንድ ቀን አንድ ሀሳብ መጣላት ከሰው መልእክት እንደተላከለት አድርጎ ቀጠሮ መያዝና ከስራ ውጭ አግኝቶ ለሱ ያላትን ፍቅር መናገር፡፡ግን ማድረግ አልቻለችም፡፡

> ሰናይት ቀኑን ሙሉ ሲያስፎክራት የዋለው ወኔዋ ትቷት ሄዶ የሴትነት ባህሪዋ አላናግራት አለ፡፡ “ሌላ ጊዜ እነግርሀለው” ብላ ተሽኮረመመች፡፡ በሁኔታው ግራ የተጋባው ግርማም አስገድዶም ሆነ ተለማምጦ መልእክቱን መስማቱ ተገቢ አለመሆኑን በመረዳት “እሺ” አላትና ሌላ ወሬ ጀመረ፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎች ፣1982፣47)፡፡

ከጥቅሱ እንደምንረዳው ሰናይት ፍቅሯን ለመግለጽ የባህል ተጽእኖ ያደረሰባትን ጫና ነው፡፡ አሁንም በግርማ ፍቅር እየተሰቃየች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላት ማህበራዊ ግንኙነትም እየቀዘቀዘ መጣ፡፡ከግርማ ጋር ያላትን ግንኙነት እያጠናከረች ብትመጣም ለሱ የያዛትን ፍቅር ግን መናገር አልቻለችም፡፡

ፍቅሯን ተናግራ የሱን ስሜት ባትረዳም ከስራ በኋላ በመገናኘት፣አብሮ በማምሸት ግንኙነታቸውን አጠናከረች፡፡ ከዚህ በኋላ ነበር የሁለቱ ግንኙነት ወደ አልጋ ያመራው፡፡እንደዚህ መሆኑ ለሰናይት ጥሩ አጋጣሚ መሰላት፡፡ለግርማ ግን አብሮ ከማደር የዘለለ ስሜት አልነበረውም፡፡

ከዛሬ ነገ እነግረዋለሁ የምትለው ለወደፊት የትዳር ጓደኛ አድርጋ የተመኘችው ግርማ ግን በአንድ አጋጣሚ ባለትዳር እና የልጅ አባት መሆኑን አወቀች፡፡ ከዛሬ ነገ እነግረዋለሁ ያለችው ፍቅርም ቅዠት ሆኖ ቀረ፡፡ታሪኩን በዚህ የቋጨችው ጸሀፊዋ  አጽንኦት መስጠት የፈለገችው ሴት ልጅ ፍቅር እንኳን ሲይዛት ደፍራ መናገር እንደማትችል ነው፡፡

ሴት ልጅ የምታድገው የሴት ልጅ ባህሪ ወግ በሚባል አጉል ልማድ ተተብትባ መሆኑን ባሳየችበት በዚህ አጭር ልቦለድ የባህል ተጽእኖ በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጫና ነው፡፡ ሴት ሁሉንም ማድረግ እንደምትችል ባሳየችበት ታሪክ ከባህል ተጽእኖ መውጣት እንደሚያስፈልግም በታሪኩ ጭብጥ አድርጋ አቅርባዋለች፡፡

### 4.2.5. "የባከነ ጊዜ"

የምወድሽ ለአጭር ልቦለዶች ስብስቧ መጠሪያ የሰጠችው "የባከነ ጊዜ" አጭር ልቦለድ የሴት ልጅ የፍቅር ምርጫን የሚከለክል ታሪክ ላይ የሚያጠነጥን ነው ፡፡የባከነ ጊዜ "በስለት" የተወለደች ለቤተሰቡ ብቸኛ የሆነች ልጅን ታሪክ የያዘ ነው፡፡ልጅቷ ገና ተማሪ ሳለች በቤተሰቡ ይመጥናል ወይም በወቅቱ አጠራር "ባላባት" ለሆነ ሀብታምን እንድታገባ የተወሰነባት ናት፡፡

የ"ስለት" ልጅ የሆነችው "ደብሪቱ" እና "ዓለሙ"(ጩኒ) የታሪኩ ዋና ገጸባህሪያት ናቸው፡፡ የስለት ልጅ እና የባለሀብት ልጅ የሆነችው ደብሪቱ እና የእነደብሪቱ አገልጋይ ከሆኑ ደሀ እናት የተወለደው ዓለሙ በፍቅር ወድቀው የሚያሳልፉትን ፈተና የሚያሳይ እና የደብሪቱ የሕይወት ጉዞ ላይ የሚያጠነጥን ታሪክ ነው፡፡

ሁለቱ አብረው ያደጉ አብረው የሚማሩ ወጣቶች ነበሩ፡፡በዚህ መሀል በሁለቱ መካከል የፍቅር ስሜት ተፈጠረ እና ተዋደዱ፡፡የሁለቱን መዋደድም የደብሪቱ ቤተሰቦች ሰሙ፡፡ ደብሪቱ እና ዓለሙ ቢዋደዱም "የሀብታም ልጅ እና የድሀ ልጅ በጋብቻ መተሳሰር አይችሉም" የሚል አመለካከት ያላቸው የደብሪቱ ቤተሰቦች ከዓለሙ ጋር መለያየት እንዳለባት በቤተሰብ የመጣውን "የባለአባት" ልጅ ማግባት ግዴታዋ እንደሆነ ነገሯት፡፡

በሁለቱ መካከል ግንኙነቱ እየጠነከረ ሄዶ የታሰበው ቀርቶ ያልታሰበው ሆነ፡፡ደብሪቱ አረገዘች ይህም የሁለቱን ግኝኙነት ለማስቀጠል ያግዘኛል ብላ በማሰብ ለእናቷ ተናገረች፡፡

ዓለሙ አልሽኝ ዓለሙ ይጥፋና ይሂ ምናምንቴ እሱ ነው ለካ ጠላቴ የኔን ትርፍራፊ በልቶ ጉድ ያደረገኝ፡፡ደግሞ እንጋባለን በይ የምን ጋብቻ አመጣሽብኝ እናቱን ጠርቶ አባቱን የማይደግም የኔ አማች አይሆንም፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣62-63)፡፡

የሁለቱን ጋብቻ የፈቀደ ቤተሰብ ባይኖርም ደብሪቱ ከዓለሙ ያረገዘችውን ልጅ ወለደች፡፡ቤተሰቦቿ ግን ከዓለሙ እንዳትገናኝ እና ልጅ መውለዷ ማንም እንዳይሰማ አደረጉ፡፡ የደብሪቱ እናት ልጃቸውን በማግባባትም ሚስጥራቸው እንዳይሰማ ልጁንም ለጉዲፈቻ ተሰጥቶ እንዲያድግም ከመኖሪያቸው ራቅ ወዳለ ቦታ ለአሳዳጊ ሰጡት፡፡

በትምህሩ ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሰው ዓለሙም ከደብሪቱ ጋር የተግባቡትን የትዳር ቃል ለመፈጸም ቢፈልግም አልቻለም፡፡ደብሪቱ ጸባይዋ ተቀይሯል፡፡ ትጠጣለች፣ ትቅማለች፣ ታጨሳለች ውሎና አዳሯ በቅርብ ካወቀቻቸው ጓደኞቿ ጋር ጭፈራ ቤት ሆነ፡፡ጸባይዋ መቀየሩን ያወቀው ዓለሙ ብዙ ቢጥርም ሊሳካለት ባለመቻሉ ሌላ ትዳር መሰረተ፡፡ደብሪቱ የልጅነት ህልሟ ዓለሙን ማግባት ባለመቻሏ ከሌላ ወንድ ጋር ፍቅር መጀመር እንጅ መጨረስ አልቻለችም፡፡

> ቁጭት የባከነ ጊዜን አይመልስም እንጅ አንዳንዴ መኝታዋ ላይ ሆና የዓለሙን የልጅነት ፍቅረኛዋን ስታስበው ድህነቱ ይጋባ ይመስል ከሱ መቆራረጧ በልጅነት ወልዳው ለአሳዳጊ የተሰጠው ልጅዋ አድራሻው ያለመታወቁን ስታሰላስል ሳይታወቃት ፓኬጅ ሲጃራ ታቦናለች፡፡በአንድ አካባቢ ያደጉ ሴት ባልንጀሮቿ እኩያ ልጆች አድርሰው በማእረግ ሲኖሩ ስታይ እርር ድብን ትላለች፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣ 68)፡፡

> ጊዜው እየሄደ ነው፡፡ደብሪቱም የምትመኘውን ትዳር ሳትመሰርት እድሜዋ እየገፋ ነው፡፡ደብሪቱ ስሟንም ወደ ሪታ ቀይራለች፡፡ስራም ይዛለች ጥሩ ኑሮ እየኖረች ነው፡፡ ያለትዳር የገፋችው እድሜ በስተመጨረሻ ከአንድ ሰው ጋር ቢያገናኛትም የመውለጃ እድሜዋ አልፏል፡፡ከስራ ጡረታ የምትወጣበት ደብዳቤ ሲደርሳት ጊዜዋ ባክኖ መቅረቱ ታወቃት፡፡የደረሳትን የጡረታ ደብዳቤ እያነበበችም "የባከነ ጊዜ አለች ሪታ ደግማ ደጋግማ እያነበበች"፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣72)፡፡

ደራሲዋ በዚህ አጭር ልቦለድም ሴት ልጅ የፍቅር ምርጫ ላይ የሚደርስባትን ጫና አሳይታለች፡፡ ታሪኩ እንደሚያስረዳው በቤተሰብ ያለፍላጎት የሚደረግ የጋብቻ ጫና ለሴት

ልጅ እድሜ መባከን ምክንያት ይሆናል፡፡ የሴትን ልጅ የፍቅር ምርጫ መከልከል ላይ ባተረኮረው በዚህ ታሪክ ጋብቻ በመፈላለግ እንጅ በሀብት ደረጃ መወሰን እንደሌለበት ጸሀፊዋ ትተቻለች፡፡ የሴት ልጅ መብት በቤተሰብም መከበር እንዳለበት ካልሆነ ግን የሚያደርሰውን ኪሳራ "የባከነ ጊዜ" እንደሚሆን በታሪኩ አሳይታለች፡፡ መሰል አጉል ባህላዊ ልማዶችን ማሕበረሰቡ መንቀፍ እንደሚገባውም በታሪኩ አስረድታለች፡፡

### 4.2.6. "ሙላቱ"

"ሙላቱ" እና "ማርታ" የታሪኩ ዋና ገጸባህሪያት ሆነው የተሳሉበት "ሙላቱ" አጭር ልቦለድ ሴት ለትዳሯና ለልጇ ስትል የምታሳለፈው ውጣውረድ ላይ ያተኮረ ታሪክ ነው፡፡ ታሪኩ "ሙላቱ" እና "ማርታ" ትዳር መስርተው የአንድ ልጅ ወላች ከሆኑ ጀምሮ በማርታ ላይ የሚደርሰውን መከፋት፣የትዳር አለመስመር ያሳያል፡፡ ልጅ ከወለዱ ከ8 ወራት በኋላ የሙላቱ ጸባይ እየተቀየረ መምጣት ለፍቅሩ እና ትዳሩ የነበረውን ቦታ በመተው ወደ ቀድሞው ሕይወቱ ወደ መጠጡ በቡና ቤት ወደ ማምሸቱ ማዘውተሩን በልቦለዱ ቀርቧል፡፡

> የተወውን መጠጥ እንደገና ሲጀምረው የገነባው ትዳሩ እንደሚፈርስ አላሰበውም፡፡ ጭራሹን ሰክሮ እየተወላገደ ይመጣና ለመማታትም ይሞክራል፡፡አንዳንዴማ በወንደላጤነቱ ጊዜ ያሳለፈውን ሁሉ እያነሳ ትዳሩን ያማርራል ይሳደባል፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣83)፡፡

ማርታ ትዳሯን ከመበተን ለመታደግ እና ልጇንም ያለ አባት ላለማሳደግ ብዙ ጣረች፡፡ሙላቱ ግን በሱስ ሕይወት ቀጠለበት፡፡ቤቱን ትቶ ውጭ ማደር እና ከነአካቴው ወደ ቤቱ መምጣትን ቀስ በቀስ እየተወ መጣ፡፡ ብዙ የታቀደለት ትዳርም በአጭር በፍች ተቋጨ፡፡ሙላቱ ትዳሩን ፈቶ ገንዘብ ካላት የቡና ቤት ባለቤት ጋር ግንኙነት ጀመረ፡፡ ከባለሀብቷ ጋር የጀመረው ግንኙነት የህይወቱ ፍጻሜ ሆነ፡፡በቡና ቤቱ ከሚሰራ እና ከባለሀብቷ ጋር ግንኙነት ካለው ሌላ ፍቅረኛዋ ቶሎሳ ጋር በተፈጠረ ግጭት በጩቤ ተወግቶ ሞተ፡፡"ወይኔ ማርታ ወይኔ ልጄ እበላለሁ ብየ ተበላሁ ብሎ ጸጥ አለ"፡፡ (የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣90)፡፡

በዚህም አጭር ልቦለድም ደራሲ የምወድሽ ዋና ትኩረት ያረገችው ሴት ፣ ትዳር እና ሱስ ላይ ነው፡፡ ሴት ልጅ በትዳር ውስጥም የምታሳልፈውን ስቃይ ለልጇ ብላ የምትከፍለውን ዋጋ ያሳየችበት ታሪክ ነው፡፡ እንዲሁም ሱስ ለቤተሰብ መበተን የሚዳርግ እና ሕይወትንም

የሚያሳጣ በዚህም ሴት ልጅ ተጎጅ መሆኗን ለታሪኩ በተሳሉት ገጸባህሪያት ሕይወት አሳይታለች፡፡

### 4.2.7. "ቁጭት"

"ቁጭት" በሰራችው ወንጀል እስር ቤት ገብታ የምትጸጸት ባለታሪክ ላይ የሚያጠነጥን አጭር ልቦለድ ነው፡፡ የልቦለዱ ዋና ገጸባህሪ የውብዳር በአቻ ግፊት ያለእድሜዋ ጾታዊ ግንኙነት ጀመረች፡፡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ የነበረችው የውብዳር ያለ አባት ያሳደጓት እናቷን ጥሩ ደረጃ ደርሳ ለመጦር ህልም ነበራት፡፡ነገር ግን የእለት ጉርስ ከማያሳስባቸው የሀብታም ልጆች ጋር በፈጠረችው ጓደኝነት ውሎ እና አዳሯ ጭፈራ ቤት በመሆኑ ያለእድሜዋ ተደፈረች፡፡

የፈጸመችው የተሳሳተ ድርጊት እና የደረሰባት መደፈር በትምህርቷ እየቀነሰች እንድትመጣ አደረጋት፡፡ ጥሩ ውጤት ማምጣት አልቻለችም ሚኒስትሪን ወደቀች፡፡ ከዚህ በኋላ በልጅነቷ ወደ ሴተኛ አዳሪነት ገባች፡፡ ከተለያዩ ወንዶች ጋር በምታደርገው ጾታዊ ግንኙነት አባቱን የማታውቀው ልጅ አርግዛ ወለደች፡፡

የልጅ እና የእናቷን የእለት ጉርስ ለመሙላትም ሴተኛ አዳሪነቱን ገፋችበት፡፡በዚህ መሀል አብራው ካደረችው ወንድ ኪስ ያለፈቃድ የወሰደችው 3 መቶ ብር ለእስር ዳረጋት፡፡ እንዳሻው ሲያደርጋት የነበረው ወንድ የጎደለውን ማጀቷን ለመሙላት በወሰደችው 3 መቶ ብር ለፖሊስ አሳልፎ ሰጣት፡፡በፈጸመችው ወንጀልም የ 1 አመት እስር ተፈረደባት፡፡

> እናቴ በሌብነት ወንጀል ተከሰሼ እስራት ሲበየንብኝ ልጄን አዝላ ውሳኔውን ትሰማ ነበርና፡፡ በሁለቱ ጉንጮቿ ዕንባዋን ዘራችው፡፡ ዋ! የዛሬው ቁጭት ምን ሊያደርግልኝ ብላ የውብዳር ዕንባዋን ስትጠርግ የወሕኒ ቤቱ የጥበቃ ፖሊስ ፊሽካ አሰማ፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም ፤1982፣ 97)፡፡

የታሪኩ ዋና ማጠንጠኛ ጭብጥ ታዳጊ ሴቶች በአቻ ግፊት ለተለያየ ችግር ተጋላጭ እንደሚሆኑ የሚያሳይ ነው፡፡ በእንደዚህ አይነት ታሪኮች ያለእድሜያቸው ለጾታዊ ጥቃት፣ለስነልቦና ችግር ከዛም ሲያልፍ ለሴተኛ አዳሪነት፣ለእስር ተጋላጭ የሆኑ በርካታ ሴቶች መኖራቸውን ጸሀፊዋ በዚህ ታሪክ አሳይታለች፡፡ ሴት ልጅ በሚኖርባት ሀላፊነት ችግሮችን ብቻዋን እንድትጋፈጥ እንደምትገደድ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል፡፡

### 4.2.8. "ፈላጊዋ"

"ፈላጊዋ" አጭር ልቦለድ በትዳር ላይ የሚፈጸም ውስልትና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር ወንጀል ላይ የሚያተኩር ታሪክ ነው፡፡ ዋና ገጸባህሪያት ሆነው የተሳሉት ወይዘሮ "ስንቅነሽ" እና "ዓይናለም" ናቸው፡፡ የወይዘሮ ስንቅነሽ ባለቤት ማረፉን ተከትሎ በሚሰማ የለቅሶ ጥሩንባ የሚጀምረው ታሪኩ የሟቹን አማሟት በመፈለግ ላይ የሚያጠነጥን የወንጀል ምርመራ ታሪክን ያሳያል፡፡የወይዘሮ ስንቅነሽ ባለቤት ከተቀበሩ ሶስት ቀን በኋላ የሚጀምረው የሟች የአማሟት ምርመራ ለቤተሰቡ ድንጋጤን የፈጠረ ሆኗል፡፡

አቶ ለማ በቤታቸው በራፍ ላይ ወድቀው ቢገኙም ከጀርባቸው በስለት ተወግተው መሞታቸውን ፖሊስ በሀኪም ማስረጃ አረጋግጧል፡፡በታሪኩ "ግን ማነው የገደለው" የሚለው ነው አጠያያቂ የሆነው፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ዓይናለም የምትጠራጠረው ምናልባትም የሞታቸው ምክንያት ሊሆን የሚችል እውነታ እንዳለ የተናረችው፡፡

ዓይናም የሰፈር ነዋሪ ስትሆን ለሟች የሞት ምክንያት ወይዘሮ ስንቅነሽ(የሟች ባለቤት) እንደሆኑ ጠቆመች፡፡ጥቆማው የደረሰው ፖሊስም ባለቤቱን በጥብቅ መመርመሩን ቀጠለበት፡፡ወይዘሮ ስንቅነሽ ግን ወንጀሉን እንዳልፈጸሙ ደጋግመው መናገራቸውን ቀጥለዋል፡፡ዓይናለም ደግሞ ስታየው የነበረውን አጠራጣሪ ነገር ሁሉ ለፖሊስ መረጃ በየጊዜው ታቀብላለች፡፡

ፖሊስ የወንጀል ምርመራው በማጠናከር ወይዘሮ ስንቅነሽ በውሸት የአጎቴ ልጅ ነው ከምትለው ሲራክ ጋር የጀመረችው ፍቅር መኖሩን ደረሰበት፡፡ ፖሊስ ወይዘሮ ስንቅነሽ ከባሏ ጋር ለመለያየት  ወስና እንደነበርም ከሲራክ ማረጋገጥ ቻለ፡፡ወንጀሉን የፈጸሙት ባለቤት እራሳቸው መሆኑንም አወቀ፡፡

> እሺ አሁንማ ምኑን እደብቀዋለሁ የዚያ የደጉ ባለቤቴ የልጆቸ አባት ንጹህ ደም አጋልጦኝ እኔን ብሎ ገዳይ ፈላጊ ከእንግዲህማ ተፈላጊዋ እኔ ነኝ፡፡ በማለት የፈጸመችውን ወንጀል በሙሉ ተናዘዘች፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣112)፡፡

"አይ ! የባል ገዳይ ፈላጊዋ ብሎ መርማሪ ፖሊስም ራሱን በመነቅነቅ ተገረመ"፡፡(የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፣1982፣113)፡፡ በዚህ ታሪክ ዋና ጭብጥ ሆኖ የተነሳው የወንጀል ምርመራ ነው፡፡ ደራሲዋ ወንጀል በረቀቀ መልኩ የራሴ በሚሉት የቅርብ ሰው ሊፈጸም እንደሚችል

በታሪኩ አሳይታለች፡፡ በሚፈጸም ወንጀል ወንጀለኛውን ለህግ በማቅረብ እና ፍትህን ለማስፈን ደግሞ እንደ "ዓይናለም" ወንጀልን አጋላጭ መሆን እንደሚገባ ነው፡፡

በተለይም "ቁጭት" እና "ፈላጊዋ" አጭር ልቦለዶች የምወድሽ በፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ በወንጀል ምርመራ ላይ ከሰራቻቸው ዘገባዎችና ገጠመኖች መነሻነት የተደረሱ ይመስላል ምክንያቱም ወንጀል ነክ የሆኑ የምርመራ ዘገባዎች ለድርሰት መነሻ ሀሳብ እንደሆኑ፣የወንጀል ታሪኮች ለድርሰቶቿ ብዙ እገዛ እንዳደረጉላት በምዕራፍ ሶስት በቀረበው የሕይወት ታሪኳ መረዳት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም የባከነ ጊዜና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች በብዛት ዋና ትኩረታቸው ሴቶች ላይ አድርገው የተደረሱ ናቸው፡፡የምወድሽ እነዚህን ታሪኮች ለመጻፍ ከማህበረሱ ውስጥ ያሉ እውነታዎችን መነሻ ብታደርግም ሴቶች ላይ ለምን አተኮረች ብሎ መጠየቅ ተገቢነት አለው፡፡ ሴቶች በብዙ ጫና ውስጥ የሚያልፉ መሆኑን በአጫጭር ልቦለዶች በተደጋጋሚ ያሳየችበት ምክንያት ሴት መሆኗ፣ የሶስት ሴት ልጆች እናት መሆኗ እንዲሁም በስራ ሕይወቷ ያየቻቸው የወንጀል ታሪኮች መሆኑን ያሳያል፡፡ እነዚህ ምክንያቶች የሴቶች ህመም አብልጦ እንዲሰማት ወደ ድርሰት እንዲቀየሩም ገጠመኝን ፈጥሯል፡፡

## 4.3. ረጅም ልቦለድ

### "ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች" (2002 ዓ.ም.)

"ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች" አንድ አብይ ታሪክና ለታሪኩ አጋዥ የሆኑ ንኡሳን ታሪኮችን ይዟል፡፡ ከውጭ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ከመጣች ሰባት አመት ከሆናት እንግሊዛዊት "ሚስማርጋሬት" ቤት የሚጀምረው የልቦለዱ ታሪክ በቤቱ ባለቤት የቤት ሰራተኞች ሆነው የተሳሉ 3 ሰራተኞችን ጨምሮ የታሪኩ ዋና ጉዳይን የያዘችውን ህይወትን ዋና ገጸባህሪ በማድረግ በየተጻፈ ነው፡፡ 2 መቶ የገጽ ብዛት ያለው ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች ረጅም ልቦለድ ዋና ታሪኩ በሴት ላይ የተፈጸመ የግድያ ወንጀል ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

በእንግሊዛዊቷ ሚስ ማርጋሬት አትክልተኛ ሆኖ የተቀጠረው ነጋልኝ ልክ እንደወትሮው አትክልት ሲኮተኩት ያላሰበው አስደንጋጭ ነገር ገጠመው፡፡ የሚቆፍርበትን ዶማ ከመሬቱ ጋር አጣብቆ የያዘው እንግዳ ነገር ተፈጠረ፡፡ ከወትሮው የተለየ ስለነበር ነጋልኝ ቁፋሮውን አጠናክሮ ቀጠለ፡፡ከትንሽ ሰአታት ቁፋሮ በኋላ ግን ያገኘው የሰው አስከሬን ፣ከሙዚቃ

ክር(ካሴት) ጋር ነበር፡፡አስከሬኑ ማንነቱን ለመለየት ቢያስቸግርም የሴት አስከሬን መሆኑን ግን ለማወቅ አልተቸገሩም ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ነው የወንጀል ምርመራው የሚጀምረው፡፡ ሚስ ማርጋሬትን ጨምሮ ሰራተኞቹ ለፖሊስ ቃላቸውን ሰጡ፡፡ፖሊስ ግን አትክልተኛውን ነጋልኝን በእስር እንዲቆይ አደረገው፡፡

ነጋልኝ አዲስ አበባ ማንም የሚያውቀው ሰው ባለመኖሩ ዋስ ሁኖ የሚያስፈታው አጣ ያለዋስ የቀጠሩት አሰሪው እንኳን ዋስ ሊሆኑት አልፈለጉም፡፡ነጋልኝ በእስር ቤት የሚያሳልፋቸውን ጊዜያት እና የወንጀሉን ፈጻሚ ለማግኘት የሚደረገውን የምርመራ ሂደት እስከመጨረሻው የሚያሳይ ልቦለድ ነው፡፡

በዚህ ረጅም ልቦለድ ወንጀል ፈጻሚዎች ለምን ወንጀልን እንደሚፈጽሙ፣እስር የሚፈረድባቸው ወንጀል የሰሩ ናቸው ወይስ እንደ ነጋልኝ ዋስ በማጣት ወንጀል መፈጸማቸው ሳይረጋገጥ ነው የሚታሰሩት የሚለውን ለማረጋገጥ ወንጀል ሳይፈጽም የታሰረ ደራሲም የሚያደርጋቸውን ማጣራቶች የምርመራ ስራዎች ደራሲዋ በልቦለዱ አሳይታበታለች፡፡

በትዳር ላይ በሚደረጉ ውስልትናዎች የግድያ ወንጀል እንደሚፈጸምም ደራሲዋ እንዲህ አስፍራለች፡፡

> ይገርመኛል ከወንዶቹ ሴሰኝነት ይልቅ ሴቶቹ ናቸው አንጀቴን የሚያበግኑኝ ባለትዳር ትሁን ሴተላጤ አለቃዋ አብሯት መጋደሙን እንደ ጀግንነት ትቆጥረዋለች ተምራ በዕውቀቷ ሰርታ ማደሯን አትተማመንበትም፡፡በወሲብ ድሪያው ነው ሕይቷን ለመለወጥ የምትሻው፡፡አለቃዋ ጉያ መወደቋ ሳይበቃት በንቀት ለማየት የሚዳዳት ሞልታለች፡፡እኔ እንጃ በተወሸሙ ቁጥር የበላይ የሆኑ ይመስላቸው ይሆን?አንዳንዶቹን ብታዩ በማያውቁት ጉዳይ ሁሉ ውሳኔ ሰጭዎች የሚሆኑበት አጋጣሚም ይስተዋላል፡፡አለቅየውን ለማነጋገር የፊት ለፊት ጸሀፊ የድብቅ ውሽማውን መልካም ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልግበት ጊዜም አለ፡፡ በአደባባይ ስለዝሙት የሚያወግዙ አንዳንድ የስራ ሀላፊዎችም ውግዘቱ ቢሮየን አይጨምርም ያሉ ይመስላል፡፡ ይኸው እንዲህ አይነቱ ጋጠወጥነት የሰውን ሕይወት ያሰናክላል፡፡ለእኩይ ተግባርም መንስኤ ይሆናል ብቻ ከብትነት ነው፡፡(ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች፣2002 ፣96)፡፡

ከዚህ የታሪኩ ሀሳብ እንደምንረዳው ከትዳር ውጭ የሚማግጡ ሴቶችም ወንዶችም ለብዙዎች የሰው ቤት መፍረስ ምክንያት እንደሆኑ ነው፡፡እንዲሁም ለቤተሰብ መበተን መንስኤ የሚሆኑ መሰል ሰዎች ለወንጀል መፈጸም መበራከት እየሆኑ እንደሆነ በታሪኩ ከተፈጸመው ወንጀል ጋር ተያይዞ እንዲሄድ የተደረገበት ነው፡፡

ታሪኩ ሲቀጥል ተቀብራ የተገኘችው ሴት ግድያ በመሰል ድርጊት የተፈጸመ ወንጀል እንደሆነ ነው፡፡አትክልተኛው ነጋልኝ የወንጀሉ ፈጻሚ ባይሆንም በእስር ቤት ሆኖ የቀደመ ታሪኩን ሲያስታውስ እስሩ የሚገባው እንደሆነ ይናገራል፡፡ቀድሞ በነበረው ታሪኩ ይኖርበት ከነበረው ጅማ ወደ አዲስ አበባም የመጣውም በሰራው ወንጀል በአካባቢው ማህበረሰብ በመገለሉ ነው፡፡

በጅማ አግብቶ እና ወልዶ ይኖርበት በነበረው ሰላማዊ ኑሮ አንድ ቀን የፈጸመው ስህተት ከቀየው እንዲወጣ አድርጎታል፡፡ሚስቱ በጎረቤት ከሚኖር ሰው ጋር ግንኙነት እንዳላት መስማቱ ሚስቱን እንዲገድላት ምክንያት እንደሆነው እና ለፈጸመው ወንጀልም ተፈርዶበት ከእስር ሲወጣ ወደ አዲስ አበባ እንደመጣ ታሪኩ ይናገራል፡፡

“ሚስማር ጋሬት” ፣“አትክልተኛው ነጋልኝ” እና ሌሎች የቤት ሰራተኞች ወንጀሉን እንዳልፈጸሙ በሚያሳየው ታሪክ ወንጀለኛው እንዲያዝ ግን ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸው በታሪኩ ቀርቧል፡፡ ተቀብራ የተገኘችው ሕይወትን ማን ገደላት?፣ወንጀሉስ እንዴት ተፈጸመ? የሚለው የወንጀል ምርመራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ከሴቷ አስከሬን ጋር የተገኘው ማስታወሻን እና ካሴት መነሻ በማድረግ እስከመጨረሻው በመከታተል ትክክለኛ ወንጀል ፈጻሚው “ደንድር ኬሬ”ን ከአዲስ አበባ ወደ አዳማ ሄዶ ከተደበቀበት ሲያዝ እና ሲፈረድበት የሚያሳይ ልቦለድ ነው፡፡

የምወድሽ በፍቅር የጠማቸው ረጅም ልቦለድ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ግድያን ፣በአንጻሩ ደግሞ ሴቶች ላይ ለሚፈጸም ወንጀል ራሳቸው ሴቶችም ተጠያቂ መሆናቸውን በየቤቱ ፍቅር የጠማቸው በርካታ ነፍሶች መኖራቸውንም አሳይታለች፡፡ ሰዎች ውስጣቸው ሲታወክ ስሜታቸው ሲነካ ወዳልወደዱት ነገር ይገባሉ፡፡ ይህም በልቦለዱ በእነ “ሕይወት” ሕይወት ላይ ይታያል፡፡

የምወድሽ በቀለ በጥቅሉ የኑሮ ውጣውረድን እና ምስቅልቅል ችግሮች በፍቅር የጠማቸው ልቦለድ ላይ አሳይታለች፡፡እንዲሁም ወንጀል በረቀቀ ሁኔታ እንደሚፈጸም፣ የወንጀል

ውስብስብነት እና ወንጀል ፈጻሚውን ወይም ጥክክለኛውን ወንጀለኛ ለማግኘት የሚደረግን የወንጀል ምርመራ ሂደት በልቦለዱ ይታያል፡፡የፍትህ ሂደት አድካሚ እና የምርመራ ሂደቱ ጥንቃቄን የሚፈልግ እንደሆነም የምወድሽ በዚህ ረጅም ልቦለድ መንገዱን አቅርባበታለች በአጠቃላይ "ፍቅር የጠማቸው" ረጅም ልቦለድ ወንጀል ነክ ታሪክ ላይ የሚያጠነጥን እና የወንጀል ምርመራን ሂደቶች የሚያስረዳ ነው፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በየምወድሽ በቀለ ወልደገብርኤል የህይወት ታሪክና ስራዎቿ ላይ የተደረገ ነው፡፡ ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን የየምወድሽ በቀለ ውልደትና አስተዳደግ፣ የትምህርት ቤት ሕይወት፣ የስራ አለም፣ የድርሰት ሕይወት፣ የንባብና የመጻፍ ልማድ፣ የግል አመለካከት፣ ሐይማኖት፣ የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ በሌሎች ማህበራዊ ስራዎች ላይ ስላላት ተሳትፎ እንዲሁም በግሏ እና ከሌሎች ጸሀፍት ጋር በጋራ የሰራቻው ድርሰቶችን አሳይቷል፡፡

የጋዜጠኝነት ስራን በስድስት ወር ስልጠና ቀጥሎም በዲፕሎማ ባገኘችው ትምህርት የጀመረችው የምወድሽ "በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ" በተልእኮ ተምራ በ"ፐብሊክ ሪሌሽን ኤንድ ኮሚኒኬሽን" የመጀመሪያ ድግሪዋን አግኝታለች፡፡ በተጨማሪም የስነጽሁፍ ትምህርቷን በኔዘርላንድ ኤምባሲ ባገኘችው እድል "በሮያል ኮሌጅ" ከ 25 ሴት ደራሲያን ጋር ለ አስር ወራት ተምራለች፡፡ የምወድሽ አሁን ላይ የ63 አመት ጎልማሳ ስትሆን በ"ሊደርሽፕ እና ፕሮጀክት ማኔጅመንት" ሁለተኛ ድግሪዋን በ 2015 ዓ.ም.አግኝታለች፡፡

የመጀመሪያ ድርሰት ስራዋ የታተመው በ1972 ዓ.ም በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አማካኝነት ሲሆን ይህ ጥናት እስከተደረገበት 2016 ዓ.ም. ድረስ በግሏ እና ከሌሎች ደራሲያን ጋር በጋራ 16 መጻሕፍትን ለአንባቢያን ማድረስ ችላለች፡፡ በ 1974 ዓ.ም መጨረሻ በፖሊስ ሚዲያ "ፖሊስና ርምጃው" ጋዜጣ ስራ ጀምራለች፡፡ በዚሁ ጋዜጣ 26 አመታትን ያገለገለችው የምወድሽ ሲቪል መርማሪ ጋዜጠኛ በመሆን የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መነሻ በማድረግ የምርመራ ዘገባዎችን ሰርታለች፡፡

ከፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ በተጨማሪም በብሌን ቁጥር 3 መጽሄት በ1999 ዓ.ም "አርትኦት ምንድን ነው? አርታኢስ ማነው"? በሚል ርእስ አርቲክል በመጻፍ አስነብባለች፡፡ ከፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ በጡረታ ከወጣች በኋላም ሙያውን ቀጥላበታለች፡፡ "የምወድሽ ገጾች" በሚል የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጅታ እያቀረበች ነው፡፡

የምወድሽ በግሏ ከምትሰራው የጋዜጠኝነት ስራ በተጨማሪ በ 2007 ዓ.ም.“Women Can Do It” (ሴቶች ይችላሉ) የተሰኘ የበጎ አድራጎት ሀገር በቀል ድርጅት በመክፈት እና በመምራት በሴቶች ዙሪያ እየሰራች ትገኛለች፡፡ የምወድሽ በቀለ ባለትዳር እና የሶስት ሴቶች እንዲሁም የአንድ ወንድ ልጅ እናት ናት፡፡

ለቤተሰቦቿ ብቸኛ ሴት ልጅ መሆኗ ፣ የሶስት ሴት ልጆች እናት መሆኗ ስለሴቶች በተደጋጋሚ እንድታነሳ ተፅእኖ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የጋዜጠኝነት የስራ ሕይወቷ በወንጀል ላይ ያተኮረውን “ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች”ን ረጅም ልቦለድ ለመጻፍ መነሻ ገጠመኞችን ፈጥሮላታል፡፡

በልጅነቷ አባቷ በየሳምንቱ ይገዙላት የነበሩ የአጫጭር፣የረጅም ልቦለድ ታሪኮች እና የግጥም መጻሕፍት አሁን ላይ በተለያዩ የሥነፅሑፍ ዘውጎች ድርሰቶችን እንድትጽፍ አስችሏታል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ሐረገወይን ሸዋረጋ፡፡"በባህርዳር ከተማ የታዋቂ አዝማሪዎች የሕይወት ታሪክ እና ቃላዊ ግጥሞች ክዋኔ፡፡"አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለአማርኛ ቋንቋ የስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መረሃ ግብር ማሟያነት የቀረበ 2004፡፡

ማሚ ግርማ፡"የአርቲስት ጌታቸው ደባልቄ የሕይወት ግለታሪክና ኪናዊ ስራዎቻቸው፡፡" አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለአማርኛ ቋንቋ የስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መረሃ ግብር ማሟያነት የቀረበ፣2007፡፡

ሣህለ ሥላሴ ብርሀነ ማሪያም፡፡ "ባዮግራፊ አውቶባዮግራፊ፡፡" ብሌን፤ ቁጥር4፤መጽሔት 1999፡፡

የምወድሽ በቀለ፡፡አብዮታዊ ግጥሞች፡፡አዲስ አበባ፣ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣1972፡፡

………………፡፡የባከነ ጊዜ እና ሌሎችም፡፡አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣1982፡፡

………………፡፡ዕጣ፡፡አዲስ አበባ፣ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፣1995፡፡

……………..፡፡ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች፡፡ፋር ኢስትትሬዲንግኃላ.የተ.የግ.ማህበር፣2002፡፡

……………..፡፡ዋኒኖስ፡፡አዲስ አበባ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር፣2003፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡አዲስ አበባ፣ተፈራ ስዩም ማተሚያ ቤት፣2006፡፡

አንዱአለም ሽመልስ ፡፡"የቋንቋ አጠቃቀም እና የአተራረክ ቴክኒክ በእብዷ በለጠች ኖቬላ ልቦለድ፡፡"አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጽሁፍ፣1998፡፡

ኤልሳቤጥ መኩሪያ ፡፡ "የደራሲ ይልማ ሃብተየስ እጅጌ የሕይወት ታሪክ፡፡"አዲስ አበባ፣

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጽሁፍ፣ 2009፡፡

እዝራ እጅጉ፡፡ መዝገበ አእምሮ፡፡ አዲስ አበባ ተወዳጅ ሚዲያ እና ኮሚኒኬሽን፣ ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2014 ፡፡

ዘነበ ወላ፡፡ማስታወሻ፡፡አዲስ አበባ፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር፣2009፡፡

ጌታቸው አበበ፡፡የኢትዮጵያ ደራሲያንና ሥራዎቻቸው ክፍል አንድ፡፡ አ.አ.ዩፕሬስ፣ብራና ማተሚያ ድርጅት፣2011፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነ ቃል መምሪያ፡፡አዲስ አበባ፣ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አሳታሚዎች፣1991፡፡

…………..፡፡ፕሮጀክት፡፡“ግለታሪካዊ ጥናታዊ ጽሁፍ፡፡”1999፡፡

ፋንታሁን እንግዳ፡፡ ስነጽሁፋዊ ሙዳዬ ቃላት ከነማብራሪያቸው፡፡አዲስ አበባ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣2003፡፡

Biratu Keneni. “Brigadier General Taddasa Birru Amilitry Political Biography (1922-1975).”Addis Ababa University, College Of Social Sciences Department Of History, In Partial Fulfilment Of The Requirements For The Degree Of Doctor Of Philisophy In History,2019.

Edele,Leon.*Litrary Biography*.New York ,Double Day,1959.

Freeman,William. *Biographics Scintists and Investors*, London sir Isac Piturm & Sons LTD, 1954.

Kendall,Paul Murray. *Biographical Literature*. In The New Encyclopedia Britannica, 15th ed. Vol. 23. Edited by Philip W.Goetz.Chicago: Inc,1986.

Liers,Frederick.*Biography."In New Dictionary of the History of Ideas*. Vol.1, Editor centre for the study of the horn of Africa ,2005.

Reidulf,K.Molvaer. *Black Lion*s. The creative lives of modern Ethiopian's litrary giants and pioneers.Asmara, Eritrea:The Red Sea Press, Inc,997.

Robin,Fleming."*Writing Biography at the Edge of History*."Oxford University Press on behalf of the American Historical Association Vol. 114, No. 3 , 2009.

Show,Harry.K. *Black Lion.* The Crative Biography of Mans Litracy, USA: Mc-hill Press,Inc,1997.

……………….Dictionary of Litracy Terms, USA:Mc-hill Press,Inc,1997.

Tamrat Haile."Yilma Deressa A Political Biography (1907-1979)."Addis Ababa University, College Of Social Sciences Department Of History, In Partial Fulfilment Of The Requirements For The Degree Of Doctor Of Philisophy In History ,2016.

The Cambirige Encyclopidia Literature. New York Cambirige University Press, 1990.

……………..vol. II,a New Encyclopdiaya Britanica, inc,1993.

The New Encyclopedia Britannica,15th edition, Vol. 2. Edited by Robert Mc Henry. The University of Chicago Press, 1993.

Zerihun Asfaw."Stories of Women in the Novels of Selected Ethiopia Women."Addis Ababa University, Ethiopian Journal of Languages and

Literature, Vol. XII No. 2, 2012.

http://keydifferences.com/difference-between-biography-and-autobiography.

## አባሪ አንድ
## ለየምወድሽ በቀለ የቀረቡ ጥያቄዎች

1.የአንችን ሙሉ ስም የእናት እና የአባትሽን ሙሉ ስም ብትነግሪኝ?

2.መቸ ተወለድሽ አመተምህረት ቀንና ወሩ መቸ ነው?

3.የተወለድሽበት ቦታ እና የመንደሩ ልዩ ስም?

4.የምን ሀይማኖት ተከታይ ነሽ እናትና አባትሽ የምን ሀይማት ተከታይ ናቸው?

5.የእናትና የአባትሽ ስራ ምን ነበር?

6.የአስተዳደግ ሁኔታሽ እንዴት ነበር?

7.ትምህርት መቸ ጀመርሽ የት ትምህርት ቤት የከፍተኛ ትምህርትሽን የት ተማርሽ ያጠናሽው ትምህርት ምን ነበር?

8.የሥነ ጽሁፍ ዝንባሌ እንዳለሽ መቸ እና እንዴት አወቅሽ?

9.መጻፍ መቸ ጀመርሽ ?

10.በድርሰቶችሽ በተደጋጋሚ የምታነሻቸው ዋና ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

11.በአብዛኛው ማንበብ የምትወጅው ምን አይነት ጭብጥ እና ዘውግ ላይ ያተኮረ ድርሰት ነው?

12.በተለያዩ ዘውጎች ለመጻፍሽ ምክንያቱ ምንድን ነው? እንዴት?

13.በድርሰቶችሽ የምታነሻቸው ጉዳዮች ከግል ሕይወትሽ ግንኙነት አላቸው? ለምን በእነዚህ ጉዳች ትኩረት አደረግሽ?

14.ከስነጽሁፍ እና ከጋዜጠኝነት ሙያ ውጭ የተሰማራሽበት የሙያ ዘርፍ አለ?

15.ከመስሪያ ቤት የስራ ባልደረቦችሽ ጋር ያለሽ ቅርርብ እና ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?

16.መደበኛ ስራሽን እና የድርሰት ስራሽን እንዴት በአንድ ላይ ማከናወን ቻልሽ?

17.ድርሰት እንድትጽፊ ተፅእኖ ያሳደረብሽ ደራሲ ፣ጓደኛ፣ቤተሰብ አለ ወይ?

18.ለጋዜጠኝነት ሙያስ ተጽእኖ ያሳደረብሽ ሰው አለ?

19.ድርሰት ስትፅፊ የምትመርጭው ቦታ እና ሁኔታ አለ ወይ?

20.በድርሰት ስራዎችሽ ላይ ያጋጠመሽ መጥፎ ወይም ጥሩ አጋጣሚ ካለ ብትነግሪኝ?

21.በጋዜጠኝነት ሙያ ያጋጠመሽ ጥሩ ወይም መጥፎ ነገር አለ?

22.የድርሰት ስራዎችሽን እያነበበ የሚያርምሽ በመደገፍም ሆነ በመቃወም ሀሳብ የሚሰጥሽ ሰው ነበረ?

23.በድርሰት ስራዎችሽ እና በጋዜጠኝነት ስራዎችሽ ያገኘሽው ሽልማት እና ሹመት አለ?

24.በድርሰት ስራና እና ጋዜጠኝነት ሙያ የክስ ጉዳይ ገጥሞሽ ያውቃል?

25.ወደፊት ለመስራት ያሰብሻቸው ድርሰቶች እና ሌሎች ስራዎች አሉ?

26.ስለ ሕይወት ያለሽ አመለካከት ምን ይመስላል?

27. የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያሽ ብትነግሪኝ? ምን ያዝናናሻል ለምን?

**አመሰግናለሁ፡፡**

## አባሪ ሁለት

## ለጋዜጠኛ ኮማንደር ተስፋዬ ምትኩ የቀረቡ ጥያቄዎች

1.ሙሉ ስም፣የትውልድ ዘመን፣የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ሁኔታ ቢነግሩኝ?

2.ከየምወድሽ ጋር የተዋወቁበት ጊዜ መቸ ነበር?

3.ትውውቃችሁ በምን ላይ የተመሰረተ ነው?

4.ከእርሰዎ ጋር የነበራት ቅርበት ምን ያህል ነበር?

5.አብራችሁ የሰራችሁበትን ተቋም ቢነግሩኝ?

6.ምን ያህል ጊዜ አንድ መስሪያ ቤት ሰራችሁ?ቀድሞ የገባው ማን ነበር?

7.የምወድሽ በቀለ በስራዋ ላይ ያላት የግል ሁኔታና ባህሪ?ለስራ ያላት የግል አቋም?

8.አብራችሁ ስትሰሩ ከጋዜጠኝነት ስራው በተጨማሪ ሌሎች ስራዎች ላይ ያላት ተሳትፎ ምን ያህል ነበር?

9.ከስራ ውጭ ያላትን ማህበራዊ ተሳትፎዋን ቢነግሩኝ?

10.የምወድሽ ስለምታነባቸው መጽሀፎችና መጽሄቶች የሚያስታውሱት ካለ ቢነግሩኝ?

11.የምወድሽ ከጻፈቻቸው ድርሰቶች ምን ያህሉን ያውቃሉ?ምን ያህል ስራዎቿን አንብበዋል?ድርሰቶቿን አንብበው አስተያየት አለ ወይ?

12.በስራ የገጠማችሁ ጥሩም ይሁን መጥፎ አጋጣሚ አለ?

13.ስለየምወድሽ ሊነግሩኝ የሚፈልጉት ተጨማሪ አለ?

**አመሰግናለሁ፡፡**

## አባሪ ሶስት

## ለወይዘሮ መሰረት ነጋ የቀረቡ ጥያቄዎች

1.የአንችን ስም፣የእናትና የአባት ሙሉ ስም፣የትምህርት ደረጃና የስራ ሁኔታ ብትነግሪኝ?

2.ከየምወድሽ በቀለ ጋር ያለሽ ዝምድና ምንድን ነው?

3.ከየምወድሽ ጋር ያላችሁ ግንኙነት እና ቅርበት ምን ያህል ነው?

4.የምወድሽ የሚያስደስታትና የሚያሳዝናት ነገር ምንድን ነው?ስለግል ባህሪዋ ብትነግሪኝ?

5.ከየምወድሽ መፅሀፍ ምን ያህሉን አንብበሻል?ከመፅሀፎቿ በልዩነት የምትወጅው የትኛውን ነው?ለምን?

6.የምወድሽ ጋዜጠኛ በመሆኗ በቤተሰቡ ላይ ያመጣው ጥቅም ወይም ጉዳት አለ?በድርሰቱስ?

7.የምወድሽ ከልጆቿ ጋር ያላት ቅርበት ምን ያህል ነው?በቤት ውስጥ ምን አይነት እናት ናት?

8.ከቤተሰብ ውጭ ያላት ማህበራዊ ግንኙነት ምን ያህል ነው?

9.የምወድሽ ስትጽፍ እና ስታነብ ምን አይነት ቦታ ፣ሁኔታና ሰዓት ትመርጣለች?

10.የምወድሽ ለአንቺ በትምህርት ወይም በስራ የምታደርግልሽ ድጋፍ አለ?

11.በስራዋ ላይ የምትሰጫት አስተያየት እና የምታደርጊላት እገዛ ካለ ብትነግሪኝ?

12.ከቤተሰቡ ውስጥ የድርሰት ወይም የጋዜጠኝነት ሙያን የተከተለ አለ?

13.በጥቅሉ ስለ የምወድሽ ተጨማሪ ነገር ካለ ብትነግሪኝ?

አመሰግናለሁ፡፡

## አባሪ አራት

## ለደራሲ እንዳለጌታ ከበደ (ዶ/ር) የቀረቡ ጥያቄዎች

1.ሙሉ ስም፣የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ሁኔታ ብትነግረኝ?

2.ከየምወድሽ በቀለ ጋር የተዋወቃችሁበት ጊዜ መቸ ነበር?

3.ትውውቃችሁ በምን ላይ የተመሰረተ ነበር?

4.ከየምወድሽ ድርሰቶች ምን ያህሉን ታውቃለህ?ምን ያህሉንስ አንብበሀል?

5.ካነበብከው ውስጥ በተለየ መልኩ የወደድከው ድርሰት አለ ወይ?ካለ ለምን?

6.ከየምወድሽ ድርሰቶች አንብበህ የወሰድከው ቁም ነገር ካለ ብትነግረኝ?

7.በጥቅሉ ስለ የምወድሽ በቀለ ልትነግረኝ የምትፈልገው ካለ ብትነግረኝ?

**አመሰግናለሁ፡፡**

# አባሪ አምስት

## የየምወድሽ በቀለ የግጥም መጻሕፍት

| የድርሰቱ ርእስ | የህትመት አመተ ምህረት |
|---|---|
| አብዮታዊ ግጥሞች | 1972 ዓ.ም. |
| ያልፈራ ፍሬ እና ሌሎች የግጥም ስብስብ | 1992 ዓ.ም. |
| ዋጊኖስ የግጥም መድብል | 2003 ዓ.ም. |

## አባሪ ስድስት

## የየምወድሽ በቀለ የልቦለድ መጻሕፍት

| የድርሰቱ ርእስ | የህትመት አመተ ምህረት |
|---|---|
| የባከነ ጊዜ አጫጭር ልቦለዶች ስብስብ | 1982 ዓ.ም. |
| እብዱ በለጠች ኖቤላ ረጅም ልቦለድ | 1996 ዓ.ም. |
| ፍቅር የጠማቸው ነፍሶች ረጅም ልቦለድ | 2002 ዓ.ም. |

## አባሪ ሰባት

## የየምወድሽ በቀለ ኢ. ልቦለድ መጻሕፍት

| የድርሰቱ ርእስ | የህትመት አመተ ምህረት |
|---|---|
| ናዋጉ ምሁር | 2004 ዓ.ም. |
| የጀርባ ሐቆች | 2010 ዓ.ም. |
| ነገን በተስፋ አያለሁ | 2013 ዓ.ም. |
| ከባድ ቁስል | 2014 ዓ.ም. |

# አባሪ ስምንት

## የፎቶግራፍ አባሪዎች




የምወድሽ በቀለ በ2013 ዓ.ም. ለስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ሴት ተፎካካሪዎችን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡




የምወድሽ በቀለ በፖሊስናርምጃው ጋዜጣ ስትሰራ አባት አርበኛን ቃለመጠይቅ ስታደርግ፡፡


የምወድሽ በቀለ በአሀዱ ራዲዮ ስቱዲዮ የምወድሽ ገጾች ቀጥታ ውይይት ላይ፡፡



የምወድሽ በቀለ የጎዳና ልጆችን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡



የምወድሽ በቀለ በፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ ከባልደረቦቿ ጋር በስራ ላይ፡፡



የምወድሽ በቀለ በሴት ደራሲያን ማህበር ንግግር ስታደርግ፡፡




የምወድሽ በቀለ በ1996 ዓ.ም. በሴት ደራሲያን ክበብ ምረቃ ላይ ንግግር ስታደርግ፡፡




የምወድሽ በቀለ የካቲት 5 በ1997 ዓ.ም.የፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ 45ኛ ዓመት ክብረ በዓል ላይ ከጋዜጣው የስራ ሀላፊዎች ከነ ጄኔራል በቀለ ነዲ ጋር፡፡



ምን አስተዋለ?

ሕግ አስከባሪዎች ሕጉን በአግባቡ ይተረጉሙታል?

የምወድሽ በፖሊስና ርምጃው ጋዜጣ ትሰራቸው ከነበሩ ውስጥ "ምን አስተዋለ"አምድ ላይ የተወሰደ፡፡


የምወድሽ በአዲስ አበባ የጎዳና ልጆችን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡



የምወድሽ በቀለ የአፋር የኮሚኒቲ ፖሊስ አባላትን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡




የምወድሽ በቀለ የአድዋ ቀን ሲከበር አባት አርበኛን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡



የምወድሽ በቀለ የጎዳና ልጆችን ቃለ መጠይቅ ስታደርግ፡፡



በ1997 ዓ.ም.በአዲስ አበባ ስታዲየም “ድንቄም አዲስ አበባ” የተሰኘ ግጥም ስታቀርብ፡፡



የምወድሽ በቀለ ከደራሲ ስብሐት ገብረእግዚአብሄር ጋር፡፡



የምወድሽ በቀለ በአሀዱ ራዲዮ ስቱዲዮ በስራ ላይ፡፡



ደራሲና ጋዜጠኛ የምወድሽ በቀለ በ 2015 ዓ.ም. የተነሳ ፎቶ፡፡

**ይህ ጥናት የእኔ መሆኑን በውስጡም የተገለገልኩባቸው በሙሉ በራሴ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡**

**ስም-------------------------------------------------**

**ፊርማ-------------------------------------------------**

**የማስረከቢያ ጊዜ-------------------------------------**